# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፬ኛ ዓመት ቁ. ፫ ጥቅምት/ኅዳር ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## መስጠት የሚገባንን ክብር እንስጥ

የአንዳንድ መጻሕፍትም ሆኑ መጽሔቶች የፊት ለፊት ሽፋን ላይ የእመቤታችን ወይም የቅዱሳንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስ ቶስን ሥነሥዕል እመለከታለሁ:: እነዚህ መጽሐፍትም ሆኑ መጽሔቶች ሽፋናቸው ብዙም ጠ ንካራ ባለመሆኑ ከአያያዝ ጉድለት የተነሣ ይተሻሻሉ ከባሰም ይቀደዳሉ:: ይህ ደግሞ ለሥነ-ሥዕሎች መስጠት የሚገባንን ክብር የሚቀንስ ይመስለኛል:: በመሆኑም ስለመጻሕፍት አያያዝ ለአንባብያን ትምህርት ቢሰጥና በጥንቃቄ እንዲይዙት ቢደረግ ወይም ሥዕሎች በውስጥ በኩል መቀመጥ ቢችሉ መልካም ነው:: ሁላችንንም ስለሚመለከት ትኩረት ልንሰጠው ያስፈልጋል::

ግርማ አርጋው /ከጅማ ዞን -ሶኮሩ/
ሞላ ፈጠነ /ከ ደብረ ታቦር /

## ተዋሕዶ ውብነሽ

የአንዲት ጥምቀት መሠረት
የተጋድሎ ጽናት ሥምረት
የሳጥናኤል መንግሥት ውድቀት
የፈያታዊ ዘየማን ይቅርታ
የማርያም መግደላዊት ዕልልታ
ለሚያምኑባት ውበት ጌጧ
ለነአውጣኪ ትምህርት ድጧ
የጥል ግድግዳን አፍራሽ
በአንደበተ ኤፍሬም አወዳሽ
የእስጢፋኖስ ጽዋ ቅማሽ
የፊልጶስ ጥያቄ ምላሽ
ሐመረ ኖኅ የተባልሽ
ተዋሕዶ በእውነት ውብነሽ::

ከመምህርት ጺጋነሽ ዓለማየሁ
/ህገረ ሰላም/

## ሳየው የኋላዬን

ዘወር ብዬ ሳየው የኋላዬን
የጨለማ ኑሮ ስቃዬን
ምንኛ መራራ አስቸጋሪ ነበር
እየሰሙ ገደል እያዩ መቃብር
ዛሬ ግን ዓይኔ በርቶ
ደንዳናው ልቤ ተከፍቶ
የጌታዬ ፍቅሩን
በቅርብ ተመልክቼ
«ልጄ ሆይ ና»ሲለኝ ጥሪውን ሰምቼ
ትልቁን ግብዣውን
ሥጋውን በልቼ-ደሙንም ጠጥቼ
ይኸው እኖራለሁ
የዘላለም ደስታን-እረፍትን አግኝቼ

ሙሉነህ ተሾመ
/ግራዋ.ቅ/ጊዮርጊስ ሰ/ት/ቤት/

## ባዕድ አምልኮ እንጂ ባሕል አይዳለም::

በዘመን መለወጫና በመስቀል ሰሞን የታዘብኩት ነገር አለ:: ይኸውም አንዳንድ ሰዎች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስ ቲያን ጣኦት አምልኮን፣ በየጠ ንቋዩና በየቃልቻው ቤት መሄድን የፈቀደች ይመስል የሚያደርጉት ኢክርስቲያናዊ የሆነው ተግባር ሲጠየቁ «ባሕላችን ነው፣ ሃይማ ኖታችን አይከለክልም» ሲሉ ሰምቻለሁ:: ለምሳሌ ለእንቁጣጣሽ ቀይ፣ ነጭ፣ ጥቁር ወዘተ.. እያሉ ሲያማርጡና በመስቀል ዕለት በየወንዙ ሲያጓሩ የነበሩ ሁሉ እምነቴ ተዋሕዶ ነው ቢሉ ለእኔ አይዋጥልኝም:: ከሃይማኖታችን ሕግና ከቃለ እግዚአብሔር የሚ ለየን ባሕል - ባሕል ሳይሆን ራሱን የቻለ ሰይጣናዊ አምልኮ ነው:: ስለዚህ ይህንን በባሕል ስም የሚደ ረግ ባዕድ አምልኮ ብዙ የዋሐን ወገኖቻችን እየተከተሉት ነውና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ልናስተምር ያስፈልጋል:: ተለይ ከንስሐ አባቶች ብዙ ይጠበቃል:: ይህንን የሚፈጽሙ ሰዎች በጉባኤያት ወይም በመጽሔት በሚሰጥ ትምህርት ልናገኛቸው ስለማንችል ንስሐ አባቶች ሥራቸው ነውና እየጠሩ ወይም በየቤታቸው እየሄዱም ቢሆን ቢያስተምሩ የበለጠ ውጤት ይገኛል ብዬ አስባለሁ::

ከበደ ጣፋ /አ.አ/

## በጾም ጋብቻ!

በጾም ወቅት ጋብቻ መፈጸም የተከለከለ መሆኑ ይታወቃል:: አንዳንድ የእኛው ቤተክርስቲያን ሰዎች ግን በጾም ወራት በተለይም በገናና በሐዋ ርያት ጾም ወቅት ጋብቻቸውን ሲፈጽሙ ይታያል:: እኛም ይህ ጊዜ የጾም ወቅት ስለሆነ ሌላ ጊዜ ብትፈጽሙትስ ስንላቸው «ጾሙ የቄሶች ጾም ነውና ችግር የለውም» የሚል መልስ ይሰጡናል:: ስለዚህ ሌሎች አጽዋማት ጭምር እየተ ጣሉና እንደ ቅርስ በየገዳማቱ ብቻ ተወስነው ከመቅረታቸው በፊት ክርስቲያን ሁሉ መጾም እንዳለበት በየአጋጣሚው ትምህርት ሊሰጥ ያስፈልጋል::

ወ/ሚካኤል ኀ/ማርያም
/ጉሬ/

## ስትቆዝም

ብርሃን ተጋርዶብህ
ድንግዝግዝ ሲልቀኑ
ሕይወት ስትደፈርስ
ቀርቶባት መስከኑ
ልክ እንደመጫኛ
ችግርም ሲረዝም
አቅምህ ሲከዳህ
ክፉኛ ስትቆዝም
ዙሪያው ገባገደል
ሲሆንብህ ጉዞው
ጥላህ እግር አውጥቶ
ሲሄድ አንተን ጥሎህ
እግዚአብሔርን ተስፋ
መርኩዝህ አድርገህ
ሕይወትህን ምራ
ሁሉም ያልፋል ብለህ ::
ወንዶሰን ጎሣዬ /አ.አ/

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሐመር

4ኛ ዓመት ቁጥር 3

ጥቅምት/ኅዳር 1989 ዓ.ም


## ይዘት


የማኅበሩ መልእክት
- «ይህች ባቄላ...» .......... 2

ደብዳቤዎች .......... 3

ከሰሞኑ በረከት
- ልጄን ከግብፅ ጠራሁት .......... 5

ትምህርተ ሃይማኖት
- የእግዚአብሔር ሕግ .......... 7
- ብሉይ ኪዳን በሐዲስ ኪዳን .......... 9
- ቅዱሳን መላእክት .......... 11

የጥያቄዎቻችሁ መልስ
- ጸሎተ ፍትሐት .......... 13

ኪነ ጥበብ
- መሐንዲሱ .......... 14
- ሰባቱ ነገሮች .......... 16

እናስተዋውቃችሁ
- ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም .......... 18
- ጻድቁ አቡነ ሀብተ ማርያም .......... 20

ዓምደ ወራዙት
- የጽዋውን እና የውጭውን ወገኑ ማጥራት .......... 21
- ንስሐ ለምንና እንዴት? .......... 22

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- ጥያቄዎቻችሁ .......... 23
- ውርጃ .......... 24
- ወደ እውነት ለመድረስ ቤሐሰት ጉዳና? .......... 25

ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ
- የንዋየ ቅድሳት ዝርፊያ ከትናንት እስከ ዛሬ.27
- የቤተክርስቲያን ታሪክ .......... 29
- የምድረ ርስት ልጆች ነን .......... 30



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::


# ከአዘጋጁ

## ለቤተክርስቲያን ማሰብ የሁሉም ግዴታ ነው !

በክርስቶስ ክርስቲያን፣በወልድ ውሉድ የተባሉ ምእመናን ለእናት ቤተክርስቲያናቸው የማሰብ ፣ የመጨነቅ፣ የአቅማቸውን አስተዋፅዖም የማድረግ ሃይማኖታዊ ግዴታ አለባቸው:: ጥሩ ሥራ ሲሠራ ደስ የሚላቸውን ያህል ፣ክፉ ሥራም ሲሠራ «ለምን?» ብሎ መጠየቁ መብታቸው ነው:: ቅርሶች ሲዘረፉ፣ አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ ዝም ብሎ መመልከት ተገቢ አይደለም:: በትንሹ መቅጨት ካልተቻለ ነገ የማይነቀንቁት ትልቅ ቋጥኝ ሆኖ መቀመጡ አይቀርም:: መጽሔታችንም በ4ዓመታት ጉዞዋ ምእመናን ይህንኑ ያውቁ ዘንድ የበኩሏን ጥረት ስታደርግ ቆይታለች:: ወደፊትም ትገፋበታለች:: ስለዚህም ስለ መሠረተ እምነታችን ፣ስለ ትውፊታችንና ስለ ታሪካችን እንድናውቅ መጣጥፎችን ታቀርባለች:: የተጻፈውን ማንበባችን፣የሚሰጠውን ትምህርት መቀበላችን ግን የሚታወቀው በምንሠራው መልካም ሥራ ይሆናል::

እናት ቤተክርስቲያን ከውስጥ በሐሰተኛ ወንድሞች /ቢጽ ሐሳውያን/ ከውጭ በመናፍቃን፣ አላውያንና ከሐድያን እንዳትጠቃ መጠበቁ የልጆቿ ፈንታ ነው:: በየአጥቢያችን ንዋየ ቅድሳትን ከዘራፊዎችና በውስጣችን ካሉ አስዘራፊዎች፣ሰንበት ት/ቤቶቻችንን በክህደት ትምህርት ከሚበርዙ ፣ዓላማው ሳይገባቸው ከሚበትኑ ደካሞች መጠበቅ ይገባናል:: የወቅቱ ትልቁ ተግባር ይህ ነው:: ከእንቅልፋችን ነቅተን፣ ምን አገባኝ ማለትን ትተን ስለቤ ተክርስቲያን ለማሰብ፣ የሚገባንንም ለመፈጸም መነሣት ያስፈልጋል::

ለሁሉም እግዚአብሔር ይርዳን::አሜን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር::


ዋና አዘጋጅ ብርሃኑ ጎበና ካሣ

ም/ዋና አዘጋጅ ዲ.ደጀኔ ሺፈራው

ስልክ 550099 Ext 46

ፖስታ 80078

አዲስ አበባ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

## «ይህች ባቄላ...»

እሷ ኩሬ ውስጥ ሆና ማዶ መንደር ሲቃጠል ያየች እንቁራሪት «አውጣኝ... አውጣኝ...» እያለች ስትለምን ጓደኛዋ ሰምታ «አሁን ምንልሁን ብለሽ ነው አምላክን የምታስቸግሪው ? አንቺ ያለሽው ውኃ ውስጥ ፣ እሳት የት እንዳያገኝሽ ነው?» ብላ ስትቀልድባት «አይ ሞኝ እሳቱ እንዲጠፋ ውኃ የሚወስዱት ከዚህ መሆኑን ረሳሽው? ያንጊዜ አብረን መወሰዳችንና እሳቱም ለኛ መትረፉ ይቀራል?» አለቻት አሉ።

የንዋየ ቅድሳት ዝርፊያ፣ የአብያተ ክርስቲያናት መቃጠል የተለመደ ዜና ከሆነ ሰነበተ። እኛም መጀመሪያ አካባቢ እንደነግጥ «እግዚኦ» እንል እንዳልነበረ ጆሮአችን ጠገበውና 'የተለመደ ነው' እያልን ተውነው። እኒያን ከ30 ብር በላይ ደመወዝ የማያገኙ ፣ የዕለት ምግብ የማይሟላላቸውን እና የዓመት ልብስ የነሣናቸውን በየገዳማቱ የሚገኙ አበው የዕዳውም የአደራውም ብቸኛ ተሸካሚ አደረግናቸው።

በዓመት አንድ ጊዜ ብንጐበኛቸው እንኳን ለጊዜው በዓሉን አክብረን አለያም እንደ ቱሪስት ተንሸራሽረን መምጣት እንጂ « ገዳሙ ምን ችግር አለበት? ካህናቱስ ምን ይቸግራቸዋል? ከእኛስ ምን የሚጠበቅ አለ? » ፣ ብሎ የሚጠይቅ ባለመኖሩ 38 ሚሊዮን ምእመን ያላት ቤተክርስቲያን ገዳማቷና አድባራቷ በስግብግቦች ፣በሌቦችና በመናፍቃን ሲደፈሩ ማየት የዕለት ዜና ሆነ፡

«መከራ ሲመጣ አይነግርም ዐዋጅ
ሲገሠግስ አድሮ ቀን ይጥላል እንጅ» እንዳለ የሀገራችን ሰው።

ከመከራም መከራ፣ ከመቅሰፍትም መቅሰፍት አፄ ገብረ መስቀል ያሠሩት ፣ ቅዱስ ያሬድ የዘመረበት፣ ግራኝ እንኳን ሊያቃጥለው ያልቻለው የደብረ ዳሞ ዕቃ ቤት ባለፈው ዓመት ተቃጠለ። ብዙ ሺ ዘመን የቆዩ ቅርሶች ነደው አለቁ። የተቃጠለው የደብረዳሞ ዕቃ ቤት ብቻም አይደል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጭምር እንጂ! የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብቻም አይደል የኢትዮጵያም ታሪክ እንጂ! ምን የኢትዮጵያ ታሪክ ብቻ የአፍሪካ ክብር እንጂ! የዓለም ብርቅ ቅርስ ጭምር እንጂ።

እንግዲህ ይህን ስንሰማ ምን እንል ይሆን? ሰው መውለድ ይቻላል፣ ቤት መሥራትም ቀላል ነው። የደብረ ዳሞን ዕቃ ቤት ሕንፃ እንደገና ልንገነባው እንችል ይሆናል። የ2000 ዓመት ታሪክ መሥራት ግን አይቻልም። ጥንታውያኑን ቅርሶች መመለስ ግን ከዐቅማችን በላይ ነው። እንግዲህ የተረፈን ዕንባ ብቻ ነው።

ጠቅላይ ቤተክህነት ሁኔታውን የሚያጣራ ኰሚቴ አቋቁሞአል። በትክክልም ነገሩ ሊጣራ የሚገባው ጉዳይ ነው። በአካባቢው ያሉ ሰዎች በመብረቅ መቃጠሉን ይናገራሉ። በርግጥ በመብረቅ ተቃጥሎ ከሆነ በአካባቢው ሊገኙ የሚችሉ ምልክቶች አሉ። በወደቀበት መሬት ላይ የሚፈጥረው ለውጥም አለ። የተቃጠሉትና የተረፉት ዕቃዎችም መመርመር ይገባቸዋል። በአካባቢው መብረቅ ሊፈጥር የሚችል የአየር ጠባይ እንደነበረም ሊጣራ ይገባዋል። ጠቅላይ ቤተ ክህነትም ለዚህ ነው በአስቸኳይ እንዲጣራ ያዘዘው።

ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የማይተኙ ደም በለበሰ ዓይናቸው የሚያይዋት ፣ በታሪኳ ፣ በባሕሏ፣ በሥርዓቷ የሚቀኑባት አያሌ ናቸው። የእነርሱ እጅ ሊኖርበትም ይችላል። አለያም ደግሞ በስንፍና የተሠራ ስህተትም እንዲህ ያለውን አደጋ ያመጣል። እግዚአብሔር ተቆጥቶንም ይሆናል።

ግን እንዲሁ ተድበሰብሶ በአንድ ነገር ተመካኝቶ መቅረት የለበትም። ዛሬ ታሪካችን «ሲሞት» ካልነቃን፣ ዛሬ ደብረዳሞ ሲቃጠል ከንፈር መጥጠን ከተቀመጥን ነገ ላሊበላ፣አኩሱም፣ደብረ ሊባኖስ ወዘተ... ይደገማሉ።

ምእመናንም የአንገት በላይ ሐዘን፣ ራስ መነቅነቅ ብቻ ከሆነ መልሳችን፣ በአጥቢያችን ያሉትን ሀብቶቻችንን ነቅተን ካልጠበቅን ፣ የተቸገሩትን ካልረዳን ፣ የፈረሱትን ካልጠገንን፣ የወደቁትን ካላነሣን የታሪክ ባለቤቶች ፣ የአባቶቻችን ልጆች መሆናችን ያከትማል። እሳት ካንቀላፋ ገለባ ይጐበኘዋልና ስንፍናችን ለጠላቶቻችን በር እንዳይከፈት መጠንቀቅ ይገባል። ችግሩን በእንጭጩ እንቅጨው። «ይህች ባቄላ....»

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## ምን ለማለት ፈልጋችሁ እንደሆነ አብራሩልኝ

በሐመር 4ኛ ዓመት ቁጥር 1 እትም «ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ» ዓምድ ሥር በአንድ ጽዋ ማኅበር ያሉ ተባእትና አንስት መጋባት እንደሚችሉ ያወጣች ሁት ጽሑፍ የኢትዮጵያ ቤተክርቲያን ታሪክ በሚለው የአቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐ ፍ ላይ ከተገለጸው ጋር ይጋጫልና ምን ማለት ፈልጋችሁ እን ደሆነ አብራ ሩልኝ::

ታዮ ሺፈራው
/ጎባ ቅ/ገ/ስ/ት/ቤት
ተስፋዬ ሙሉጌታ /አ.አ/

<u>ከአዘጋጁ</u>

በቅድሚያ በ4ኛ ዓመት ቁ.1 መጽሔታችን ላይ የተገለጸው የጽዋ ማኅበርተኞችን አይመለከትም:: እንዲያውም እንደጥንቱ ሥርዓት ቢሆን ባልና ሚስት ካልሆኑ በስተቀር ወንድና ሴት የአንድ ጽዋ ማኅበር አባላት መሆን አይችሉም ነበር:: ቁጥራቸውም ከአሥራ ሁለት ወይም ሁለት ሁለት እየሆኑ ከ24 አይበልጥም:: ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ወንድና ሴት በአንድ ጽዋ ማኅበር መጠጣት ጀመሩ:: ቁጥራቸውም በአንዳንድ ቦታዎች ገደብ የሌለው ሆነ:: እንደዚህ ከሆነ ልክ አቡነ ጎርጎርዮስ እንደገለጹት እኅት ወንድም ይባባላሉ እንጂ መጋባት አይችሉም:: አስተውላችሁ እንደሆነ እኛ የገለጽነው ማኅበር ነዳያንን ለመርዳት፣ ገዳማትን ለመጎብኘት፣ ወዘተ በብዙ ወጣቶች የሚመሠረተው ዓይነት ማኅበርን ነው:: በዚህ ውስጥ አሁንም እንዳይጋቡ የሚከለክላቸው ሕግ የለም:: በተረፈ የአንድ ሰንበት ት/ቤት አባላትንም በተመለከተ ሰንበት ት/ቤቱ ራሱ በውስጠደንቡ እስካልከለከለ ድረስ መጋባት ይችላሉ:: ነገር ግን በድጋሚ መግለጽ የምንፈልገው የተሰበሰቡበት ዓላማ እንዳይደናቀፍ ወጣቶች በማስተዋል ቢጓዙ መልካም ነው:: በሕግ ደረጃ ግን ጋብቻን የሚከለክል ሕግ የለም::

✦✦✦

## ለአዛውንት አይጠቅምምን?

ልጆቻችን የሐመር አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? እኛ ዕድሜአችን ወደ ሰባና ሰማንያዎቹ እየገባ ያለን የመጽሔታችሁ አንባቢዎች ነን:: ይህንን ደብዳቤ የጻፈውን ልጅ ጨምሮም አሥር ልጆችን አፍርተናል:: እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውና በቆጠርናት ፊደል ሐመርን ስናነባት ብዙ ጠቃሚ ቁምነገሮች እንገበያለን ::
ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች መጽሔቱ የሚዘጋጀው እንደናንተ ላሉ አዛውንቶች ሳይሆን ለወጣቶች ብቻ ነው እያሉ እንዳናነብ ያሳንፉናል:: እኛ ግን የምናገኘውን ጥቅም ተረድተን እስካሁን ማንበባችንን የሙጥኝ ብለን ይዘነዋል:: መጽሔታችሁ ለአዛውንቶች አይጠቅምም እንዴ? የሚጠቅም ከሆነ ሌሎች የእኛ ዕድሜ እኩዮች እንዲያነቡ ገፋፏቸው:: በተጨማሪም በአብዛኛው ወጣቱን ብቻ ማስብትታችሁ አዛውንቶችንም የሚመለከቱ ጽሑፎችን ጨመርመር አድርጉልን::

አቶ እሸቱ ዘለቀ እና
ወ/ሮ አማረች በሀብቱ
/አርባ ምንጭ/

<u>ከአዘጋጁ</u>

አባታችን እና እናታችን በዚህ ዕድሜአችሁ መጽሔታችንን ስላነበባችሁልን በጣም ደስ ብሎናል:: እንዳላችሁት መጽሔቷን ያለ እድሜ ገደብ ሁሉም ቢያነባት ትምህርት ሊያገኝበት ይችላልና ምንም ብትባሉ ማንበባችሁን አትተው:: እስቲ እናንተም ተወያዩና የወላጅ ምክራችሁን ለግሱን:: በጸሎታች ሁም አስቡን::

✦✦✦

## ለምን ከአዋጅ ጾም አልተመደበም?

በቅድሚያ መንፈሳዊ ሰላም ታዬ ይድረሳችሁ እያልኩ ተሳትፎዬን በጥያቄ እጀምራለሁ:: የጽጌ ጾም ለምን ከሰባቱ አጽዋማት ውስጥ አይመደብም?

<u>ከአዘጋጁ</u>

ወርኃ ጽጌ ከሰባቱ አጽዋማት ጋር ተቆጥሮ ስምንተኛ ያልሆነበት ምክንያት በቤተክርስቲያን ሥርዓት በአዋጅ እንዲጾም ስላልተደነገገ ነው:: በመሆኑም ወርኃ ጽጌ በፈቃድ የሚጾም ጾም እንጂ የአዋጅ ጾም አይደለም:: ከአዋጅ አጽዋማት ባይቆጠርም በፈቃድ /በግል/ መጾም ይቻላል:: አንዳንዶች እንደሚያደርጉት የማይጾሙትን ሰዎች ሥርዓት አንጻ ፈረሱ ቆጥሮ ኃጢአተኛ አድርጎ መመልከ ትና መንቀፍ ግን ትክክል አይደለም::

✦✦✦

## አስወግዛችኋለሁ

ሐመሮች÷ ከዚህ በፊት ሁለት መጣጥፎች ልኬላችሁ የውኃ ሽታ ቢሆኑም ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥምና እንደገና ጻፍኩላችሁ:: ብቻ እንደልማዳችሁ የቅርጫታችሁ ሲሳይ ታደርጓትና ዋ! አስወግዛችኋለሁ:: ደንበኝነቴንም እፍቃለሁ:: ተቀይመህ ኖሯል ሰላምታውን የነፈግከን ? እንዳትሉኝ ፡ ሰላምታዬ ባላችሁበት ይድረሳችሁ:: ፈቃዳችሁ ከሆነ ለወደፊቱ የተለያዩ ጽሑፎችን ልልክላችሁ ቃል እገባለሁ:: አንድ ነገር ጠቁሜአችሁ ልሰናበት:: በጋሞጎፋ ክፍለሀገር በምዕራብ ዓባያ ወረዳ በብርብር ከተማ መሥዋዕተ ኦሪት የተሰዋባት በእመቤታችን ስም የተሠራች ገዳም ስለምትገኝ እባካችሁ ጉብኟትና ታሪኳን ለሕዝብ አሳውቁ::

ዲ. ኃ/መለኮት ተረፈ
/ጨንቻ/

<u>ከአዘጋጁ</u>

ወንድማችን እርስዎም ተስፋ ቆርጠው እኛም ይህን ያህል አስቀይመን ዎት ውግዘት ደረጃ እንደራረስም:: የፈሯት ቅርጫት ቀርቶ ስንጥር ቀርከሃ የለችንምና ቃልዎን አክብረው ይጻፉልን :: ከሚደርሱን ጽሑፎች መካከል ለአንባቢያን ይሆናሉ የምንላቸውን እየመረጥንና ወቅቱን እየጠበቅን ስለምናወጣ ያንን እያሰቡ እንደሚጽፉልን ተስፋ እናደርጋለን::

✦✦✦

## ልቦለድ ለማቅረብ ፍላጎት አለኝ

ሐመሮች÷ እግዚአብሔር በአገልግሎታችሁ ያጽናችሁ እያልኩ ለዝግጅት ክፍሉ ልቦለድ ለማቅረብ ፍላጎት አለኝ:: እናም እንዳቀርብ የምትፈቅዱልኝ ከሆነ በአስቸኳይ ግለጹልኝና ልቀጥል::

ስብለ ወንጌል ሞሲሳ
/አ.አ/

<u>ከአዘጋጁ</u>

እኅታችን ሁሉም ሰው እንደየተሰጥኦው መሳተፍ ይችላልና ይቀጥሉ::

## ውይይቶችን እና ቃለመጠይቆችንም አቅርቡልን

ውድ አዘጋጆች የመጽሔታችሁ የመውጫ ጊዜ በኅትመት፣ በሥርጭት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ሊሆን ይችላል እየዘገየብን ተቸግረናል:: ወደፊት በርትታችሁ እንደም ታስተካክሉት ስናስብ ደግሞ እንጽናናለን:: በተጨማሪም በጽሑፎቻችሁ ወጣቱን /ጀማሪውን/ በሚገባ እንደዳሰሳችሁት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እዲያካትትላችሁ ከሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ጋር ውይይቶችን እና ቃለ መጠይቆችን ብታቀርቡልን የበለጠ እንደሰታለን:: በተረፈ ጥያቄዎቼን እና ግጥሜን እንደምታስተናግዱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ::

ዲ.አሸናፊ ገ/ማርያም/ወልቂጤ/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከአዘጋጁ

አስተያየትዎን ተቀብለናል:: እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተቻለንን እናደርጋለን:: ግጥምዎ ተራውን ጠብቆ ይወጣል:: የጥያቄዎችዎንም መልስ በአድራሻዎ ይጠብቁ::

✦✦✦

## ፍራፍሬ ይዞ መግባት ይፈቀዳልን?

በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት የሚበላ ነገር ቤተክርስቲያን ውስጥ ይዞ አይገባም:: ነገር ግን ሚያዝያ 5 ቀን 1988 ዓ.ም የትንሣኤ ዋዜማ ዕለት መሆኑ ነው፣ በአጋጣሚ ከምኖርበት አካባቢ ራቅ ወደአለ ቦታ በዓሉን ለማክበር ስሄድ የገጠመኝ ግን የተለየ ሆነብኝ:: ይኸውም ምእመናን ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ኮክ ወዘተ... ቤተክርስቲያን ውስጥ ይዘው ገብተው ሥርዓተ ጸሎቱ እንዳበቃ ወጥተው ሲበሉ ተመለከትኩ:: ፍራፍሬ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይዞ መግባት ይፈቀዳልን?

ክብካብ ወንድወሰን
/መካነ ሰላም/

ከአዘጋጁ

በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት የሚበላ ነገር ቤተክርስቲያን ወስጥ አይገባም:: በዚያ ቅዱስ ሥፍራ ልንመገብ የሚገባን የጌታችንን ሥጋ እና ደም ነው:: ፍራፍሬም ከሚበሉ ነገሮች አንዱ ስለሆነ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይዞ መግባት አይፈቀድም:: እርስዎ እንዲህ ያለ ድርጊት ሲፈፀም ያዩበት አካባቢ በስህተት ሊሆን ይችላልና በአጥቢያው ለሚገኙ ካህናት በመጠቆም እንዲተባበሩን በዚሁ አጋጣሚ እናሳስባለን::

✦✦✦

## መንታ መውለድ ኃጢአት ነውን?

ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች ብዙ እናቶች በአካባቢአቸው ወይም በራሳቸው መንታ መውለድ ሲገጥማቸው ሰማዩ የተናደባቸው ይመስል እጅግ ሲማረሩና እግዚአብሔር ከኃጢአታቸው ብዛት የተነሣ ወይም የአያት የቅድመ አያቶቻቸውን ኃጢአት ቆጥሮ እንዳመጣባቸው በማሰብ ሲያጉረመርሙና ሲያዝኑ አጋጥሞኛልና ለመሆኑ መንታ መውለድ ኃጢአት ነው?

አበበ ይልማ
/ከመተሐራ/

ከአዘጋጁ

መንታ መውለድ ጸጋ እንጂ የኃጢአት ምልክትና በኃጢአት ምክንያት የሚመጣ ቁጣ አይደለም:: እናታችን ርብቃ መንታ ወልዳለችና :: ዘፍ25÷21 –26:: የሚያሳድጉበት አቅም ካላቸውና በሰላም ከተገላገሉ እንኳን መንታ ከዚያም በላይ ቢወልዱ ሊደሰቱ ይገባል እንጂ መመረርን ምን አመጣው

✦✦✦

## መስፈርቱ ምንድን ነው?

ሐመሮች መንፈሳዊ ትምህርት ለመከታተል ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ:: ስለሆነም የቤተክርስቲያናችን መንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ ለመግባት መመዘኛው ወይም መስፈርቱ ምንድን ነው? ጠይቃችሁ ግለጹልኝ::

እሸቱ ኃ/ማርያም
/አ.አ/

ከአዘጋጁ

በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብቶ ለመማር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይና ሥልጣነ ክህነት ያለው፣/ቢያንስ ዲቁና/ በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ሁለት ነጥብ እና ከዚያም በላይ ኖሮት በእንግሊዘኛ " C " እና ከዚያም በላይ ያለው መሆን ይኖርበታል:: እንዲሁም ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የድጋፍ ደብዳቤ ማጻፍ አለበት::

## ከሴቶችስ የመጀመሪያዋ ማን ናት?

የመጀመሪያዎቹ የወንድ መነኮሳት አባ እንጦንስና አባ መቃርስ እንደሆኑ ይነገራል:: ከሴቶችስ የመጀመሪያዋ መነኩሲት ማን ይባላሉ? የየትስ ሀገር ተወላጅ ናቸው?

መ/ም መስፍን አዱኛ
/ከመካከለኛው አዋሽ/

ከአዘጋጁ

ከሴቶች ምንኩስናን የጀመረችና የሴት ገዳም በወንድሟ አማካኝነት እንዲሠራ ያደረገች የአባ ጳኩሚስ እኅት ማርያም ስትሆን ትውልዷም ግብጽ ነው:: /ሉሌ መልአኩ፣ አጭር የቤተክርስቲያን ታሪክ/

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው የመጽሔታችን ተሳታፊዎች የላካችሁልን የእንኳን አደረሳችሁ ካርዶች ደርሰውናል ፣ጽሑፎቻችሁ ለአንባቢያን የሚመጥኑ ከሆኑ ወቅቱን እየጠበቁ ይወጣሉ::ጥያቄዎቻችሁ በየተራ በመጽሔቱ እና በግል አድራሻችሁ /ከገለጻችሁልን/ ይመለሳሉ:: እስከዛሬ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይመለሱላችሁ ለቀሩት በማዘግየታችን ይቅርታ አድርጉልን:: ከቦታ ጥበት የተነሣ መልእክቶቻችሁ መድረሳቸውን ያላሳወቅናችሁ ደግሞ በሚቀጥለው መጽሔት ስለም ንገልጽ በትዕግሥት ጠብቁን:: በተሳትፎአችሁ አትለዩን::

ዲ.ኃ/ማርያም አጽናፉ እና ተማሪ ዓለማየሁ ደበላ /ሀገረ ማርያም/፣ ዘውዱ አላምረው /ድኅጽዮን/፣ዲ.አክሊሉ ሞገስ /አ.አ/ ፣ጌቱ ፈቃዱ /ሮቤ መ/ማ.ተቋም/፣ሲሳይ ሺራ እና ደርቤ እርገጤ /መተሐራ/፣ ሐዲስ አረጋይ/ሻሸመኔ/፣ ተማሪ ካሡች ረጋሣ /ጎባ/ ፣ግርማ ከበደ /አ.አ/፣ ሺመልስ ተስፋዬ /ቴፒ/፣ ኃይለ መስቀል /ጐሬ/ ፣ዘሪሁን አሰፋ /ሊሙገነት/ ተስፋዬ ወ/ሚካኤል /ቦንጋ/ ፣ ተክለወልድ ነራ /ሻኪሶ/፣ ተካልኝ ልባይ /አ.አ/፣ አሥራተ ኢየሱስ /አዲስ አበባ/ ፣ ወርቁ ዘውዴ /ጐደሬ-ጋምቤላ/፣ ዮናስ ፈጠነ / ደብረ ዘይት/፣ ገብርየስ ገቢቶ /ቦንጋ/፣ ቢራቱ ገለታ /ቂልጡ/፣ አቶ ያረጋል መኩሪያቸው /ቻግኒ/፣ ወንድወሰን ተክለማርያም /ባሌ እርሻ ልማት/ ፣ ተማሪ ኀብረት ለማ /ወላይታ ሶዶ/፣ ያሬድ ሠይፉ ወልዴ /ዋሽንግተን ዲሲ ቅ/ማ/ቤ/ክ/፣ ማርታ ሺፈራው /አ.አ/፣ ዮናስ ተሰፋዬ /ደሴ/፣ መ/ር አዲስ ይታይህ /ማንኩሣ/፣ታደለ ምርከና /አምቦ-ሜጢ/፣ ረጋ ድንበሩ /ቡሬ/፣ አንዱዓለም ኃ/ማርያም /አዲስ አበባ/፣ ተማሪ መስፍን ግርማ /አ.አ.ዩ/፣ መርዕድ ካሣዬ /አ.አ/፣ ሙሉ ገብሬ /ቢሲዲ/፣ አቶ ጥላሁን አዱኛ /እንድብር/ ፣ክፍለ ዮሐንስ ይትባረክ /አዲስ አበባ/፣ መልአከ ምሕረት /ደብረ ማርቆስ/፣ መ/ር ጌትዬ ብርቅነህ /ደብረ ብርሃን/፣ ሰውነት ታዬ /ናዝሬት/፣ ዲ.አዲሱ ከተማ /ፍቼ/፣ ትዕዛዙ ኃ/ማርያም /ጋዌ/፣ ሺፈራው ደርቤ /ሻኪሶ/፣ ዲ.ወንድሜነህ ተስፋዬ /ቦንጋ/፣ ሰሎሞን እንባ /ነጆ/፣ ተመስገን አየለ /ኮፈሌ/፣ እጬመ/ር ዳዊት ተፈራ /ነቀምቴ/፣ ተማሪ ፈረደ አልማው /ቡሬ/፣ መ/ር በላይ ተባባል /ደምቢ/፣ ያዕቆብ ዘደብረ ብሥራት፣ መ/ር ተስፋዬ ደምሴ/ንፋስ መውጫ/፣ ኃይለ ሚካኤል በፈቃዱ /ጅማ/ ሰሎሞን አበበ /አርጆ/፣ አብነት አበበ /ቦዲቲ/፣ ክንፈ ማርያም ኃ/ጊዮርጊስ /ነፋስ መውጫ/፣ ቴዎድሮስ ወ/ማርያም /አዲስ አበባ/፣ አስግድ ደምሴ /ደብረ ዘይት/፣ ታሪኩ አሰፋ /ባሌ-ሮቤ/፣ ሀብተማርያም ዓለምነው /ጋይንት/፣ ማኅተም አያሌው /አዴት/፣ ከአቡሐራ ድንግል የመዘምራን ማኅበር /ደብረ ዘይት/፣ ኃይሉ ጸጋዬ /ወልድያ/፣ ወስናችው ካሣ /አዋሳ/፣ ትዝታ ፍራንሲዝ /ፍቼ/፣ ዮዲት ገ/እግዚአብሔር /አዲስ አበባ/፣ ዘላለም ማሞ /አ.አ.ዩ/ ፣ ደረጀ አየለ /ጅንካ/ ፣ ኤልያስ ደስታ /አዲስ አበባ/::

✦✦✦



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከሰሞኑ በረከት

## ልጄን ከግብፅ ጠራሁት

ከ ጎርጎርዮስ ደጀኔ

ግብፅ አበ ብዙኃን አብርሃም በራብ ምክንያት የተሰደደባት፣ ዮሴፍ ባሪያ ሆኖ የተሸጠባት፣ እሥራኤል ባሮች ሆነው ለአራት መቶ ዓመታት የተገዙባት አገር ናት:: ዘፍ.12÷10፣ 37÷36፣ የሐዋ.7÷6:: እሥራኤል ዘሥጋ በግብፅ መከራ በመቀበላቸው በጊዜው አገሪቱ የሲኦል ምሳሌ ተብላ ለች:: ቀዳማዊ አዳም ከገነት እንደተ ሰደደ ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስ ቶስም ከኢየሩሳሌም ወደ ግብፅ በመሰ ደድ የስደትን ጽዋ ቀምሷል:: ስደተ ኞችን ወደ ቀደመ ክብራቸው ለመመ ለስ የመጣ አምላክ በስደቱ ሞትን አሳደደው:: ከዚህም ሌላ ስደትን ለስማዕታት ባረከላቸው :: ቀደሰላቸ ውም:: ሰማዕትነት በእሳት መቃጠል በስለት መቆረጥ ብቻ ሳይሆን አገር ንም ጥሎ መሰደድ ሰማዕትነት ነውና:: ስለ ጽድቅ የሚሰድዱ ብፁዓን ናቸው:: እንዳለ:: ማቴ 5÷10::

ለጌታችን መሰደድ ምክንያት የሆነው ንጉሡ ሄሮድስ ነበረ:: ይህ ንጉሥ በቅንዓት ተይዞ ሕፃኑን ለመግ ደል በፈለገ ጊዜ ምሥ ጢሩን የእግ ዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ ስለገለጠ በት አሳቡ ሁሉ ከንቱ ሆኖ ቀርቷል::

ሰብአ ሰገል ኮከቡን በምሥራቅ አይተው በኮከቡ እየተመሩ በመምጣት ሰግደው ወርቅ፣ዕጣን፣ከርቤም ገብረው ሄሮድስ በተንኰል እንደ ነገራቸው ሳይሆን በሕልም ከመልአኩ እንደተረ ዱት በሌላ ጐዳና፣ በሌላ ኃይለቃል፣ በሌላ ሃይማኖት ተመል ሰዋል:: በሌላ ጐዳና ሁለት ዓመት የተጓዙትን በአርባ ቀን፣ በሌላ ኃይለቃል «ወዴት ነው?» እያሉ የመጡትን «አገኘነው» ብለው ፣በሌላ ሃይማኖት«ንጉሠ አይሁድ ነው» ያሉትን «አምላክ ነው» እያሉ ተመልሰ ዋል::

ሰብአ ሰገል ከሄዱ በኋላ ከእግ ዚአብሔር የታዘዘው መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ «ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገ ድለው ይፈልጋልና ሕፃኑን እና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ:: እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ::» ብሎታል:: ማቴ.2÷13:: መልአኩ ሕፃኑንና እናቱን ማለቱ እናትና ልጅ የማይነጣጠሉ በመ ሆናቸው ነበር:: ይህም የጌታን ቸርነትና የእመቤታ ችንን አማላጅነት አምነው ዓለምን ለሚንቁ ቅዱሳን አብነት ነው::

መልአኩ የስደቱን ነገር ሰብአ ሰገል ከመሄዳቸው በፊት ያልተ ናገረው ስለ ሁለት ነገር ነው:: አንደኛው ስደቱን አይተው አምላክነ ቱን እንዳይጠራጠሩ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የጌታ ስደቱ ወደ ግብፅ እንጂ ወደ ባቢሎን ባለመሆኑ እኛ ይዘነው እንሄድ እንዳይሉ ነው::

የእመቤታችን ስደት ወደ ኢትዮጵያም ጭምር ነበር:: ይህንንም ትንቢት አስቀድሞ የተናገረው ነቢዩ ዕንባቆም ነው:: «እግዚአብሔር ከቴማን ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል:: ክብሩ ሰማያትን ከድኗል፣ ምስጋናውም ምድርን ሞልቷል:: ፀዳሉ እንደብርሃን ነው፤ ጨረር ከእጁ ወጥቶአል፤ ኃይሉም በዚያ ተሰውሮአል....መንገዱም ከዘላለም ነው:: የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ::»ብሏል::ዕንባ.3÷3-7:: በትንቢቱ መሠረት የፋራን ተራራ የተባለችው እመቤታችን ስትሆን ከፋራን ተራራ ይመጣል የተባለው ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ድንኳን ደግሞ የስደተ ኞች ማረፊያ ነው:: በመሆኑም «የኢት ዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ::» የሚለው ዐረፍተ ነገር የእመቤታችን ስደት ወደ ኢትዮጵያም እንደሆነ የሚያመለክት ነው::

በራእየ ዮሐንስ በምዕ.12÷1-17 የተጻፈውም የእመቤታችንን ስደት የሚናገር ነው:: ትርጓሜውም የፀነሰች ሴት የተባለችው ያለ ዘርዐ ብእሲ በመንፈስ ቅዱስ ግብር አምላክን በድንግልና የፀነሰች እመቤታችን ናት:: ዮሐንስ በራእዩ «በምጥ ተይዛ ልትወ ልድ ጮኸች::» ማለቱ በሌሎች ሴቶች ልማድ መናገሩ ነው እንጂ በእመቤታችን ይህ ሁሉ የለባትም:: ምክንያቱም በማኅፀኗ የተፀነሰው አም ላክ አስጨንቆ በምጥ የሚወለድ ሳይሆን የድንግልና በሯን ሳይከፍት እንደገባ ሳይከፍት የሚወጣ ነውና:: ሕዝ.44÷1-44፣ኢሳ.7÷14:: ደግሞም ምጥ በእርግማን ምክንያት የመጣ ነው:: ሔዋን «ብፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፣ በጭንቅ ትወልጃለሽ፣ » ዘፍ.3÷16 ተብላ ነበር:: እመቤታችን ግን የአዳም ኃጢአት በዘር ያልተላ ለፈባት ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ንፃ የሆነች ንጽሕት ቅድስት ናት:: ከእግዚአብሔር የተላከ ቅዱስ ገብርኤል እና መንፈስ ቅዱስ ያደረባት ቅድስት ኤልሳቤጥ « አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ::»ብለው በአንድ ቃል ያመሰገኗት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጭ ነሽ ሲሏት ነው::

በሌላ በኩል ቅዱስ ዮሐንስ 'ምጥ' ያለው ጌታን በመውለዷ ምክን ያት በአይሁድ የዘወትር ጠላትነት እና በስደት የሚደርስባትን መከራ ነው:: ጽኑ መከራ ምጥ ይባላል:: «እነዚህ ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው» እንዳለ:: ማቴ.24÷8 ፣ኢሳ 26÷16::

«በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ» የተባለው ዘንዶ በሄሮድስ ያደ ረው ሰይጣን ነው:: እርስዋም አሕዛ ብን ሁሉ በተወደደ በጽኑ ሥልጣኑ የሚጠብቃቸው ኃያል ወልድን ወለደች ማለት ነው::

«ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ::» ማለቱ በተዋሕዶ ፍጹም ሰው የሆነው አምላክ አማኑኤል እንደ ሰውነቱ ሲሰደድ እንደ አምላክ ነቱ በአብ ቀኝ እንዳለ መናገር ነው:: ሴቲቱም /እመቤታችንም/ ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን /ሦስት ዓመት ከመን ፈቅ/ በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብ ሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ሥፍራ ወደ በረሀ /ወደ ግብፅ / ሸሸች::

ዘንዶውም /በሄሮድስ ያደረው ዲያብሎስ/ ወደ ምድር እንደተጣለ /ከሥልጣኑ እንደተሻረ/ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት /እመቤታ ችንን/ በሄሮድስ አድሮ አሳደዳት:: ከዕባቡም ፊት /ከሄሮድስ ፊት/ ርቃ አንድ ዘመን /አንድ ዓመት/ ዘመናትም



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

/ሁለት ዓመታት/ የዘመንም እኩሌታ /ስድስት ወር/ በጠቅላላው ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ወደምትመገብበት /ወደምት ጠበቅበት / ወደ ሥፍራዋ ወደ በረሀ /ወደ ግብፅ -- ወደ ደብረ ቁስቋም» እንድትበር ለሴቲቱ /ለእመቤታችን/ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት ይላል፡፡ ሁለት ክንፎች የተባሉት ንጽሐ ሥጋ እና ንጽሐ ነፍስ ናቸው፡፡ ይህም እመቤታችን በንጽሐ ሥጋ በንጽሐ ነፍስ የጸናች መሆኗን የሚሳይ ነው፡፡

እመቤታችን በስደቷ ጊዜ ብዙ መከራ ተቀብላለች፡፡ የፀሐዩ ዋዕይ፣ የሌሊቱ ቁር፣ ረኃቡና ጥሙ ቀላል አልነበረም፡፡ የቤተክርስቲያን አባት አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ድርሰቱ ላይ «ድንግል ሆይ ርኅም በሆነ በሄሮድስ ዘመን ከእርሱ ጋር ካገር ወደ አገር ስትሸሽ ካንቺ ጋር መሰደዱን አሳስቢ፡፡ ድንግል ሆይ ከዓይኖችሽ በፈሰሰው እና በተወደደ ልጅሽ ፊት የወረደውን መሪር ዕንባ አሳስቢ፡፡ ድንግል ሆይ ረኃቡንና ጥሙን፣ ችግሩ ንና ኃዘኑን ከርሱ ጋር የደረሰብሽንም ጭንቅ ሁሉ አሳስቢ፡፡» ያለው ለዚህ ነው፡፡/ቁጥር 167/

ሳሌም ለመሄድ ፈራ፡፡ አንድም የይሁዳ ሰዎች ልጆቻችን ያለቁ በእናንተ ምክን ያት ነው፡፡ ብለው እንዳይጣሉት ነው፡፡ ምክንያቱም በቤተልሔምና በአውራጃዋ የነበሩ ሁለት ዓመት የሆናቸው ከዚያም የሚያንሱት ሕፃናት ከመካከላቸው ኢየሱስ ክርስቶስ አይጠፋም በሚል ሰበብ በሄሮድስ ሠራዊት ተገድለው ነበርና፡፡

በመጨረሻም ዮሴፍ በሕልም ተረድቶ ወደ ገሊላ አገር ሄደ፡፡ በነቢ ያት «ናዝራዊ ይባላል» የተባለው ቃል ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ፡፡

በቤተክርስቲያናችንይህ የስደት ጊዜ ከመስከረም 26 - ኅዳር 6 ድረስ በልዩ ሁኔታ በማኅሌት ይታሰባል፡፡

ይህ ወቅት የአበባ /የጽጌያት /ጊዜ በመሆኑ ወርኃ ጽጌ ይባላል፡፡ ከዚህ የተነሣ የሚቆመው ማኅሌት ማኅሌተ ጽጌ ይባላል፡፡ በወርኃ ጽጌ በተለይም ካህናት በየሣምንቱ ቅዳሜ ማታ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ እስኪነጋ ድረስ ያለምንም ዕረፍት ማኅሌተ ጽጌን ቆመው ያድራሉ፡፡



ጻድቁ ዮሴፍ እመቤታችንን እና ጌታን ይዞ በግብፅና በኢትዮጵያ እየተዘዋወረ ሳለ ፣ከእግዚአብሔር የታዘ ዘው መልእክ «ተንሥእ ንሣእ ሕፃነ ወእሙ ወሑር ውስተ ምድረ እሥራኤል፡፡ ተነሥተህ ብላቴናውንና እናቱን ይዘህ ወደ ምድረ እሥራኤል ተመለስ፣ የዚህን ብላቴና ነፍስ ለጥፋት የሚሿት ሰዎች ጠፍተዋልና» አለው፡፡ የእመቤታችን ጠባቂ ዮሴፍም ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ እሥራኤል ተመለሰ፡፡ እንደተመለሰም በአባቱ በሄሮድስ ፈንታ ይሁዳን ለመግዛት አርኬላኦስ እንደነገሠ ሰምቶ የክፉ ልጅ ክፉ እንዲሉ እርሱስ ያባቱን ይተዋልን? ብሎ ወደ ኢየሩ

ማኅሌቱም እጅግ ጣፋጭ በመሆኑ ወርኃ ጽጌን የማይናፍቅ ካህን የለም፡፡ የድርሰቱ ምሥጢር እና የዜማው ስልት ፈጽሞ ይለውጣቸዋል፡፡ በተመስ ጦም በመንፈስ ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ፡፡ በእመቤታችን ፍቅር እንባቸው ይፈሳል፣ ወዛቸው ይንጠፈጠፋል ፡፡ የዜማውን ስልት ጠብቀው ሲያዜሙ፣ ጸናጽሉን ሲጸነጽሉ፣ ከበሮውን ሲመቱ፣ መቋሚያውን በትከሻቸው አድርገው ሲያሸበሽቡ፣ ወረቡን ሲወርቡ የት እንዳሉ እንኳን አያውቁትም፡፡ በዚህ ጊዜ አተኩሮ ለተመለከታቸው ሰማያው ያን መላእክትን እንጂ ምድራውያን ሰዎችን አይመስሉም፡፡ የዚህ በረከት

ተሳታፊዎች ለመሆንም አብረው ከካህናቱ ጋር የሚያድሩ ምእመናን አያሌ ናቸው፡፡

የባሕርይ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶ ስን «ልጄ» ብሎ ከግብፅ የጠራው አምላክ ዛሬም እኛን የጸጋ ልጆቹን በቃሉ ከመጥራት ያቋረጠበት ጊዜ የለም፡፡ በመሆኑም ጥሪውን አድምጠን ከግብፅ /ከዓለም/ እንውጣ፣ ወደ ኢየሩ ሳሌምም እንመለስ ፡፡ ምክንያቱም ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን እንደወጣን የቀረን ብዙዎች ነንና፡፡ ጥሪው ሰማያዊ በመሆኑ በእምነት ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን ልንገሰግስ ይገባናል፡፡ ስለዚህ ከሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከተ፡፡ ተብለናል፡፡ ዕብ.3፥1፡፡

ዛሬ እርሱ «ልጆቼ» እያለ በፍቅር ሲጠራን ዝም ካልነው ታግሦ ታግሦ እርሱም በተራው ዝም የሚልበት ፣ ጥሪያችንን የማይሰማበት ጊዜ ይመጣል፡፡ «በጠራሁ ጊዜ እምቢ ስላላችሁ፣እጄን በዘረጋሁ ጊዜ ማንም ስላላስተዋለ፣ ምክሬን ሁሉ ግን ቸል ስላላችሁ፣ ዘለፋዬንም ስላልፈቀዳችሁ ፤ እኔም ስለዚህ በጥፋታችሁ እስቃለሁ፤ ጥፋታችሁም በመጣ ጊዜ አላግጥባች ኋለሁ፤ ድንጋጤ እንደ ጉርፍ በደረሰ ባችሁ ጊዜ፣ ጥፋታችሁም እንደ ዐውሎ ነፋስ በመጣ ጊዜ፣ የዛን ጊዜ ትጠ ሩኛላችሁ፤ እኔ ግን አልመልስላች ሁም፡፡» ምሳ.1፥24 ብሏል፡፡

እንግዲህ የአባታችንን የእግ ዚአብሔርን ጥሪ ሰምተን ወደ እናት ቤተክርስቲያን የምንገሰግስ ልጆች ያደርገን ዘንድ የእግዚአብሔር ቸር ነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅ ነት አይለየን ፡፡ አሜን ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

ለመጽሔታችን የክርስትና ማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ ጥያቄ የምትልኩ አንባብያን

- ዕድሜ
- ፆታ
- የሥራ ሁኔታ
- የጋብቻ ሁኔታ/ያገባ/ያላገባ/
- የቤተሰብ ሁኔታ /የተለያዩ በአንድ ላይ የሚኖሩ/
- የክህነት ደረጃ /ካለ/
- የትምህርት ደረጃ
- በቤተክርስቲያንአገልግሎት ያላችሁ ቦታ /በ ሰ/ት/ቤት፣በሰበካ ጉባኤ....../ወዘተ አሟልታችሁ ብትልኩልን ለመልሱ ያመቹናል፡፡

የዝግጅት ክፍሉ



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

## የእግዚአብሔር ሕግ

በዲ.እሸቱ ታደሰ /ካለፈው የቀጠለ/

ባለፈው እትማችን የአምልኮ ዓይነቶችን በመዘርዘር አራቱን በየተራ ተመልክትን ነበር:: ዛሬ ደግሞ ከአምስተኛው እንጀምራለን ::

### 5 ዓለምንና የዓለምን ፍላጎት ማምለክ

ዓለም ሌላኛዋ ጣዖት ናት:: ከዓለም ጋር በፍቅር የተሳሰረ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ለእርሱም ያለውን ታዛዥነት እና እምነት ሁሉ ይረሳል፣ ይተዋልም:: ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ « ዓለምን መውደድ ለእግ ዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን ? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ኾኗል::» በማለት ይህንን ገልጦታል:: ያዕ.4፥4:: ፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐን ስም በበኩሉ ይህን በመጀመሪያው መል እክቱ አጉልቶታል:: « ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ :: በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት፣ ስለገንዘብም መመ ካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም:: ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ :: የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል:: » 1ዮሐ.2፥15-17::

አንድ ጥያቄ ለራሳችን ኅሊና እናቅርብ:: የምናመልከው እግዚአብሔርን ወይስ ዓለምንና ፍላጎቷን? በእውነት እግዚአብሔርን የምናመልክ ከሆነ ዓለምን ድል መንሣት ይገባናል:: ፈቃዷም በእኛ ላይ መሠልጠን የለበትም:: ይህን አስመልክቶ ቅዱስ ዮሐንስ «ከእግዚአብሔር የተወለደው ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ፣ ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው:: » እንዳለ:: 1ዮሐ.5፥4:: የዓለም ፍላጎት ባሸነፈን ጊዜ ግን እምነታችን ከውስጣችን ፈጽሞ ይጠፋል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ከባድ ፈተና «ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወድዶ ትቶተኛልና » 2ኛ ጢሞ.4፥10 በማለት ተናግሮአል:: የሥጋ ፍትወታት ሰዎችን ረግጠው የሚገዙ አማልክት ናቸው::ለምኞታቸው የሚገዙ ሰዎችም እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው ፣በፍጹም ሐሳባቸው እና በፍጹም ኃይላቸው ያመልካሉ ማለት ያስቸግራል::

አንዳንድ ሰዎች የአካላቸውን ውበት ያመልካሉ:: ሁልጊዜም ስለ ውበታቸው ቢናገሩ ይወዳሉ:: የተፈጠሩበት ሌላ ዓላማ የሌለ ይመስል ለውበታቸው ብቻ ሲጨነቁ ይታያሉ:: እነዚህ ሰዎች «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» የሚለውን ቃል አፍርሰዋል:: «ከላይ በሰማይ ካለው፣ በታችም በምድር ካለው ከምድር በታች በውኃ ካለው ነገር የማንኛውንም ምሳሌ የተቀረፀውንም ምስል ለአንተ አታድርግ» የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል መሻራቸው አይታወቃቸውም:: ለእነርሱ የሚታያቸው ድንጋይ ጠርበው እንጨት አለዝበው ፣ አለማምለካቸው ብቻ ነው:: ነገር ግን ማንም ቢሆን እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክና ልቡናውንም ለእግዚአብሔር ብቻ አሳልፎ መስጠት እንጂ ራሱን እንደ ጣዖት ማምለክ የለበትም::

ሌሎች ደግሞ ትኩረታቸው ሁሉ መብል እና መጠጥ ላይ ብቻ ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለእነርሱ «ሆዳቸው አምላካቸው ነው፣ ክብራቸው በነውራቸው ነው ፣ ሐሳባቸው ምድራዊ ነው::» ፊልጵ.3፥19:: በማለት አስተምሯል:: ከዚህም በላይ እነርሱ የመስቀሉ ጠላቶች መሆናቸውንና ስለዚህም የሚያለቅስላቸው መሆኑን ጨምሮ ተናግሯል:: በእርግጥ አንድ መለኪያ አረቄ አምላካቸው የሆነ ፣ፈቃዳቸውም ሁሉ ወደመብልና መጠጥ ያዘነበለ ብዙ ሰዎች አሉ:: እሥራኤላውያንስ በአንድ ወቅት ስለሥጋ፣ ዓሣ፣ ዱባ፣ በጢኽ ፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ነጭ ሽንኩርት አልቅሰው አልነበረምን? ዘኁ.11፥4-5:: ኤሣውስ ብኩርናውን ከነበረከቱ ለምስር ወጥ አልሸጠምን? ዘፍ.25፥29-34:: አዳምና ሔዋንስ ለመብላት ያማረች ፣ ለዓይን የምታስጎመጅ ከሆነችው ዛፍ ፍሬ በመብላት በሰው ሁሉ ላይ ርኩሰትንና ሞትን አምጥተው የለምን? ዘፍ.3፥6::

ቅዱሳን አበው ለጣዖት ከመንበርከክ ይልቅ ሰማዕትነትን ይመርጡ እንደነበር ገድላቸው ይነግረናል:: የዘመኑ ትውልድ ደግሞ በተቃራኒው በየቀኑ ለጣዖት መሥዋዕት ሲያሳርግ ይውላል:: የዘመኑ ሰው በየቀኑ የሚሠዋላቸው እነዚህ ጣዖታትም ገደብ የሌላቸው የሥጋው ፍላጎቶች ፣የዓይኑ አምሮቶች ናቸው ::

ሥልጣንን፣ ማዕረግን፣ ክብርን፣ የተለያዩ ንብረቶችን እንደ አምላክ የሚ መካባቸው እና የሚያመልካቸው ሰው ለእነዚህ ፍላጎቶቹ ሲል ፈጣሪው እግዚአብሔርንና ኅሊናውን ይሸጣል:: «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ » የሚለውን የእግዚአብ ሔርን ትእዛዝ ወደ ጎን በመተውና በመዘንጋት ፍላጎቱን ለመፈጸም አስፈላጊ ነው ያለውን መሥዋዕትነት ሁሉ ከመክፈል ወደኋላ አይመለስም:: ለዚህም መድኃኒቱ ለሥጋዊ ፍላጎት ከመገዛትና እርሱንም ከማምለክ መራቅ ነው::

### 6 ራስን ማምለክ

ከጣዖታት ሁሉ የበለጠውና አደገኛው ራስን ማምለክ ነው:: ሰው ከሥጋዊ ፍላጎቱ ማየል የተነሣ ሁልጊዜ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ይፈልጋል:: በዚህ ደግሞ ራሱን ማምለክ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዲያመልኩት፣ እርሱነቱ በሁሉም ዘንድ እንዲገን፣ እንዲከብርና እንዲፈራ ይሻል:: ሰዎች መልካምና ያማረ ነው የሚሉት ሁሉ በእርሱ ማንነት ውስጥ እንዲገኝና ሰዎችም ሁሉ እንዲያደንቁት ይፈልጋል::

እስቲ አንድ ጥያቄ እናንሣ:: ሐዋርያው ያዕቆብን ባስገደለው በንጉሥ ሄሮድስ ላይ አደጋ ያመጣበት ምንድን ነበር? የእግዚአብሔር መልአክስ ለምን ቀሰፈው? ለምንስ በትል ተበልቶ ሞተ ? ሰዎች እንደ አምላክ የማይገባውን ክብር ሲሰጡት ባለመቃወሙና የማይገባውን ክብር በመሻቱ አልነበረምን? የሐዋ.12፥21-23::

ቀደም ብለን የጠቀስናቸውን ጣዖታት ሁሉ ድል ነሥተው ነገር ግን ራስን ማምለክን ማሸነፍ የተሣናቸው ሰዎች የሄሮድስ መሰሎች ናቸው:: ይህን የመሰሉት ሰዎች ከራሳቸው በቀር ሌላ አስተዋይ፣ የተሻለ፣ ጠቢብ፣ የደመቀ፣ያማረ አለ ብለው ሰለማያ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ምኑ ራሳቸውን ያመልካሉ:: ሰውም እንዲያመልካቸው ይሻሉ:: ለዚህ ዓይነቱ ሰው የእርሱ ማንነት እርሱ ብቻ የሚያውቀውና በእርሱ አእምሮ የተሣለው እርሱነቱ ብቻ ነው:: በምኞት ብቻ የቀረ ማንነት:: ለእርሱ እንደሚመስለው ከእርሱ በቀር ሁሉም ስህተተኛ ነው:: ከሌሎች ጋር ቢጋጭ እንኳ እነርሱ እንጂ እርሱ እንዳልተሳሳተ ያምናል:: ምክንያቱም በፍጹም ስህተት አይሠራምና:: «ሰዎች ሊረዱኝ አይቻሉ እንጂ የእኔ ጠባይ ትክክለኛ ነው» የሚል የራሱ እምነት አለው::

በዓለም ላይ የሚነሡትና የተነሡት አምባገሮዎች በአብዛኛው ራስን የማም ለክ ውጤቶች ናቸው:: በመሆኑም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ከመሰ ለው አምልኮ እንድንጠበቅ እንዲህ ብሏል «በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ » ማር.8÷34::

ራስን መካድ ምን ማለት ነው? ሰው ራሱን ማምለክን ከልቡናው ያጥፋ፣ ራሱን አመድ የምድርም ትቢያ እንደሆነ ይመን ማለት ነው:: ነገር ግን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲጣላና ከአምላኩ ጋር እንዲፎካከር ከሚያደርጉት ነገሮች አንደኛው የራሱን ታላቅነትና ከሁሉ በላይ መሆኑን መሻቱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ራሳችንን መውደዳችን አይደለምን? ፍላጎታችን ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ፈቃዳችንን ከመፈጸም ይልቅ «እርሱ እግዚአብሔር ሊልቅ እኔ ላንስ ያስፈልጋል» ዮሐ.3÷30:: ያልን እንደሆነ ያንጊዜ ራሳችንን እንደካድን በዚህ ይታወቃል:: በእርግጥም ራሳችንን እንድናመልክ ይሚያደርገን ደግሞ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚጋጩ የተወሰኑ ፍላጎቶችን ለማሟላት ያለን ዓላማ ነው::

የመላእክት አለቃ የነበረውን ሳጥናኤልን ለመውደቅ ያበቃው ምንድን ነው? ራሱን የሁሉ የበላይ ማድረጉ አይደለምን? ምክንያቱም የተሰጠውን ትቶ ከሚገባው በላይ ታላቅና ከፍ ያለ ለመሆን ሽቷልና:: እናም እንዲህ ብሏል:: «ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፤ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፤ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፤ በልዑልም እመስላለሁ:: » ኢሳ.14÷13-14:: ሳጥናኤል እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ከፍ ከፍ ማለትን ፈለገ:: ነገር ግን ትዕቢቱ ውርደትን እንጂ ክብርን አላስገኘለትም:: አዳምና ሔዋንን ባሳታቸውም ጊዜ በተመሳሳይ ፈተና ነበር ያታለላቸው:: ዘፍ.3÷5

ስለዚህ ማንም ሰው እራሱን መግዛትና መካድ ከቻለ ዋነኛውን ጣዖት ከልቡ ናው አጠፋ ማለት ነው:: አሥራትን ለእግዚአብሔር ከመስጠት ይልቅ ለራሳችን ስንወስድ፣ ሰንበትን ለሥጋዊ ፈቃድ መፈጸሚያ ስንጠቀም ራሳችንን መውደዳችን አይደለምን ? ፍላጎታችን ከእግዚብሔር ትዕዛዝ ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ፈቃዳችንን ከመፈጸም ይልቅ « እርሱ እግዘአብሔር ሊልቅ እኔ ላንስ ያስፈልጋል » ያልን እንደሆነ ያን ጊዜ ራሳችንን በመካድ ሕይወታችንን ለዘለዓለም እንደምንጠብቃት እርግጠኞች እንሆናለን:: ራስን ከማምለክ ነፃ እንድንወጣ ራሳችንን ለመካድ የሚያበቃ የጸጋ ስጦታን የሚያድል መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቸርነቱ፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ ይርዱን:: አሜን::

ይቀጥላል::

## አንድ ሰው ከቅድስና ሕይወት ሲርቅ የሚታዩት ምልክቶች በየደረጃው::

1. ስመ እግዚአሔርን መጥራት፣ ሞትንና ፍርድን ማስታወስ አይፈልግም፣
2. በክርስቲያናዊ የግል ሕይወቱ /መዝሙር ማዳመጥ፣ መጸለይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ፣መጾም ወዘተ.../ እየቀነሰ ይመጣል፣
3. መንፈሳዊ ወንድሞቹንና እኅቶቹን ማግኘት አይፈልግም፣
4. መንፈሳዊ ጉባኤያትን ችላ ማለት ይጀምራል፣
5. የሚውልበትን አካባቢና ጓደኞች ይለውጣል፣
6. የሌሎችን ክርስቲያናዊ ሕይወት እየተመለከተ መንቀፍ ያበዛል፣
7. ኃጢአትን በሥውር እየፈጸመ በውጪ ቅን መስሎ ለመታየት ይሞክራል፣
8. ኃጢአትን ሲላመደው በግልጽም ይፈጽመዋል:: ለሚሠራው ሁሉ ግን ምክንያትን ይሰጣል፣
9. ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ያፋልሳል፣ የቅዱሳንን ፍቅር ያጣል፣
10. ከፍቅረ እግዚአብሔር ተለይቶ ክዶ ይገለላል::

*አንዱ ዓለም ኃ/ማርያም*
*/ቅ.ያሬድ ቤ/ክ ፣አ.አ/*

## ሠላሳ ሰባት ዓመት በማማ ላይ!

«ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አምላክ አንድ ባሕርይ ነው::» ብለው በማመናቸው በካቶሊካውያን የሮማ ሰዎች ብዙ ጸዋትወ መከራ ከተቀበሉት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ /ኦሪየንታል ኦርቶዶክስ/ ክርስቲያኖች መካከል የሶሪያ ክርስቲያኖች ይገኙበታል::

የሶሪያ መነኰሳት እምነታቸውን ለምእመኖቻቸው አጥብቀው በማስተማራቸው ፣ የነአባ እንጦንስንና የነአባ ጳኲሚስን ዱካ በመከተላቸው ፣ በገዳሞቻቸውም የአንድነት /የማኅበር/ ኑሮን በመኖራቸው የሚታወቁ ናቸው:: ከእነዚህም መካከል 37 ዓመታት ከተቀመጠበት ማማ ላይ ሳይወርድ በጾምና በጸሎት ተወስኖ በመኖሩ የሚታወቀው ሶሪያዊው ቅዱስ ስምዖን ዘዐምድ /389-459ዓ.ም/ ይገኝበታል:: ይህ አባት በምኑና ከኖረባቸው 56 ዓመታት 37 ዓመታትን በማማ ላይ ከመኖሩ በተጨማሪ በቋሚ ኵሉን /አንድ ወጥ ረጅም ድንጋይ ላይ ያረፈ፣ መደገፊያ ግድግዳ እንጂ ጣራ የሌለው «ማማ» የመሠለ ደርብ/ ሠርቶ የሌሊቱ ቁር፣የቀኑ ሐሩር ሳይበግረው እዚያ ሆኖ በመጾም፣ በመጸለይ እና በማስተማር ወዘተ... የብሕትውና ኑሮ መኖርን የጀመረው እርሱ ነው:: ሌሎቹም ይህንኑ አብነት አድርገው ሲኖሩ ከታች /ከመሬት/ ከሚኖሩት ትምህርታቸውን ለመስማት፣ ካደረባቸው ደዌ ለመፈወስ ወደእነርሱ ከሚመጡት ምእመናን ጋር የሚገናኙት በመሰላል አማካይነት ነበር::

ይህ አባት በአንድ ቦታ ተወስኖ 37 ዓመታትን በጾም፣ በጸሎትና በትሩፋት ኖረ:: እኛስ ከእድሜያችን ለጾም፣ ለጸሎትና ለስግደት እንዲሁም መንፈሳዊ ምግባራትን ለመፈፀም የምናውለው ጊዜ ምን ያህል ይሆን?

ለሁሉም እግዚአብሔር ከስምዖን ዘዐምድ ረድኤት በረከት ይክፈለን :: አሜን ::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ብሉይ ኪዳን በሐዲስ ኪዳን

ዲ.ደጀኔ ሺፈራው

/ካለፈው የቀጠለ/

## ሀ. ሊቀ ካህናታችን ማነው?

በታላቁ መምህር በገማልያል እግር ሥር በትጎትና የተማረው ምሁረ አሪት ቅዱስ ጳውሎስ ከደማስቆ ከተማ ተጠርቶ ሕገ ወንጌልን ተቀብሎ፣ በሕገ ወንጌል ጸንቶ ለወገኖቹ ለዕብራውያን ባስተላለፈው መልእክቱ «ስለዚህ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፣ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ።» ዕብ.3÷1 « ወብነ ሊቀ ካህናት ዐቢይ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ዘተለዓለ እምሰማያት፤ እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላለን ፣ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ ፣ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። » ዕብ.4÷14። ብሏቸዋል።

ሐዋርያው ይኸንን ያለምክንያት አልጻፈላቸውም ። ዕብራውያን መከራ ብንቀበል ማን አብነት ይሆነናል? እንዳይሉ እና ወደ ኋላ እንዳያፈገፍጉ መከራ የተቀበለውን ኢየሱስ ክርስቶስን አብነት አድርገው ፣ መከራውን እየታገሡ በክርስትና ጐዳና እንዲጓዙ ነው። ዳግመኛም ከይሁዲነት ወደ ክርስትና ብንመለስ ማን ያስታርቀናል እንዳይሉ ደግሞ ቢመለሱ፣ በሕገ ወንጌል አምነው ቢጠመቁ፣ ሥጋውንና ደሙን ቢቀበሉ፣ እርቅን በሞቱ አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ የፈጸመ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በሚገባ እንዲያውቁ ነው።

## የሊቀ ካህናቱ ሥራ ምን ነበር?

በኦሪቱ የሊቀ ካህናት ሥራ ቤተ መቅደስን ማስተዳደር እና ካህናትን መቆጣጠር፣ በሸንጐም ላይ ሊቀመንበር መሆን ነበር። 1ሳሙ.3÷12፣ 2ነገ.12÷7፣ 22÷4፣ ማቴ.26÷57-65። ከዚህም ሌላ ሊቀካህናቱ በማስተሥሪያ ቀን ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ልዩ መሥዋዕት ያቀርባል። በዚህም ቀን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ በታቦቱ ላይ ደም ይረጫል። ዘሌ.16÷1-34።

የእሥራኤል ሕዝብ በ7ኛው ወር በአሥረኛው ቀን /ጥቅምት 10 ቀን ገደማ/ ሥራቸውን ሁሉ ትተው ይጾሙ ፣ኃጢአታቸውንም ይናዘዙ ነበር። ሊቀ ካህናቱም የማዕረግ ልብሱን አውልቆ /በትኅትና/ ሌላ ልብስ በመልበስ መጀመሪያ ለራሱ እና ለካህናቱ ቀጥሎም ለሕዝቡ መሥዋዕት ያቀርባል። በታቦቱ መክደኛ ላይም ደም ይረጫል። የታቦቱም መክደኛ የስርየት መክደኛ የሚባለው ፣ ስለ ስርየተ ኃጢአት የሚፈሰው ደም ስለሚረጭበት ነው። እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሁላችንም ኃጢአት፣ ኃጢአታችንን ይሰረይ ፣ በደላችንም ይደመሰስ ዘንድ መሥዋዕትን በማቅረቡ ሊቀ ካህናት ተብሏል። ጌታችን ስለ እኛ ያቀረበው መሥዋዕት መለኮት የተዋሐደውን የራሱን ሥጋ ና ደም ነው። እርሱ ኃጢአታችንን ፈጽሞ የሚያስተሰርይ በግ ሆነልን፣ ተሠዋልንም። ዮሐ. 1÷29 «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና፤ » እንዲል 1ቆሮ. 5÷7። ኢየሱስ ክርቶስ ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ፣ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ የሆነ ሊቀ ካህናት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ የጌታችን ክህነት በመልከ ጼዴቅ ክህነት መመሰሉንም ጭምር ተናግሯል። «እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ፤ አይጸጸትም።» መዝ. 109÷4። ዕብ.5÷6።

## ለ. መልከ ጼዴቅ ማነው ?

መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥ ነበር። ይህም የሰላም ንጉሥ ማለት ነው ። ሳሌም በሄኖን አቅራቢያ የነበረ የመልከ ጼዴቅ ከተማ ነው። ዘፍ.14÷18፤ ዮሐ. 3÷23። መልከ ጼዴቅ የሰላም ንጉሥ የተባለበት ምክንያት የአገሩ ሰዎች ሄደው ንግሥልን ቢሉት በጎልጎታ የተቀበረውን አፅም ይጠብቅ ስለነበር ያስጠበቀኝን ትቼ አይሆንም ብሏቸዋል። ይሁን እንጂ ተጣልተው ወደ እርሱ ሲመጡ የማታ ማታ ያስታርቃቸው፣ ሲከራከሩም እውነት ይፈርድላቸው ነበር። ከዚህም የተነሣ ንጉሠ ሰላም ወጽድቅ ተብሏል።

ለመልከ ጼዴቅ አባቱ እገሌ ነው እናቱ ደግሞ እገሊት ናት ተብሎ አልተነገረለትም። «ወአልቦ ጥንት ለመዋዕሊሁ ወኢማኅለቅ ለሕይወቱ» በዚህ ቀን ተወለደ በዚህ ቀን ደግሞ ሞተ ብሎ የተናገረለት መጽሐፍ የለም። ምነው በስንክሳር ተጽፎ የለምን ? ቢሉ በሌዋውያን መጽሐፍ ስላልተጻፈ ነው። «በአምሳሊሁ ለወልደ እግዚአብሔር ይነብር ክህነቱ ለዝሉፉ» የመልከጼዴቅ ክህነት ለወልደ እግዚአብሔር ክህነት በምሳሌነቱ ለዘለዓለሙ ጸንቶ የሚኖር ነው።

አበ ብዙኃን አብርሃም ኮሎዶጎሞርንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ነገሥታት ወግቶ ድል አድርጎ በተመለሰ ጊዜ ምሳሌውን እንዲያይ ተፈቅዶለት ነበርና ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ መልከጼዴቅ ሄደ። መልከጼዴቅም በመንፈስ ተረድቶ በሴዊ ሸለቆ ሊቀበለው ወጣ። እንጀራንና የወይን ጠጅንም አወጣ፣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ። ባረከውም ። ዘፍ. 14÷17-20 ቅዱስ ጳውሎስ ይኸንን ታሪክ አስታውሶ እንደሚከተለው ለዕብራውያን ጽፎላቸ ዋል። «የሳሌም ንጉሥ እና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከ ጼዴቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው ፤ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አሥራት አካፈለው። የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው። አባትና እና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፤ ለዘመኑም ጥንት ወይም ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም፤ ዳሩ ግን በእግዚአ ብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።» ዕብ.7÷1-3።

## ሐ. የመልከጼዴቅ ምሳሌነት:-

ለመልከጼዴቅ አባቱ እገሌ ነው እናቱ ደግሞ እገሊት ናት ተብሉ አለመነገሩ ለጌታም ለሰማያዊ ልደቱ ከአብ ሲወለድ እናቱ እገሊት ናት አይባልም። ለምድራዊ ልደቱም ከእመቤታችን ሲወለድ አባቱ እገሌ ነው አይባልም። እርሱ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት፣ ድኅረ ዓለም ደግሞ ከእመቤታችን ያለ አባት ተወልዷልና።

ለመልከ ጼዴቅ «ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም።» ተብሎለታል ። ጌታችንም ለዘመኑ ጥንትና ፍጻሜ የለውም። «አልፋና ኦሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው ፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።» ራእ፡ 22÷1፣1÷17

መልከ ጼዴቅ በስንዴ እና በወይን ያስታኩት ነበረ። ጌታችን ደግሞ ሥጋውን በስንዴ ደሙንም በወይን አድርጐ ሰጥቶናል። ማቴ. 26÷26። መልከ ጼዴቅ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ለመጣው ለአብርሃም ኅብስ ትና ወይንን እንደመገበው ጌታም በመስቀል ላይ የቆረሰው ኅብስት ሥጋውንና ያፈሰሰውም ወይን ደሙን ዮርዳኖስን ተሻግረን ለቀረብን ለውሉደ ጥምቀት መግቦናል።

መልከ ጼዴቅ ሹመቱን ከእገሌ አግኝቶታል ፣ ለእገሌም ተላልፏል አይባልም። ሹመቱን ያገኘው ከእግዚአብሔር ነው። «እንዲሁ ክርስ ቶስ ደግሞ ሊቀ ካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም። ነገር ግን :- አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ያለው እርሱ ነው፤ እንደዚህም በሌላ ሥፍራ ደግሞ አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ይላል።» ዕብ.5÷5። በዚህ መሠረት ጌታንም ስለለበሰው ሥጋ «ሤሞ አቡሁ - አባቱ ሾመው ይለዋል» እዚህ ላይ የተሾመው ሥልጣንን ያገኘው በተዋሕዶ አምላክ የሆነ ሥጋ ነው ። ይህም ሹመት እንደ መልከ ጸዴቅ ሹመት ለእገሌ አለፈ አይባልም።

የሌሎቹን ሊቃነ ካህናት ሹመት ብንመለከት ግን እንዲህ አይደለም ። ከአንዱ ወደ ሌላ የሚተላለፍ ነበር ። ለምሳሌ የአሮን ሹመት ለልጁ ለአልዓዛር ተሰጥቷል። ዘሁ.20÷22 ። ካህናት ፣ሊቃነ ካህናት ሆነው የሚሾሙትም ሌዋውያን ብቻ ነበሩ። ቅዱስ ጳውሎስ መልከጼዴቅን የጠቀሰው ያለምክንያት አልነበረም። በሮም ክታቡ /ሮሜ.4÷1/ ጽድቅን ከኦሪት አውጥቶ ለወንጌል እንደሰጠ ተናግሮ፣ ለዚያው ምስክር አብርሃምን እንዳመጣ ፣ ከዚህም ክህነት ከቤተ ሌዊ አውጥቶ ለቤተ ይሁዳ ለሁሉ እንደሰጠ ተናግሮ ለምስክር መልከጼዴቅን አምጥቶታል። ምክንያቱም አይሁድ የጥንቱን ይዘው ክህነት ለሌዋውያን ብቻ ነው ይሉ ስለነበር ነው።





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

### ቅድስተ ቅዱሳን:-

ቅድስተ ቅዱሳን የቤተ መቅደስ ውስጣዊ እና ሦስተኛው ክፍል ነው:: ዘጸ 26÷33-35፣ « ወለውሣጢትስ ደብተራ እንተ እምድኅረ ካልእ መንጦላዕት ይብልዋ ቅድስተ ቅዱሳን » ከሁለተኛው መጋረጃ ወዲያ ያለችውን ዐሥራቱን ክንድ ቅድስተ ቅዱሳን ይሏት ነበር:: « በውስጥዋም የወርቅ ማዕጠንት ነበረ፣ ሁለተኛዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት ፣ በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ፣ በላይዋም ማስተስሪያውን የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል ነበሩ:: » ዕብ.9÷3-5::

ቅድስተ ቅዱሳን የወንጌል፣ የመንግሥተ ሰማያትና የነፍስ ምሳሌ ናት:: «ሊቀካህናቱ ብቻውን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ይገባባታል፣ እርሱም ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ስሕተት የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም:: » ዕብ.9÷7:: «ወክርስቶስ ዘመጽአ ከዊና ሊቀ ካህናት ለእንተ ትመጽእ ሠናይት በውስተ እንተ ተዓቢ ወትሄይስ ደብተራ እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ ወኢኮነት በውስተ ዝዓለም ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀካህናት ሆኖ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነ ድንኳን የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም::» ዕብ. 9÷11-12

ለምትመጣው ሕግ ለወንጌል ሊቀካህናት ሆኖ የመጣው ክርስቶስ ግን በምክንያተ ዘርዕ ያይደለ እንበለ ዘርዕ /ያለ ዘር/ የተገኘች ሰውነቱን ይዞ /ተዋሕዶ/ የገዛ ደሙን በመስቀል ላይ አንድ ጊዜ አፈሰሰ :: እንደ ብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናት በየዓመቱ ደም ማፍሰስ አላስፈለገውም:: አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ በፈጸመው ቤዛነት ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከራሱና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አስታረቀን:: ይህም በመስቀል ላይ አንድ ጊዜ ስለተፈጸመ ከመስቀል በኋላ ያስታርቃል /ያማልዳል/ አይባልም:: ዮሐ. 16÷26 እንዲህ ማለት በየጊዜው መከራ ይቀበላል ፣በየጊዜው ይሞታል ማለት ነውና::

«ወአኮ ዘልፈ ዘይሠውዕ ርእሶ ዘይገብር ሊቀ ካህናት ወይበውከመ ውስተ ቅድስተ ቅዱሳን በበዓመት በደመ ባዕድ ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም::» ዕብ.9÷25:: እንዲህ ቢሆን ኖሮ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር:: አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ማለትም ኑሮ ኑሮ አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም በሱ መሥዋዕትነት ኃጢአትን ያጠፋት ዘንድ አንድ ጊዜ ራሱን ሠዋ:: አንድ ጊዜ ሞተ:: የብዙዎችን ኃጢአት ያስተሰርይ ዘንድ አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታያቸዋል:: ዕብ.9÷26-28:: ይህም ማለት ከዚህ ቀደም በሰው ኃጢአት ሊሞት እንደ መጣ ከእንግዲህም ወዲህ በሰው ኃጢአት ሊሞት አይመጣምና ::

እነዚያ የቀደሙ ካህናት ብዙዎች ቢሆኑም ሞት ያሳልፋቸው ነበር:: በሕይወት ይኖሩ ዘንድ አያስናብታቸውም ነበርና:: አንድ የሚሆን እሱ ግን ለዘላለም ይኖራል:: ክህነቱም አይሻርም:: ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል:: ይህም ማለት አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ በፈጸመው ቤዛነት በርሱ አስታራቂነት ወደ እግዚአብሔር የቀረቡትን ማዳን ይቻለዋል ማለት ነው:: ወደ እግዚአብሔር የቀረቡትን ሲል በራሱ ቤዛነት ወደ ራሱም የቀረቡትን ማለት ጭምር እንደሆነ ልንዘነጋ አይገባም:: ምክንያቱም እርሱም እግዚአብሔር ነውና:: ዮሐ.1÷1 ፣ የሐዋ. 20÷28:: እዚህ ላይ የሚያስፈልገው የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት እንዲሁም ምሥጢረ ሥጋዌን ጠንቅቆ መረዳት ነው:: «እስመ ለግሙራ ሕያው ውእቱ ወይ ተነብል ሎሙ:: ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና» የሚለው ደግሞ ትርጉሙ በዕለት ዓርብ ባደረገው ተልእኮ በፈጸመው ቤዛነት ሲያድንበት ይኖራል ማለት ነው:: የዘላለም መሥዋዕት ሆኖልን ዕለት ዕለት እየተመገብን ሕይወት የምናገኝ በትን ሥጋውንና ደሙን ሰጥቶናልና:: /ዕብ.7÷23-25/

ቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢር ይጠነቅቃሉ እንጂ ዘይቤ አይጠነቅቁም :: ይህም ማለት ያለፈውን እንደሚመጣ ፣ የሚመጣውን ደግሞ እንዳለፈ አድርገው የሚናገሩበት ጊዜ አለ:: ለምሳሌ ገና ወደፊት የሚመጣ ውን ድርጊት ልክ ተፈጽሞ እንዳለፈ አድርገው ሲናገሩ እስቲ እንመልከት ::

1.«እግዚአብሔር አምላክም አለ:- እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ::» ይላል:: ዘፍ. 3÷22:: እንደ አንዱ ሆነ ማለት እንደ ወልድ ሆነ፣ ሰው አምላክ ሆነ ማለት ነው:: ይህ ደግሞ የሆነው አዳም በበደለ ጊዜ አለመሆኑ ለማንም ግልጥ ነው:: ሁላችንም እንደምንረዳው አምላክ ሰው ሰውም አምላክ የሆነው ይህ ቃል ተነግሮ አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ከተፈጸመ በኋላ ጌታችን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በተወለደ ጊዜ ነው::

2. «ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፣ የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ :: እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ:: እነርሱም አዩኝ:: ተመለከቱኝም:: ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ ፣ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ::» መዝ.21÷16:: ይላል:: እዚህም ላይ ገና ከአንድ ሺ ዘመን በኋላ የሚፈጸመውን ነው:: ልክ እንደተፈጸመ አድርጎ በዳዊት አንደበት የተናገረው:: ይህ ሁሉ በክርስቶስ ላይ መቼ እንደተፈጸመ ታውቃል:: ማቴ.27÷35::

ተፈጽሞ ያለፈውን ድርጊት ደግሞ ልክ አሁንም እየተፈጸመ እንዳለ ፣ወደፊትም ሲፈጸም እንደሚኖር አድርጎ የሚናገረውን ክፍል ደግሞ እንመልከት::

1. «እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል::» ይሁ.ቁ7ይላል:: መቼም ሰዶምና ገሞራ አንድ ጊዜ በእሳትና በዲን ተቃጥለው ጠፍተዋል፣ እሳቱም የለም:: ቃሉ ግን አሁንም እየተቃጠሉ እንዳሉ አድርጎ ይናገራል:: ይህንን የመሳሰሉ ጥቅሶች ሌሎችም አሉ:: ለግንዛቤ ያህል ግን ይኸው ይበቃል::

ይኼንን ሁሉ የዘረዘርነው ያለምክንያት አይደለም:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ፈጽሞ ያለፈውን ቤዛነት መጻሕፍት «ስለ እነርሱ ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና» ብለው ልክ አሁንም እያማለደ እንዳለ ወደፊትም ሲያማልድ እንደሚኖር አድርገው በመናገራቸው ይኼንን ይዘው ለተሰናከሉ መልስ ላልተሰናከሉም መጠበቂያ እንዲሆን ነው:: ጌታችን «ተፈጸመ» በማለት ሁሉን ነገር አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ፈጽሞታልና:: «እርሱም እንደነዚያ ሊቀ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት፣በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም ፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና::» ዕብ. 7÷27

የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን::

ይቀጥላል::

## ዓለም አታላይ ናት

......... ብልህ ሁንባት፣
......... እውነቱን አውጣባት፣
......... ትብለጭለጭ ትንካት፣
......... አትሳሳትባት፣
......... መልካም ሥራባት፣
......... በቃል ተጓዝባት፣
......... አንተ ግን ዳንባት፣
......... በገነት ለነፍስህ፣
......... በምድር ለጉርስህ፣
......... ቤዛ እንዲሆንልህ፣
......... በዓለም መስገብገቡን
በፍጹም እረስተህ፣
......... አታላይ ናትና
እንዳትወድቅ ተታለህ፣
......... መኖር ይገባሃል ሁሌም
ተዘጋጅተህ::

አይችሉህም መንግሥቱ
/ባሕር ዳር/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቅዱሳን መላእክት

ከ ብርሃኑ ጎበና

ቅዱስ ማለት የተለየ፣ የተከበረ፣ የተመሰገነ፣የተመረጠ ማለት ነው። ቅዱሳን መላእክት ስንልም የተመሰገኑ፣ ክርኩሳን መላእክት የተለዩ፣ ክቡራን መላእክት ማለታችን ነው። መላእክት ሁለት ወገን ናቸው። ብርሃናውያን መላእክትና የጨለማ አበጋዝ የሆነው የዲያብሎስ ሠራዊት የሆኑት እኩያን መላእክት። ስለዚህ የእግዚአብሔርን መላእክት ከሌሎቹ መላእክት በአጠራር የምንለያቸው ቅዱስ በሚል ቅጽል ነው።

## መላእክት መቼ ቀን ተፈጠሩ?

መላእክት የተፈጠሩት በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ ነው። ቅዱስ ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ /ሄክስኢሜሮን/ ተብሎ በሚጠራው መጽሐፉ እግዚአብሔር መላእክትን በዕለተ እሑድ ፈጥሮ በሦስቱ ሰማያት በኢዮር፣ በራማና በኤረር ፣ በከተማ አሥር ፣ በነገድ መቶ አድርጎ አሰፈራቸው ብሏል።

## አሰፋፈራቸውም:-

በኢዮር:- በኢዮር ያሉትን መላእክት በ4 አለቃ አርባ ነገድ ከፈላቸው።

ኢዮርን እንደ ፎቅ ቤት አድርጎ በአራት ከተማ ከፈላት። በኢዮር በላይኛው ከተማም አሥሩን ነገድ ስማቸውን አጋእዝት ብሎ በመሰየም አለቃቸው ይሆን ዘንድ ሳጥናኤልን ሾመው።

በኢዮር በሁለተኛው ከተማ አሥሩን ነገድ ስማቸውን ኪሩቤል ብሎ ኪሩብ የተባለውን መልአክ አለቃ አድርጎ ሾመላቸው። ሕዝ.10÷1

በኢዮር በሦስተኛው ከተማ አሥሩን ነገድ ስማቸውን ሱራፌል ብሎ በመሰየም ሱራፌል የተባለውንም መልአክ አለቃቸው አደረገው። ኢሳ.6÷2

በኢዮር በአራተኛው ከተማ አሥሩን ነገድ ስማቸውን ኃይላት /1ጴጥ. 3÷22/ በማለት ቅዱስ ሚካኤልን በአለቃነት ሾመላቸው።

በራማ :- ራማ በተባለው የብርሃን ሰማይ ላይ ያሉትን መላእክት በሦስት አለቃ ሰላሣ ነገድ አድርጎ ከፈላቸው። ራማንም ሦስት ከተማ አድርጎ ከፍሏታል።

በመጀመሪያ በራማ የሠፈሩት አሥሩ ነገድ ስማቸው አርባብ ይባላል። አለቃቸውም ቅዱስ ገብርኤል ነው።

በሁለተኛው ከተማ የሠፈሩት አሥሩ ነገድ መናብርት ሲባሉ አለቃቸውም ሩፋኤል ነው።

በሦስተኛው ከተማ ያሠፈራቸው አሥሩን ነገድ ስማቸውን ሥልጣናት /1ጴጥ.3÷22/ በማለት አለቃቸው ይሆን ዘንድ ሱርኤል የተባለውን መልአክ ሾሞታል።

በኤረር :- ኤረር የተባለውን ሰማይ እንደ ራማ በሦስት ከተማ የከፈለው ሲሆን የቀሩትን ሰላሣ ነገድ በእነዚህ ከተማዎች አሥፍሩአቸዋል።[1]

በመጀመሪያው ከተማ አሥሩን ነገድ መኳንንት /መዝ.3/24÷7-10/ በማለት ሰዳክያል የተባለውን መልአክ አለቃ አድርጎላቸው አሥፍሩአቸዋል። በሁለተኛው ከተማ አሥሩን ነገድ ሊቃናት በማለት አለቃቸው ይሆን ዘንድ ሰላታኤል የተባለውን መልአክ ሾሞታል።

በሦስተኛ ከተማ አሥሩን ነገድ መላእክት /ጴጥ.3÷12/ ብሎ ሰይሟቸዋል። አናንያል የተባለውን መልአክም አለቃቸው አድርጎታል።

በእነዚህ በሦስቱ የመላእክት ሰማያት ላይ የሠፈሩት መላእክት በነገድ መቶ ሲሆኑ በከተማ ደግሞ አሥር ነበሩ። ከእነርሱም ሰማልያል /ሳጥናኤል/ አንዱን ነገድ ይዞ ከክብሩ ወርዷል። ኢሳ.14÷12

## የመላእክት ባሕርይ:-

መላእክት በአፈጣጠራቸው ረቂቃን መናፍስት በመሆናቸው እንደ ሥጋ ለባሽ ፍጥረታት አይበሉም ፣አይጠጡም፣ አያገቡም ፣ ማቴ 22÷30። ሉቃ 24÷39 ጾታም የለቸውም።

አንዳንድ ሰዎች ግን መላእክት በአንድ ወቅት የሰውን ልጆች እንዳገቡ ወይም በፍትወት ከሰዎች ልጆች ጋር እንደወደቁ አድርገው ይናገራሉ። ለዚህም መረጃ አድርገው ለማቅረብ የሚሞክሩት « የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች አገቡ » የሚለውን ኃይለ ቃል ነው። ዘፍ.6÷2።

በዚህ ቦታ ላይ የእግዚአብሔር ልጆች /መላእክት/ ተብለው የተጠሩት ረቂቃኑ መላእክት ሳይሆኑ ሥጋ ለባሽ የሆኑ ደቂቀ ሴት /በአቤል ፈንታ አዳም የወለደው የሴት ልጆች/ ሲሆኑ ዘፍ. 4÷25። የሰው ሴቶች ልጆች የተባሉት ደግሞ የቃየል ልጆች ናቸው። ይኸንንም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ሄኖክ እንዲህ ሲል ገልጾታል « የሰው ልጆች ከበዙ በኋላ እንዲህ ሆነ ። በዚያ ወራትም መልከ መልካሞች ደመግቡዎች ልጆች ተወለዱላቸው። በደብር ቅዱስ ያሉ ደቂቀ ሴትም እነሱን አይተው ወደዱአቸው። እርስ በርሳቸውም ኑ ለኛ ከቃየል ልጆች ሴቶችን እንምረጥ ለኛ ልጆችን እንውሰድ አሉ» መጽ.ሄኖክ 1÷1-3።

ደቂቀ ሴት ስለምን የእግዚአብሔር ልጆች /መላእክት/ ተባሉ?

1ኛ. ስለ አለቅነታቸው:- የግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት በማለት ይጠራቸዋል። መልአክ የሚለው ቃል የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አለቃ ማለት ነው። ቅዱስ መጽሐፍም መልአክ የሚለውን ቃል አለቃ ማለት መሆኑን ያስገነዝበናል። ለምሳሌ በዮሐንስ ራእይ 2÷1፣ 8÷12 ላይ ያለውን ብንመለከት አስረጅ ይሆናል። በእነዚህ ስፍራዎች «ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ» ተብሎ እናገኛለን። ይህ መልአክት ደግሞ ለሰማያውያን መላእክት ለነ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል የተላከ እንዳልሆነ የታወቀ ነው። ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አለቆች የተላከ እንጂ። ዛሬ የዚህ ደብር አለቃ ተብሎ እንደሚጠራ ሁሉ። «በኤፌሶን ላለች ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ /አለቃ/ ለሚልከው መልእክት በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ» ተብሏል።

ደቂቀ ሴትም /የሴቶች ልጆችም/ መላእክት መባላቸው አለቆች በመሆናቸው ነው።

2ኛ ስለንጽሕናቸውና ቅድስናቸው :-

ከሴት ልጆች መካከል በደብር ቅዱስ ከሴት ርቀው፣ ንጽሕና ጠብቀው በጾም ተጠምደው የሚኖሩ ስለነበሩ በዚህ ግብራቸው መላእክትን መስለዋልና የእግዚአብሔር ልጆች በመባል ተጠርተዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ትዕዛዝ የሚኖሩትን ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ይላቸዋል። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በቀዳማዊ ክታቡ «የእግዚአብሔር ልጆች ብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ » ብሏል። 1ዮሐ. 3÷1።

በጥምቀት ከእግዚአብሔር ዳግም ተወልደን የእግዚአብሔር ልጆች እንደምንሆን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯል «ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል» ይህም ደግሞ በጥምቀት የሚገኝ ጸጋ ነው። ዮሐ. 3÷1።

ከላይ በተገለጸው ምክንያት ደቂቀ ሴትን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ በመጥራት በኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር መንገድ ከወጡት ከቃየል ልጆች ጋር በፈጸሙት ዝሙት እግዚአብሔር እንዳዘነባቸው ቅዱስ መጽሐፍ አስረድቷል።

ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት ሰማያውያን መላእክት ናቸው የሚለው አመለካከት ስህተት መሆኑን የምንረዳው ከቅዱስ መጽሐፍ ባገኘነው ትምህርት መሠረት ነው። ጥቀድሞ ተብሎ እንደተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ሰማያውያን መላእክት በተፈጥሯቸው /በባሕሪያቸው/ ማግባት መጋባት መብላት መጠጣት የለባቸውም ። ፍትወተ ሥጋ የሥጋ ለባሹ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባሕርይ ነው። ስለዚህ ሰማያውያን መላእክት ከሰው ልጆች ጋር በፍትወት አልወደቁም። ማቴ. 22÷30

## የመላእክት አገልግሎት:-

ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ለአገልግሎት የሚፋጠኑ ናቸው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትንና ቸርነትን ወደ ሰው ልጆች፣ የሰዎችንም ጸሎትና ልመና ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ ናቸው።

---

1 ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 784።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

**ስለ ተራዳኢነታቸው - በቅዱሳት፦ መጻሕፍት**

ቅዱሳን መላእክት በመንገዳችን ሁሉ እንደሚጠብቁን ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል « በመንገድ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል» መዝ. 90/91/÷11፡፡

ያዕቆብ የልጁ የዮሴፍን ልጆች ምናሴንና ኤፍሬምን ሲባርክ «አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እርሱ እግዚአብሔር፣ ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን የመገበኝ እግዚአብሔር፣ __ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ__ እርሱ እነዚህን፣ብላቴኖች ይባርክ» ብሏል፡፡ ዘፍ.48÷16 በዚህም መላእክት ከክፉ ነገር ሁሉ የሚያድኑና የሚጠብቁ እንደሆኑ፣ መባረክም እንደሚችሉ አስገንዝቧል፡፡

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት የመላእክትን አዳኝነት ሲያስገነዝብ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፤ ያድናቸውማል፡፡» ብሏል፡፡ መዝ33/34/÷1

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሕዝበ እግዚአብሔር /ለእሥራኤል/ አገልጋዮች መላእክትን ሊያሳዝኑ እንደማ ይገባ ሲያስጠነቅቃቸው «በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ፣ ወደ አዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ፣ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ፤ በፊቱ ተጠንቀቁ ቃሉንም አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት» ዘጸ. 23÷20

የቅዱሳን መላእክት ረዳትነት አስፈላጊ መሆኑን ነብየ እግዚአብሐር ዳንኤል ሲያመለክት «የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ እነሆም ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ ፡፡ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት» ዳን. 10÷13

በተለይ በፍጻሜ ዘመን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ለክርስቲያኖች በአማላጅነቱና በተራዳኢነቱ እንደሚቆምላቸው «ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል» ተብሎ በነቢዩ በዳንኤል መጽሐፍ ተገልጦአል፡፡ ዳን. 12÷1

የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት በሁለት መንገድ መሆኑን ማለትም የሰውን ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር የሚያደርሱና የእግዚአብሔርንም ምሕረት ለሰው ልጆች የሚያመጡ ናቸው፡፡ በተለይ የሰዎች መከራ፣ ዕንባና ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር የሚያደርሱና ለሰዎች ልጆች እንደሚያማልዱ በትንቢተ ዘካርያስ እንዲህ የሚል ተጽፏል «... የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ እነዚህን ሰባ ዓመት የተቆጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከመቼ ነው? አለ.... እግዚአብሔር መልሶ ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ __በምልካምና በሚያጽናና ቃል__ ተናገረው፡፡ ስለዚህም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ እንዲህ አለኝ ስበክ እንዲህም በል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡፡ ... ወደ ኢየሩሳሌም በምሕረት ተምልሻለሁ» ዘካ. 1÷12-17፡፡

ጌታ በዘመኑ ስብከቱ የቅዱሳን መላእክትን አማላጅነት በምሳሌ ሲያስረዳ «አንድ ሰው በታወቀች በወይኑ ቦታ ውስጥ በለስ ነበረችው ፍሬ ሊለቅም



ወደ እርስዋ ሄደ አላገኘም፡፡ የወይኑን ጠባቂም የዛችን በለስ ፍሬ ልለቅም ስመላለስ እነሆ ሦስት ዓመት ነው፡፡ አላገኘሁም፡፡ እንግዲህስ ምድራችንን እንዳታቦዝን ቁረጣት አለው፣ እሱም መልሶ እንዲህ አለው፣ አቤቱ የዘንድሮን እንኳ ተዋት፡፡ ዙሪያዋን አፈር እስክአስታቅፋት ፍግም እስከአፈስባት ድረስ፣ ምናልባት ለከርሞ ታፈራ እንደሆነ፣ ያለዚያ ግን እንቆርጣታለን፡፡» ሉቃ. 13÷7-9፡፡

በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር የበለስዋ ባለቤት እግዚአብሔር ነው፡፡ በለስ የሰው ልጅ ነው፡፡ የወይኑ ጠባቂም ጠባቂ መልአክ ነው፡፡ አማላጆቻችን መላእክት ፈጣሪያችን በሥራችን አዝኖ በሚፈርድበት ጊዜ «አቤቱ ጌታ ሆይ ይህቺን ያሁንዋን ብቻ ታገሥ፣ እኛ ተራድተን መልካም ምግባር እንዲሠራ እናደርገዋለን፡፡ ዳሩ ግን ተራዳኢነታችንን ንቆ መልካም ምግባር የማይሠራ ከሆነ እንደፈቃድህ ይሁን» በማለት በአማላጅ ነታቸው ይራዳሉ ፡፡ ሙሴ እሥራኤል እግዚአብሔርን አሳዝነው ጽኑ ፍርድ ተፈርዶባቸው የፈረደውን ፍርድ በምልጃው እንዲያነሣ እንዳደረገው ሁሉ ፡፡ ዘጸ 32÷10-14፡፡

የቅዱሳን ጸሎት የሚያርገው በመላእክት እጅ ነው፡፡ ለዚሁም ማስረጃ የሚሆነን በዮሐንስ ራእይ ላይ ተጽፎ የምናገኘው ነው፡፡ «... የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው፡፡ የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር በመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ፡፡ » ራእይ 8÷3-5፡፡

ስለዚህ ቅዱሳን መላእክት ጸሎታችንን፣ ልመናችንን እና ዕንባችንን በእግዚአብሔር ፊት ያቀርባሉ፡፡ መልስም ያሰጣሉ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስም የመላእክትን ተራዳኢነት ሲያስገነዝብ «ሁሉ መዳንን ይወርስ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?» ብሏል ፡፡ ዕብ. 1÷14፡፡

## ብሂለ አበው

አንድ መንፈሳዊ ወንድም ወደ አንድ አባት ቀርቦ «አባቴ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገንዘብ ላደርግ የምችለው እንዴት ነው?» ብሎ ጠየቃቸው፡፡ እኒያ አባትም «አንድ ሰው ትኅትና ካለው፣ በሌሎችም ላይ መፍረድ ካቆመ እግዚአብሔርን መፍራት ይችላል፡፡ ሲሉ መለሱ ለት፡፡

ሌላ ወንድም ደግሞ ሌላ አባትጋ ሄዶ «አባቴ ለምን ልቤ ከድንጋይ ጠነከረ ? ለምንስ እግዚአብሔርን አልፈራም? » ሲል ጠየቃቸው፡፡ እኒያ አባትም «የእኔ ልጅ አንድ ሰው ስለ ሠራው ሥራ የሚቀበለውን ፍርድ ካልዘነጋ ፈሪሃ እግዚአብሔር ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም እራሱን «ነፍሴ ሆይ አስተውዪ በእግዚአብሔር ፊት ትቆሚያለሽ ! » እንዲሁም «ለሌሎች ማድረግ ያለብኝ ነገር ምንድን ነው? ካለ በሕይወቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ፈርቶ ይኖራል፡፡» ሲሉ መለሱ ለት፡፡

እኛም « በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ፣ ራሳችሁን ፈትኑ፡፡ » ተብለናልና፡፡ /2ኛ ቆሮ.13÷5/

የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ የሆነውን ፈሪሃ እግዚአብሔርን እንዳናጣ ዘወትር ራሳችንን እንጠይቅ፡፡ ምሳሌ 1÷7 ፡፡

ምንጭ
´The wisdom of the desert fathers´፣ገጽ 2





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

## ጸሎተ ፍትሐት ምንድን ነው? ለምንስ ይጠቅማል?

ፍትሐት ማለት ከዚህ ዓለም በሞት ለሚለዩት ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከሠሩትና ከፈጸሙት በደል እንዲነጹ ከማእሠረ ኃጢአት እንዲፈቱ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ጸሎት ነው:: ቤተክርስቲያን ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ ታዝዛለች::

ጸሎተ ፍትሐት ለበደሉት ስርየተ ኃጢአትን ፣ ይቅርታን ዕረፍተ ነፍስን ያስጣል፣ለደጋጐች ደግሞ ክብርን ፣ ተድላን፣ ዕረፍትን ያስገኛል::

ሙታንና ሕያዋን የሚገናኙት በጸሎት አማካኝነት ነው:: «ሕያዋን ለሙታን ይጸልያሉ ሙታንም ለሕያዋን ይለምናሉ:: ሄኖ.12÷34:: ሕያዋን ለሙታን የሚጸልዩት ጸሎትና የሚያቀርቡት መሥዋዕት በግልጽ እንደሚታይ ሁሉ ሙታንም በአጸደ ነፍስ ሆነው በዚህ ዓለም ለሚቆዩ ወገኖቻቸው ሕይወትና ድኅነትን፣ ስርየተ ኃጢአትንና ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን ጽንዓ ሃይማኖትን እንዲሰጣቸው፣ በንስሐ ሳይመለሱ፣ ከብልየተ ኃጢአት ሳይታደሱ እንዳይሞቱ፡ ፈጣሪያቸውን ይለምናሉ:: ይህም ሥርዓት እስከ ዕለተ ምጽአት ሲፈጸም የሚኖር ነው::

ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ፣መሥዋዕት እንዲቀርብላቸው በቤተክርስቲያንና በመካነ መቃብራቸው እንዲጸለይላቸው ቅዱሳን ሐዋርያት /ቀኖና ሐዋርያት/ አዝዘዋል:: «በክርስቶስ አምነው ስለሞቱ ወንድሞቻችሁ ክርስቲያኖችና ሰማዕታት በቤተክርስቲያን ያለሐኬት ተሰብሰቡ፡ በቤተክርስቲያን መሥዋዕት ሠውላቸው፣ወደ ቤተክርስ ቲያን ወደ መቃብር ስትወስዱአቸውም መዝሙረ ዳዊት ድገሙላቸው::» ዲድስ ቅልያ አንቀጽ 33÷ ገጽ 481::

ነቢዩ ዳዊትም«የጻድቅ ሞቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ክቡር ነው:: ነፍሴ ሆይ ወደ ዕረፍትሽ ተመለሽ ፣ እግዚአብሔር ረድቶሻልና፣ነፍሴን ከሞት አድኖአታልና::» በማለት ሙታን በጸሎት በምስጋና በመሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር እንዲሸኙ በመዝሙሩ ተናግሮአል ::መዝ. 115÷114-7::

የቤተክርስቲያን የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ፍትሐ ነገሥትም በፍትሕ መንፈሳዊ በዲድስቅልያ የተጠቀሰውን ያጸናል:: /አንቀጽ22/:: ስለ ሙታን የሚጸለየው መጽሐፈ ግንዘትም ካህናት ለሞቱ ሰዎች ሊጸልዩላቸው፣ በመሥዋዕትና በቁርባን ሊያስቧቸው ይገባል ይላል:: ካህናት ጸሎተ ፍትሐት በሚያደርጉላቸው መሥዋዕት እና ቁርባን ስለእነርሱ በሚያቀርቡላቸው ጊዜ መላእክት ነፍሳቸውን ለመቀበል ይወርዳሉ:: ኃጢአተኞች ከሆኑ ስለ ሥርየተ ኃጢአት ይለምኑላቸዋል፡ ይማልዱላቸዋል:: ንጹሐንም ከሆኑ ደስ ይላቸዋል:: «ሰውን ለወደደው ለእግዚአብሔር በሰማያት ክብር ምስጋና ይገባል፡ በምድርም ሰላም::» እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል:: ይህም የመላእክት ምስጋናና ደስታ ስለ ሰው ልጅ ድኅንነት ነው ተብሎ ተጽፎአል::

የደጋግ ሰዎችን ነፍሳት ቅዱሳን መላእክት እንደሚቀበሏቸው በቅዱስ ወንጌል ተጽፎአል« አልዓዛርም ሞተ መላእክትም ወደ አብርሃም ዕቅፍ ወሰዱት::» ሉቃ.16÷22::

ጸሎተ ፍትሐት የሐዘን ጊዜ ጸሎት ነው:: ቅዱስ ያዕቆብ ከእናንተ ማንም በመከራ ያዘነ ቢኖር እርሱ ይጸልይ ባለው መሠረት ከመንጋው መካከል በሞተ ሥጋ የተለዩትን ምእመናን በጸሎ ትና በዝማሬ እንሸኛቸዋልን:: ያዕ.5÷13:: ጸሎተ ፍትሐት የሚደረገው ለከሀድያንና ለመናፍቃን ሳይሆን ለሃይማኖት ሰዎች ነው:: ቤተክርስቲያን ለሥርየተ ኃጢአት ጸሎተ ፍትሐተ የምታደርገው ሞት ለሚገባው ኃጢአት ሳይሆን ሞት ለማይገባው ኃጢአት ነው::

«ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፣ ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል:: ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ፡ስለዚህ እንዲጠይቅ አልልም:: ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው:: ሞትም የማይገባው ኃጢአት አለ::» 1ዮሐ.5÷16:: ለምሳሌ በተለያየ መንገድ ራሱን ለገደለ ሰው ጸሎተ ፍትሐት አይደረግም:: ምክንያቱም ቤተ መቅደስ ሰውነቱን በገዛ እጁ አፍርሷልና:: «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖራችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፡ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ::» ይላልና:: 1ቆሮ 3÷16:: እንዲሁም ለመናፍቃን ፣ ለአረማውያንም ጸሎተ ፍትሐት አይደረግም:: ምክንያቱም ብርሃን ከጨለማ ጋር አንድነት የለውምና::2.ቆሮ 6÷14::

ቤተክርስቲያን ለሰው ልጅ የማትጸልይበት ጊዜ የለም:: ሰውን ያህል ክቡር ፍጥረት ከመጸነሱ በፊት የተባረከ ጽንስ እንዲሆን እንደ ኤርምያስ በማኅፀን ቀድሰው /ኤር.1÷5/ እንደ መጥምቀ መለኰት ዮሐንስ በማኅፀን መንፈስ ቅዱስን የተመላ አድረገው እያለች ትጸልያለች:: በወሊድ ጊዜም ችግር እንዳያጋጥመው ትጸልያለች ፣ በጥምቀትም የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን ትጸልያ ለች፡ታጠምቃለች:: በትምህርት እየተንከባከበች ጸጋ እግዚአብሔርን እየመገበች ታሳድ ጋለች:: እርሷ የጸጋው ግምጃ ቤት ናትና:: በኃጢአት ሲወድቅም ኃጢአቱ እንዲሠረይ ለት ንስሐ ግባ ትለዋለች:: እንዲሠረይለትም ትጸልያለች:: በሞቱም ጊዜ እግዚአብሔር ኃጢአቱን እንዳይዝበት በደሉን እንዳይቆጥርበት ትጸልይለታለች:: እንዲህ እያደረገች የእናትነት ድርሻዋን ትወጣለች:: አንድ ሰው ሲሞት ዘመድ አዝማድ በዕንባ ይሸኘዋል:: ቤተክርስቲያን ግን ዕንባዋ ጸሎት ነውና በጸሎቷ የዚያን ሰው ነፍስ ለታመነ ፈጣሪ አደራ ትሰጣለች ፡ነፍሳቸውን ተቀበል ብላ ትጸልያለች::

ቤተክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐትን የምታደርገው ይሆናል ይደረጋል ብላ በፍጹም እምነት ነው:: ምክንያቱም ክርስቲያን እስከ መጨረሻ ተስፋ አይቆርጥምና:: «ወኵሉ ዘሰአልክሙ በጸሎት እንዘ ትትአመኑ ትነ ሥኡ:: በሃይማኖት ጸንታችሁ የለመናችሁትን ሁሉ ታገኛላችሁ::» ማቴ.21÷22 «ስለዚህ እላችኋለሁ የጸለያችሁትን ሁሉ እንዳገኛ ችሁ እመኑ ይሆንላችሁማል::» ማር.11÷24 «ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችሁማል፡ የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልገውም ያገኛል:: መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል::» ማቴ.7÷7:: «በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ::» ዮሐ.14÷13 ይላልና:: ወንጌላ ዊው ዮሐንስም በመልእክቱ «የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ:: በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው:: እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል:: የምንለምነውንም እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን::» 1ዮሐ. 5÷3 ብሏል:: እንግዲህ የቤተክርስ ቲያን ድፍረቷ ሙሴን ከመቃብር አስነሥቶ ፊቱን ያሳየ አምላክ ማቴ 17÷3:: ለእነዚህም ሳይንቃ ቸው የምሕረት ፊቱን ያሳያቸዋል የሚል ነው:: መሐሪ ይቅር ባይ ለሆነው አምላክ የሚሳነው ነገር የለምና:: ዘፍ.18÷13፣ ሉቃ.1÷37 ::

ሐዋርያው ዮሐንስ « ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ፡ ስለዚህ እንዲጠይቅ አልልም፡ »እንዳለ ቤተክርስቲያንም የምትከተለው ይኸንኑ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ዕድሜ ለንስሐ ሰጥቷቸው ከኃጢአት መመ ለስ ከበደል መራቅ፣ ንስሐ መግባት፣ ሥጋወደሙ መቀበል ሲችሉ በሕይወታችውና በእግዚአብሔር ቸርነት እየቀለዱ መላ ዘመናቸውን የሚያሳልፉ ሰዎች አሉ:: እነዚህም በራሳቸው ላይ የፈረዱ ናቸው:: ደግሞም ስሞት በጸሎተ ፍትሐት ኃጢአቴ ይሰረያልና ኃጢአትን አልተውም ማለት በእግዚአብሔር መሐሪነት መቀለድና እርሱንም መድፈር ስለሆነ ይህም ሞት ከሚገባው ኃጢአት የሚቆጠር ነው::

እንግዲህ ለበጐ የተሠራልንን ጸሎተ ፍትሐት ክብር የምናገኝበት ያደርግልን ዘንድ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን:: አሜን::

*ምንጭ:-*

*ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም:: ገጽ 20::*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ኪነ ጥበብ

## መሐንዲሱ

ከሰይፈ ገብርኤል

«አውጥተህ አውርደህ ሐሳቤን እንደተቀበልከው ተስፋ አደርጋለሁ:: » አለ ተስፋዬ በሩን ከፍቶ እየገባ :: ናቡቴ ከሚጽፈው ወረቀት ላይ ቀና ብሎ ተመለከተውና ምንም ሳይመልስለት በእጁ አጠገቡ ወደሚገኘው ወንበር አመለከተው:: ሳለፉት ሦስት ሳምንታት ሲያወጣ ሲያወርድ የነበረው ጥያቄ ስለነበረ አዲስ አልሆነበትም:: እንዴት መጋፈጥ እንዳለበት ሲያስብ ከርሟል::«አየህ ሁል ጊዜ ስታክ ከምትኖር በልተህ አብላ፣ ጉርሰህ አጉርስ፣ ጠቅመህ ተጠቀም::» ብሎታል ያኔም:: የዚህ ሕንጻ ጣጣ መቼም ጉድ ሳያፈላ እንደማይቀር በደመነፍሱ ተረድቶታል:: ግን ምን? እግዚአብሔር ይወቀው:: አሁን አሁንማ እየለመደው ስለመጣ መፍራቱና መሸበሩ ሁሉ ለቅቆ ታል:: ባለፈው የሆነውን ግን ሲያስበው ብቻውን ያስፈልገዋል::

መሐል አዲስ አበባ ላይ የሚገነባውን ሕንፃ ሥራ ለመከታተል ወደ ቦታው የደረሰው በጠዋቱ ነበረ:: 4ቱ ፎቅ ተጠናቆ የቀረው 2ቱ የ6ወር እድሜ እንደሚበቃው ኮንትራክተሩ ነግረውታል:: ሥራውን ይከታተል የነበረው መሐንዲስ ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ከሄደ በኋላ ነበር እርሱን ተክቶ እንዲሠራ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ያዘዙት:: «የዚህ ሕንፃ ጥሩም ሆነ መጥፎ መሆን የድርጅታችንን የወደፊት ዕድል ይወስነዋል» ነበር ያሉት አለቃው::«ጥሩ ሥራ መሥራት ቢያንስ ቢያንስ ከኅሊና ፍርድ ነፃ ያደርጋል» ይላሉ ደጋግመው :: «ምን ከኅሊና ፍርድ ብቻ ከእግዚአብሔርም ፍርድ ጭምር እንጂ» ብሎ ነበር ለራሱ:: ያን ጊዜ::

ሥራውን እያጠና ከትንሽ ጀምሮ በደረጃ ወደላይ መውጣት ሲጀምር ግን በልቡናው አንድ ቅር የሚያሰኝ ነገር እየተፈጸመ እንዳለ ታወቀው :: የሕንፃው መሠረት መቆፈረ ያለበትን ያህል አልተቆፈረም:: በዲዛይኑ መሠረትም አልተሠራም:: የሕንፃው ዋስትና የሆነው መሠረቱ ካልፀና ሁሉም ባዶ ነው:: በአሸዋ ላይ የተገነባ:: የመሠረቱን ጥልቀት ለመመርመር 'ይቆፈር' የሚለውን ጥያቄ ባነሣ ጊዜ በሰዎች ፊት ላይ ያነበበው ጥላቻና ቁጣ በኋላ የሚመጣውን የባሰ ነገር አመለከተው::

«ኢንጂነር ናቡቴ መሠረቱን ቆፍሬ ማየት አለብኝ ብለሃል» አሉ የኰንስ ትራክሽን ድርጅቱ ባለቤት አቶ ካብት ይመር:: በእጃቸው የያዟትን ቁልፍ እያሽከረከሩ

«አዎ»

«ይህንን ለማለት ያነሣሣህ ምንድር ነው? ይህ ሥራ እኮ የመጀመሪያዬ አይደለም:: ገና አንተ ሳትወለድ ጀምሮ የነበርኩበት ፣ ጥርሴን የነቀልኩበትና ያረጀሁበት ሥራ ነው::» «አውቃለሁ::» አላቸው ወደርሳቸው ሳይዞር:: አጭር መልስ የሚመልስ ሰው በጣም ነው የሚያናድዳቸው:: የትዕቢተኛ አንዱ መለያ መልሱ ነው ባይ ናቸው:: «እና ትናንትና በተቋቋመው የምክር አገልግሎት በሚሰጥ ድርጅታችሁ መሠረቱን ለማየት ቆፍሩ መባላችን ስድብ መሆኑን አላወቅህም?

« ስድብን ምን አመጣው:: ሥራ ነው:: »

የዚያን ዕለቱ ውይይት በዚህ አበቃ:: ነገር ግን ሰውየው መላልሰው ከእግር እስከራሱ እያዩ ለፋሲካ ገበያ እንደቀረበ ጠቦት በግ ገመቱት:: ብዙ ጊዜ ቢጠይቁትም አሻፈረኝ በማለቱ ሌላ ዘዴ ማፈላለግ ያዙ:: እናም ተስፋዬ ተገኘ:: ሐሳቡን ካስለወጠው ጠቀም ያለ ጉርሻ እንደሚሰጠው ቃል ስለተገባለት የድሮ ጓደኝነቱን ለማደስ የሻይ ሰዓቱን በሙሉ ለዚህ አዋለው:: «ከልጅነቱ ጀምሮ አውቀዋለሁ:: ያመነበ ትን ነገር ካላሳካ ወደኋላ የማይል ግትር ነው::»ሻይ ጠጥተው ከተለያዩ በኋላ ለብቻው ያጉተመተማት ቃል ናት::

«ምን ይሻላል እባክህ ?ይሄ ወጠጠ ጓደኛህ አስቆፈረው አይደል? መሠረቱ ጥልቀት እንደሌለው ስለተረዳ ጉድ ነው የሚያፈላብን::»አሉ አቶ ካብት ይመር አገጫቸው ላይ ረዘም አድርገው ያሳደጓትን ጢማቸውን እያፍተለተሉ::

«ትንሽ ይፈራ እንደሆን ብዬ መሠረቱን እመለከታለሁ ብለህ ስታስቆፍር....» ጀመረ ተስፋዬ:: ብልጣብልጥ ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ «ሕንጻውን ቢጐዳ ተጠያቂ ነህ ብየው ነበር:: ነገር ግን መንቻካ ስለሆነ የፈለገው ይመጣ ብሎ አስቆፈረው:: «ታዲያ አሁን ምን ይሻላል?» ትዕግሥት አጥተዋል ሰውየው:: እንደተለመደው አፉን በገንዘብ መያዝ ነዋ!» ትልቅ ሐሳብ « ጥሩ 50.000ብር እንደምንሰጠው ንገረውና አግባባው፤ ይኼ አንድ ሺህ ብርም ቆጥሮ የማያውቅ ጐረምሳ ልቡ ቀጥ ነው የምትለው::» በረጅሙ ሳቃቸውን ለቀቁት:: እንዲህ የሚያደርጉት የሚቀናቀናቸውን ጠላት ድል ያደረጉ ዕለት ነው:: ተስፋዬም አብሯቸው አገጠጠ:: ጥቅም ካለበት ከሳቀው ጋር ይስቃል፤ ማልቀስ ካለበትም ያለቅሳል:: አሁንም የጥንት ጓደኛውን አግባብቶ ሐሳቡን በማስለወጥ የሚያገኘውን ብር ሲያስብ ልቡ የሐሴት ከበሮ ትደልቅ ገባች :: «እሺ ልጅ ናቡቴ ..» በዓይኑ ወጉን ጀመረ:: «መልስህን አልነገርከኝምኰ::» ናቡቴ በተራው ፊቱን በጥንቃቄ ያጠናው ነበር:: አብሮ አደግ ጓደኛውን፤ ወዛም ፊቱ በቅባት ተጥለቅልቋል:: በስብ የተሞላው አንገቱ እንደ ከረባቱ ለመንጠልጠል ደርሷል:: ፊቱን በነጭ መሐረቡ ሲያደራርቅ በጣቶቹ ላይ ያሉት ወርቆች ይንቦገቦጉ ጀመር:: በቀኝ እጁ ላይ የወርቅ አምባር አሥሯል:: የፀሐይ ጨረር ባገኙ ቁጥር የሚንተገተጉት የወርቅ ቀለበቶቹ ለተወሰኑ ደቂቃዎችም የሰውን ዓይን ይሰርቃሉ:: ሥራ የጀመሩት አንድ ጊዜ ቢሆንም አሁን ለተመለከታቸው ግን አሠሪና ሠራተኛ ጌታና ሎሌ እንጂ ጓደኛሞች አይመስ ሉም:: ለብዙ ዓመታት የገንዘብ ምንጩ ከየት እንደሆነ እየገረመው ሲያስብ ቆይቷል:: ዛሬ ግን ወዛም ግንባሩ ላይ በጉልህ እንደተጻፈ ሁሉ ቁልጭ ብሎ ታየው «ከእያንዳንዱ ሀብት ጀርባ ወንጀል አለ» የሚለውን ቃል ያስነበበው ማን ነበር? ትክክለኛነቱ አሁን ተከሰተለት:: «ትሰማኛለህ ተስፋዬ ሐሳቤን አንድ ጊዜ የገለጥኩልህ መሰለኝ::»

«አይ ናቡቴ ያልጅነትሽ አሁንም አልለቀቀሽም ::» ነገሩን በሁለት አብሮ አደጐች መካከል የሚደረግ ውይይት መሆኑን ለማሳየት ነጫጭ ጥርሶቹን ብልጭ እያደረገ ማግባባቱን ቀጠለ:: «እስኪ ንገረኝ 50,000 ብርን ያህል ዕጣ ሳይጣል የወጣ ሎተሪ እንዳትቀበል ያደረገህ ነገር ምንድር ነው? በአንተ አልተጀመረ:: ይሄ ሁሉ የምታየው ሀብታም ከዜሮ ተነሥቶ ሲመነጠቅ:: ትናንትና በእግሩ ካንተ ጋር ሲኳትን የነበረ ዛሬ ባለመኪና ሲሆን ፣ የቀበሌና የግለሰብ ቤት ውስጥ መኖር ሰልችቶት የነበረው ባለቪላ ሲሆን ፣ምሥጢሩ ምንድ ነው? ብለህ ጠይቀህ ታውቃለህ? አንተ አንዲት ትንሽ ቤት ሠርቶ መጨረስ አቅቶህ ስትንገታገት ጓደኞችህ ባለስንት ሀብት ሆነዋል:: እስኪ ንግረኝ? አንተ ከእነርሱ በምን ትለያለህ:: »

ቀስብሎ በማስረዳት የጀመረውን በስሜት ተውጦ በማብራራት ፈጸመው:: የቅድሙ ፈገግታው አሁን የለም:: አምርሯል ማለት ነው:: «እውነቱን እኮ ነው? ሲል አሰበ ናቡቴ « የጓደኞቼ ኑሮና የእኔ ሕይወት አይመጣጠንም:: አንድ ልብስ ሳልቀይር ብዙ ጊዜ ሆኖኛል:: እነርሱ ግን ዛሬ የለበሱትን ነገ አይደግሙትም:: አንዲት ቤት መጨረስ አቅቶኝ ስጨነቅ እነርሱ ለዘመዶቻቸውም የሚተርፉ ሆነዋል:: የዚህ ሁሉ ምንጩ መቼ ደሞዛቸው ሆነና:: እውነቱን ነው:: እኔ ከእነዚህ ለምን እለያለሁ» የጓደኛው ኅሊናን የሚነካ፣ ልብን ሰርስሮ የሚገባ ንግግር ለዘመናት ገንብቶት የቆየውን የታማኝነት ምሶሶ ለመፈንገል ሲያነቃን ቅበት ተሰማው::

« አየህ ናቡቴ...» ቀጠለ ጓደኛው:: « ለመቀበል የጨነቀህ ለምን እንደሆነ ይገባኛል:: ከልጅነትህ ጀምሮ የኖርከው በቤተክርስቲያን የቄሶችን ዘኬ እየበላህ ስለሆነ...» ያደገበት የልጅነት ሕይወቱን በጣፋጭ አንደበቱ ይተርክለት ገባ::

ናቡቴ ገ/ሚካኤል ተወልዶ ያደገው መሐል አ/አ ቢሆንም ሕይወቱ ግን የተቆራኘው ውዳሴና ቅዳሴ ከማይጠፋበት፣ትርጓሜ ከመዝሙሩ ከተስማማባት የበአታ ለማርያም ገዳም ነው:: እዚያ ነው ፍካሬ ዘጻድቃን....ብሎ ዳዊት የደገመው:: እዚያ ነው ሰላም ለኪ... ብሎ ጀምሮ ውዳሴ ማርያምን የተማረው:: የሊቃውንቱ ሃይማኖት፣ የሚያስተነትኑት ምሥጢር፣ ትኅትናቸው በሙሉ ዛሬም በልቡ ጽላት ተቀርጾ ቀርቷል:: እነርሱ ሳይተርፋቸው ያላቸውን አጉድለው ለሌ ላው ሲሰጡ ፣





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከራሳቸው ገፍፈው ለሌ ላው ሲያለብሱ አይቷል። እንደ ሥጋ አባትም እንደ መንፈሳዊ መምህርም ገርተው ያሳደጉት መምሬ ገ/ሚካኤል « አየህ የእኔ ልጅ ክርስትና ማለት ይህ ነው። በአንደበትህ ሳትናገር በሕይወትህ የምታስተምረው። ይህ ፍቅርና መተሳሰብ ነው አሕዛብን ድል አድርጎ ከአረማዊነት ወደ ክርስትና የመለሳቸው።» ይሉት ነበረ። ያ ቃላቸው ዛሬ ግዙፍ ገዝፎ በኅሊናው ጓዳ ተመላለሰበት።

ሙሉ ሱፍና ከረባት ለብሶ ከተቀመጠው ጓደኛው ጀርባ አዳፋ ካባን የደረበውን፣ በኑሮ ጉስቁልና ፣ በዕድሜ ብዛት የደከመውን የመምሬ ገ/ሚካኤልን ሰውነት በሐሳብ ተመለከተ። «አየህ ናቡቴ የሰው ዕንባ ጥሩ አይደለም። አንድ ቀን ባሕር ሆኖ ያሰምጣል። በሐሰት የተገኘ ገንዘብም ከፍለው የማይጨርሱት ዕዳ ነው። በሰው ዘንድ ቢዘነጋም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን አይረሳም። ስለዚህ መማለጃ፣ እጅ መንሻ አትቀበል። » በሞት አፋፍ እያሉ የተናገሩት የኑዛዜ ቃላቸው በጓደ ኛው በተስፋዬ አንደበት ተሸርሽሮ እንዳ ይናድ ፈራ።

ተስፋዬ በነጎድጓዳማ ድምፁ የራሱን ታሪክ ተርኮለት ሲያበቃ «...እና ናቡቴ ይህ የአባትህ ቃል እንደሚያስ ጨንቅህ አውቃለሁ። ግን አልሰረቅህ ፣ አልዋሸህ፣ ሰዎች አምጥተው የሰጡህን ብትቀበል ኃጢአቱ ምንድን ነው? »እያለ ማግባባቱን ገፋበት። «ይህማ ኃጢአት ነው ተስፋዬ! ጭራሽ ላደርገው አልችልም» «ለምን ? ለምን ? በምታገኘው ገንዘብ አትጠጣበት፣አትስከርበት፣አታመነዝርበት፣ ቤትህንና ትዳርህን የምትወድ መሆንህ የታወቀ ነው። ሌላው አጫሹና ጠጪው ወስዶ ከሚጠቀምበት አንተ ቁም ነገር ላይ ብታውለው ክፋቱ ምንላይ ነው?»

የተስፋዬ ፈጣን ቃላት ናቡቴን ጸጥ አደረጉት። በያዛት ብዕር ጠረጴዛውን ቢቆረቁርም መልስ አላገኘም። ልቡ ግን ወደ ጓደኛው ሐሳብ ሲሸፍትበት ይታወቀዋል። «አዎ ይህንን ብር ወስጄ ብጠቀምበት እንዴት ኃጢአት ሊሆን ይችላል?» ብዙ ሐሳቦች ተፈራረ ቁበት። የናቡቴን ዝም ማለት ሲመለከት ለድል መቃረቡን ስለተገነዘበ ተስፋዬም አሳማኝ ናቸው ያላቸውን በጥቅስ የተሞሉ ንግግሮች ማውረድ ጀመረ።

« እኛም እኮ ክርስቲያኖች ነን ። ግን እምነት በልብ ነው እንጂ በአፍ መቼ ሆነና! ደግሞ ከምታገኘው ገንዘብ የተወሰነ ውን ለቤተክርስቲያን ብታውለው «በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ » ይሆናል።»

ንግግሩ በተጠናው መሠረት ስለሄደለት እየተደሰተ የናቡቴን መልክ በጥንቃቄ አጠናው ።ግንባሩን እጁ ላይ አስደግፎ ይቆዝማል። «ለመወሰን ተቸግሯል ማለት ነው» አለ በልቡ። ኃጢአት እስኪጀምሩት በጣም ያስጨንቃል ። አንዴ ከገቡበት በኋላ ግን ውጡ ውጡ አይልም። ይጥማል። ጨው እየላሰ ወደ መታረጃው እንደሚነዳ በሬ ቢላዋው ይረሳል።ሔዋን እግዚአብሔርን ያህል ጌታ፣ ገነትን ያህል ቦታ እንደምታጣ ....5500 ዘመን በሲዖል እንደምትማቅቅ ብታስተውል መቼ እጇን ወደ እጸበለስ ትዘረጋ ነበር። ንግሥተ ሰማይ ወምድርነ ትን ስትፈልግ ንግሥተ ምድርነትንም አጣች። የሔዋን ጥያቄ ....የአዳም ፈተና ....እጅን ወደ በለስ የመዘርጋት ወይም ያለመዘርጋት ፈተና ....ዛሬ ደግሞ ለናቡቴ... ከተቆረጠ በኋላ ግን የለሁበትም የማለት ፈተና... ሐሳብ ....«ብሉ» ብቻ በኋላ ግን..።

50,000 ብሩን ቢቀበል የጀመረውን ቤቱን ሙሉ በሙሉ ያለምንም ችግር ይፈጽማል። ለቤቱ ሥራ ይቆራረጥ የነበረው ደሞዙም መሥመር ይይዛል። በቅርቡ ሚስቱ አነስተኛ ሥራ በመጀመሯ ችግሩን እንዳቃለለችለት ዛሬም ይህንን ብር ካገኘ ደግሞ የበለጠ ኑሮው የተረጋጋ ይሆናል ። ይገርማል። የዚህች ምድር ሕይወት በእውነትና ስለእውነት በመሥራት የሚስተካከለው መቼ ነው? እውነት ውሸትን አሸንፋ፣ እውነተኞች በሐሰተኞች ላይ ሠልጥነው የሚኖርበት ዘመን መቼ ይመጣ ይሆን ? ይህንን ሁሉ ጥያቄ በኅሊናው ለማውጣትና ለማውረድ አሁን ጊዜው አይደለም። ጥያቄው ዓይንን ጨፍኖ ለግል ጥቅም ተሸንፎ እያዩ እንዳላዩ፣ ሰምተው እንዳልሰሙ መሆን ወይም ለእውነት ቆሞ ይሉኝታንና ምድራዊ ሀብትን ድል መንሣ...ት ምርጫ ...ውሳኔ ...ወደሚበልጠው ማድላት።

«ልጅ ናቡቴ፣ በዚህ ሐሳብ ከተስ ማማህ ሰውየው ያዘጋጁልህ ሌላም ትልቅ የምሥራች አለልህ? »አለው ተስፋዬ ዓይኑ ሁሉ ጥርስ ሆኖ። ናቡቴ «ምንድን ጉድ መጣ» በሚል አስተያየት ቀና ብሎ ተመ ለከተው። « ባለቤትህን አሁን ካለችበት ሥራ ወደተሻለ ለመቀየር፣ ደሞዟንም በእጥፍ ለማሳደግ ቃል ገብተውልኛል።»

ወይ ጉ......ድ ለካስ ይኼም አለ። የባለቤቱ የደሞዝ እስትንፋስ የተያዘው በአቶ ካብት ይመር መዳፍ ነው። ይህ አጓጊ ሹመት ሌላ መልእክትም አለው« እምቢ ብለህ በሐሳብህ ብትገፋ ሚስትህን ከሥራዋና ከደሞዟ አፈናጥሬ ሜዳ ላይ እጥላታለሁ» የሚል። ታዲያ የቱን ይምረጥ። ጭንቅ ።

★ ★ ★

«እና ምን ብለህ መለስከው?» በጥያቄ ውስጥ ፍርሃት ....አግኝቶ የማጣት ስሜት ...ተስፋ መቁረጥ.. ሁሉንም በአንድ ጊዜ ያነበበ መሰለው። ምን ታድርግ ለብዙ ጊዜያት ጠፍቶ የነበረ በተስፋዬ አማካኝነት በብዙ ውትወታና ልመና የተገኘ ሥራ አሁን በአንድ ጊዜ የሕልም እንጀራ ሲሆን እየታያት ብትጨነቅ እውነት አላት። የእርሱም ልብ ከሚስቱ ልብ ጋር እሳት ውስጥ እንደገባ ጅማት ኩምትር ሲል ተሰማው። «ናቡቴ ....ምን አልከው ታዲያ ? በእኔ ሥራና በኑሯችን ፈርደህ አባረርከው?» እያንዳንዷ ሴኮንድ ባለፈች ቁጥር የዓይኗ እርጥበትም ይጨ ምር ገባ።

«ምንም አላልኩትም። አስቤ እነግርሃለሁ ብዬ አሰናበትኩት።» «ተስፋዬ እኮ አብሮ አደግህ ብቻ አይደለም። ባለውለታህም ጭምር ነው። ስለዚህ ለአንተ አስቦ ያደረገውን ነገር ገፍተህ ጥሩ ጓደኛህን ማሳዘን የለብህም። »

«አንቺም እንደዚህ አልሽኝ? ለገንዘብና ለክብር የሸፈተውን ልቤ,ን መል ሰሽ ጣፋጩን ሐሰት ትቼ መራራውን እውነት እንድጠጣ ታግዢኛለሽ ብዬ ነበር»

ከዚያ በኋላ የሚናገር ጠፋ። ቤቱ አስከሬን እንደወጣበት ሁሉ ፀጥ አለ። በይ እንጂ ምን ልበለው!

በአንደበቷ መልሷን ከማቅረቧ በፊት ዕንባዋ ቀደማት « የምትወደኝ ከሆነ ቃሌን ተቀበል።» ተስፋዬ የጣለባትን አደራ የምትወጣበት ሰዓት አሁን ነው። በብዙ አግባቢ ቃላት ነገ ልትኖረው የምትችለውን የደስታ ሕይወት አሳይ ቷታል። ያንን ደግሞ ማጣት አትፈ ልግም። ከሥራዋ እንዳትፈናቀል ብቻ ሳይሆን የቀረበላትን ገንዘብም ማለፍ አልፈለገችም። «አልቅሺበት ፣ እፈታሃለሁ በይው። ስለሚወድሽ ያልሽውን ያደርጋል። ኃጢአት ነው እያለ ሙጭጭ ካለብሽም በኋላ ንስሐ እንገባለን በይው። » በዚህ ተስማምተው ተለያዩ። እናም አሁን ሰዓቱ ደረሠ። ዕንባዋንና ፍቅሯን ተጠቅማ ሐሳቡን ማስለወጥ አለባት።

«ናቡቴ ተመልሼ ወደ ችግርና ሥራ ፈትነት መግባት አልፈልግም። የእኔን እጅ የሚጠብቁ ወላጆቼንም መር ዳት አለብኝ። በአንተ ደሞዝ ደግሞ ይህንን ሁሉ ማድረግ አንችልም። የምትፈልገኝ ከሆነ ቃሌን ተቀበል።

ዛሬም ደሊላዎች ....ደሊላዊ ቃሎች ...ሶምሶኖችንና ሶምሶንነታቸውን ይፈታተናሉ። ሌላ ምርጫ.... ሚስት.... ትዳር... ገንዘብ ....እውነት... ፈተናዎችና ምርጫዎች ሆነው ቀረቡ።

«እንደምወድሽማ ታውቂያለሽ። በቤተክርስቲያንና በእግዚአብሔር ፊት የሰጠሁት ቃል ነው። »

«የምትወደኝ ከሆነ ተስፋዬ ያለህን ሐሳብ ተቀበል!»

«ያ ሕግ እንዴት ይሆናል? ኃጢአት እኮ ነው።»

«ንስሐ እንገባለን።»

«ወግቶ ይማርህ እንደማለት ።»

« አለበለዚያ አትወደኝም ማለት ነው። ስለዚህ ምርጫህን አስተካክል፣ ወይ እኔን ወይ ግትር ሐሳብህን! » በሩን በኃይል ደርግማው ወጣች።

★ ★ ★

«ሃሎ ነብሩ አምልጧል። ወጥመዱ በደንብ አልያዘውም ።»ተስፋዬ የናቡቴን መልስ ከሰማ በኋላ በጉጉት ለሚጠብቁት ሰዎች ያስተላለፈው መልእክት ነበረ። መልእክቱ እንደ ደረሰ አቶ ካብትይመር በንዴት ጦፈው ጠረጴዛቸውን በቡጢ ደለቁት።«ይኼ የውሻ ልጅ 50.000ብሬን አልቀበልም ብሎ በቸርነት የተዘረጋ እጄን በትዕቢት ነከሰው። እርሱም ገንዘቡን አይበላ እኔም ሕንፃዬን አላፈርስ!»ከዚያ በኋላ በገንዘብና በሚስቱ ዕንባ፣ በሥራዋና በደመወዟ በስም ምንት አልያዝ ላለው ነብር ሌላ ወጥመድ መሞከር የግድ ሆነ ። በብዕራቸው ጠረጴዛቸውን ሲቆረቁሩ ቆይተው ቀና ሲሉ የተስፋዬ ዓይን እርሳቸው ላይ ተተክሎ ነበር ።

«ምን ትላለህ ታዲያ? »

ተስፋዬ በላይ በላይ ሲጋራውን እያጨሰ መናገር መፈለጉን ለማሳየት ጉሮሮውን ጠራረገና «ይኼ ለብዙ ዘመ ናት የተሠራውን ሥራ በሙሉ የሚያፈ ርስ ነገር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በመሆኑ በጊዜ መቀጨት ያለበት ይመስለኛል::»

«እርሱማ ሁላችንም ብለናል::» የግምባራቸው መታረስ በንዴት መቃጠላቸውን ያሳያል:: «ችግሩ እንዴት? የሚለው ነው »:: «ይኼንን ጉረምሳ ከመንገድ ለማስወገድ ለአንዴና ለመጨረ ሻም ጊዜ ማራቅ አልያም ከዚህች ምድር ማሰናበት ነው መፍትሔው::»

«እንዴት ?» አቶ ካብትይመር ቁርጥ ያለ መልስ እንጂ ዙሪያ ጥምጥም መሄድ አይወዱም::«ለምሳሌ » ቀጠለ ተስፋዬ «ለምሳሌ በጉቦ ስም ወደ ወኅኒ ማስወርወር ወይም በቴክኒክ ብልሽት ምክንያት የመጣ አስመስሎ ሥራው ቦታ ላይ አደጋ ማድረስ» አቶ ካብትይ መር ከዚህ ችግር ማምለጫ ትንሽ ቀዳዳ መኖሩን ሲመለከቱ በረጅሙ ተነፈሱ:: ዕድሜ ዘመናቸውን በሙሉ ያሳለፉበትን ከቢሮ ቢሮ የተንከራተቱበትን፣ ግማሹን በጉቦ ሌላውንም በተንኮል አስወግደው ታላቅ ዝናና ክብርን ያገኙበ ትን የሥራ መስክ በአንድ ጊዜ ማጣት ለርሳቸው ሞት ነው:: በመጨረሻም በልዩ ዘዴ ጠላትን ማጥቃት የሚለው ሐሳብ ተቀባይነት አገኘ::

«ሶስናን ከረበናት እጅ ያዳነ እግዚአብሔር እንኳን ከታሰበ ከተወረወ ረም ያድናል!»

ከፊታቸው የተሰበሰቡትን ምእ መናን በተመስጦ የሚያስተምሩት አባት ቃል በልቡ ተስላ ቀረች::«እንኳን ከታሰበ ከተወረወረም የሚያድን አምላክ » አለ ለራሱ:: ጸሎቱን አድርሶ አምላከ ቅዱስ ሚካኤል እንዲታደገው ለምኖ ቀጥታ የተጓዘው ወደ ሕንፃው ቦታ ነበር:: «ሃሎ ነብሩ ወደ ወጥመዱ እየመጣ ነው :: ሥራህን ትሠራለህ::»

«እሺ !»

የታአር ክሬኑ ኦኘሬተር አሥር ጊዜ «አምላኬ ይቅር በለኝ የሚለውን ቃል በልቡ እየደገመ »የመጨረሻውን ትእዛዝ ይጠብቅ ገባ:: እኔ ምን ቸገረኝ ኃጢአቱ ይህንን ባሰቡት ላይ እንጂ በእኔ ላይ አይደለም::»እንደ ጲላጦስ እራሱን ነፃ ለማድረግ ከኅሊናው ጋር ሙግት ያዘ :: በሕንፃው ውስጥና ዙሪያ የነበረው ሠራተኛ ሁሉ አሁን የለም:: አካባቢው ያለወትሮው ጸጥ ብሏል:: ናቡቴ አንዳች ነገር ጀርባውን የጨመደ ደው መሰለውና ዞር አለ:: ታወሩ ብቻ ይንቀሳቀሳል፣ ክብድ... ክብድ... ክብድ... ክብድብድ..... ክብድብድ..... ብድብድ ያለ ቀን::

«ሃሎ! ነብሩ ወጥመድ ውስጥ ገብቷል»

ግ... ግ... ግ... ግ... ግ...

ድንጋይ ወደምድር እንደ ሰዶም እሳት ዘነበ ::

ጩኸት... እሪታ... ዋይታ...

/ይቀጥላል/

# ሰባት ነገሮች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እና በቤተክርስቲያናችን ትምህርት በሰባት ቁጥር የታወቁ ብዙ ነገሮች አሉ:: ለዛሬ በማስታወሻችን ከያዝናቸው ሰባት ነገሮች መካከል የሚከተሉትን እንመልከት::

ሰባት ቁጥር በዕብራውያን ዘንድ ፍጹም ቁጥር ነው:: ምሳ.24÷16:: እግዚ አብሔር ከሰኞ እስከ እሑድ ያሉትን ቀናት በሰባት ቁጥር ወስኗቸዋል:: ዘፍ. 2÷2:: ሕዝበ እሥራኤል ከግብፅ ባርነት ነፃ ወጥተው በሲና በረሃ ሲጓዙ ይመሩ የነበሩት በሰባት ደመና እንደነበር የቤ ተክርስቲያናችን ትምህርት ያስረዳናል:: ዘጸ 13÷21 እና 22 1ኛ ቆሮ.10÷2::

## ሰባቱ አባቶች የሚባሉት

1. ከሁሉ በላይ የሚሆን ሰማያዊ አባታችን ልዑል እግዚአብሔር ነው:: ሚል.1÷10፣ማቴ.6÷9::
2. የንስሐ አባት::/የነፍስ አባት::/ ማቴ. 18÷18 ፣ ዮሐ. 20÷23::
3. ወላጅ አባት መዝ.102÷13::
4. የክርስትና አባት:: ሉቃ. 2÷25-28::
5. የጡት አባት:: የጡት አባት የሚባ ለው ያልወለደውን ልጅ እንደ ልጁ አድርጐ፣ከእግዚአብሔር በረከት ለማግ ኘት ሲል እንደእናትና አባት የሚያሳ ድግ አባት ነው::
6. የሥልጣን አባት /የቆብ አባት/ ፣ /የቆብ አባት ሚባለው ዲያቆናትን፣ ቀሳውስትን እየሾመ የሃይማኖት ልጆቹ እንዲሆኑ የሚያ ደርግ ነው:: /በተለይ ጳጳሳትን ያመ ለክታል::/ የሐዋ.6÷16 የሐዋ.13÷1-3::
7. የቀለም አባት ፣ የቀለም አባት የሚባለው የቅዱሳት መጻሕፍትን ንባ ብና ትርጓሜ አስተምሮ ደቀመዛሙ ርቱን በሃይማኖት የሚወልድ አባት ነው:: 2ኛ.ጢሞ.3÷12-17::

## ሰባቱ ሰማያት

ሰባቱ ሰማያት የሚባሉት ከላይ ወደታች ሲቆጠሩ

1. ጽርሐ አርያም - ከሰማያት ሁሉ በላይ ያለች ሰማይ በመሆኗ ሰማየ ሰማያት ወይም የሰማዮች ሰማይ በመባል ትታ ወቃለች:: ዘዳ.10÷13-14:: 1ኛ ነገ 8÷27::
2. መንበረ መንግሥት:- መንበረ መን ግሥት ሌሎች ሦስት ስሞች አሏት:: መንበረ ብርሃን፣ መንበረስብሐት፣ መንበረ ጸባዖት በመባልም ትታወ ቃለች:: በዚህች ሰማይ ላይ ምስጋና የባሕርይ የሆነ አምላክ ይመሰገንባ ታል:: ለወዳጆቹ ቅዱሳንም እሱ በወደ ደው መልኩ ይገለጽባታል:: ሕዝ.1÷ 26፣ ኢሳ 6÷1:: ራእ 4÷2::
3. ሰማይ ውዱድ :- ይህ ሰማይ በኪሩቤል ጀርባ ላይ የተዘረጋና ለመንበረ መንግሥት እንደ አዳራሽ ወለል ሆኖ መንበረ መንግሥት እንደ ዙፋን የተዘረጋበት ሰማይ ነው:: ሕዝ.1÷22-23::
4. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት:- የዚህች ሰማይ ሌላ ስሟ መንግሥተ ሰማያት ነው:: ክርስቲያኖች ሁላችን ተስፋ የምናደርጋትና በዘለዓለም ሕይወት የምንኖርባት ሰማይ ነች:: ገላ.4÷ 26፣ ዕብ.12 ÷12፣1ኛ.ቆሮ 2÷9፣ ራእ. 21÷2-15::
5. ኢዮር
6. ራማ
7. ኤረር :- እነዚህ ሦስቱ ሰማያት መላእክት በየነገዶቻቸው የሚኖሩባ ቸው ሰማያት በመሆናቸው የመላእ ክት ከተሞች በመባል ይታወቃሉ:: 2ኛ ቆሮ.12÷2::

## ሰባቱ «እኔ ነኝ»

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር በዮሐንስ ወንጌል ላይ የተጻፉት /እኔ ነኝ / ብሎ የተናገራቸው ቃላት የሚከተሉት ናቸው::

1. የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ:: ዮሐ. 6÷35::
2. የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ:: ዮሐ.8÷12::
3. እኔ የበጐች በር ነኝ.::ዮሐ.10÷17::
4. መልካም እረኛ እኔ ነኝ:: ዮሐ. 10÷11::
5. ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ:: ዮሐ. 11÷25::
6. እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ :: ዮሐ.14÷6::
7. እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ:: ዮሐ.15÷1::

## ሰባቱ ሊቃነ መላእክት

ሰባቱ ሊቃነ መላእክት የሚባሉት

1. ቅዱስ ሚካኤል
2. ቅዱስ ገብርኤል
3. ቅዱስ ሩፋኤል
4. ቅዱስ ራጉኤል
5. ቅዱስ ዑራኤል
6. ቅዱስ ፋኑኤል
7. ቅዱስ ሳቁኤል ናቸው::

ራእ.4÷5:: ሄኖ.6÷1-8:: ሄኖ.10÷12-16:: ይሁዳ ቁ. 9

## ሰባቱ አጽርሐ መስቀል

ሰባቱ አጽርሐ መስቀል የሚባሉት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤዛ ዓለም በደብረ ቀራንዮ፣ በዕለተ አርብ ፣በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የተናገራቸው ቃላት ናቸው::

እነርሱም:-

1. አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ? ማቴ.27÷46::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

2. አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁ ምና ይቅር በላቸው:: ሉቃ. 23÷34::
3. እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ:: ሉቃ.23÷43::
4. አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ ፣እናትህ እነኋት:: ዮሐ.19÷27::
5. ተጠማሁ:: ዮሐ 19÷29::
6. ተፈጸመ:: ዮሐ.19÷30::
7. አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰ ጣለሁ ::ሉቃ. 23÷46::

## ሰባቱ ተአምራት

ሰባቱ ተአምራት የምንላቸው ጌታ በተሰቀለ ጊዜ የተፈጸሙትን ተአምራት ነው:: ከእነዚህም ሦስቱ በሰማይ፣ አራቱ ተአምራት ደግሞ በምድር የተፈጸሙ ናቸው ::እነርሱም:-

1. የፀሐይ መጨለም፣
2. የጨረቃ ደም መሆን፣
3. የከዋክብት መርገፍ /የብርሃናቸው መራቆት/፣
4. የዐለቶች መሰንጣጠቅ፣
5. የመቃብራት መከፈት፣
6. የሙታን መነሣት፣
7. የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከሁለት መቀደድ ናቸው:: ማቴ.27÷51-54፣ 23÷44-46::

## ሰባቱ የሚጠሉ ነገሮች

1. ትዕቢተኛ ዓይን፣
2. ሐሰተኛ ምላስ፣
3. የንጹሕን ደም የምታፈስ እጅ፣
4. ክፉ ሐሳብን የሚያፈልቅ ልብ፣
5. ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር፣
6. በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር፣
7. በወንድማማች መካከል ጠብን የሚያ ፈራ ፣ምሳ.6÷16-19 ናቸው::

## ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት

ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የሚባሉት:-
1. የኤፌሶን ቤተክርስቲያን፣
2. የሰርምኔስ ቤተክርስቲያን፣
3. የጴርጋሞን ቤተክርስቲያን፣
4. የትያጥሮን ቤተክርስቲያን፣
5. የሰርዴስ ቤተክርስቲያን፣
6. የፊልድልፊያ ቤተክርስቲያን፣
7. የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ናቸው::

## ሰባቱዲያቆናት

7ቱ ዲያቆናት ብለን የምናነሣቸው በዘመነ ሐዋርያት የነበሩ ክርስቲያኖችን እንዲያስተዳድሩ በ12ቱ ሐዋርያት ጸሎት የተመረጡትን ነው:: እነርሱም:-
1. ቅዱስ እስጢፋኖስ፣
2. ቅዱስ ፊልጶስ፣
3. ቅዱስ ጵሮኮሮስ፣
4. ቅዱስ ኒቃሮና፣
5. ቅዱስ ጢሞና፣
6. ቅዱስ ጳርሜና፣
7. ቅዱስ ኒቆላዎስ ናቸው:: የሐዋ 6÷3-6

## ሰባቱ ራሶች

ሰባቱ ራሶች የምንላቸው በራእየ ዮሐንስ ስለሐሰተኛው ክርስቶስ በሚናገር በት ክፍል ላይ« የአውሬው ሰባት ራሶች አሉት» ተብለው የተገለጹትን እነርሱም ሐሳዊ መሲሕ ወደ ዓለም ሲገለጽ ለመ ጀመሪያ ጊዜ እሱን አምላክ ነው ብለው አምነው ከርሱ የሚያብሩ አገሮች ናቸው:: እነዚህም በቤተክርስቲያን ትምህርት የታ ወቁ ናቸው::
1. ኢራን ፣
2. ኢራቅ፣
3. ግሪክ፣
4. ሜዶን/2ኛ.ነገ 17÷6/፣
5. ግብፅ፣
6. ጣሊያን፣
7. እሥራኤል ናቸው::

## ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት

ክርስቲያኖች በቀን ውስጥ ጸሎት የሚያ ደርጉባቸው የታወቁ ሰባት ጊዜአት አሉ እነርሱም:-
1. ነግህ/ የጠዋቱ 12 ሰዓት/መክ.5÷3፣
2. ሠለስቱ ሰዓት /ከጠዋቱ 3 ሰዓት ዳን.6÷10፣
3. ስድስት ሰዓት /እኩለ ቀን/ መዝ.54 ÷17፣
4. ተሰዓቱ ሰዓት/ከቀኑ 9 ሰዓት/፣
5. ሰርክ /ከቀኑ/11 ሰዓት / መዝ.140÷4፣
6. ንዋም /ከምሽቱ3 ሰዓት/ መዝ.135÷2
7. መንፈቀ ሌሊት/እኩለ ሌሊት / መዝ. 118÷62::

## ሰባቱ አጽዋማት የሚባሉት

1. ዐቢይ ጾም /የሁዳዴ ጾም/ማቴ 4÷5፣
2. የሐዋርያት ጾም /የሰኔ ጾም/ማቴ.9፣
3. የፍልሰታ ጾም /ጾመ ማርያም / ኤፌ. 2÷20፣
4. ጾመ ነቢያት/የገና ጾም /ዳን.10÷2-4፣
5. ጾመ ገሐድ እዮ.2÷12፣
6. ጾመ ነነዌ ዮና.3÷1-10፣
ጾመ ድኅነት /የረቡዕና ዓርብ ጾም/ ኢዮ.1÷14::

## ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የሚባሉት

1. ምሥጢረ ጥምቀት፣
2. ምሥጢረ ሜሮን፣
3. ምሥጢረ ቁርባን፣
4. ምሥጢረ ክህነት፣
5. ምሥጢረ ተክሊል፣
6. ምሥጢረ ንስሐ፣
7. ምሥጢረ ቀንዲል ናቸው::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወ ላዲቱ ቅድስት ድንግል ማርያም:: አሜን!

**ምንጭ:-**

*በዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ትምህርት ክፍል በየወሩ እየተዘጋጀ የሚወጣ የስሌዳ መጽሔት*

ንቀህ ወደተውካት ዓለም ዞረህ አትይ
.......... እንደሎጥ ሚስት የጨው ዓምድ ሆነህ ትቀራለህና
/ዘፍ. 19÷26/

በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ እጅህን በክፋት አታንሣ
.........እንደ ኢዮርብአም እጅህ ደርቃ ትቀራለች
/1ነገሥ. 13÷4/

የሐሰት ቃል ከአንደበትህ አይውጣ
......... እንደሐናንያና ሰጲራ ትዋረዳለህና
/የሐዋ.5÷3-10/

ለድሻ ከመመጽወት አትቦዝን
...........እንደ ነዌ ያለጊዜው ይጸጽትሃልና
ሉቃ 16÷23-25

የሐሰተኛ ነቢያትን ምክር ሰምተህ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አትጣስ
........እንደ ኢዮኤል ክፉ አውሬ ያለቦታህ ያስቀርሃልና!
/1ነገ.13÷22/

በአባቶችህ አትሳለቅ.
............እንደ ካም ትረገማለህና
/ዘፍ.9÷20-25/

የእግዚአብሔርን ቤት አትድፈር
................ እንደ ዖዛ ትቀሰፋለህና
/2ሳሙ.6÷6-7/

የቤተክርስቲያንን ንዋያተ ቅድሳት ለራስህ አትጠቀም.
................ እንደ ብልጣሶር በእግዚአብሔር ተመዝነህ ቀለህ ትገኛለህና
/ዳን.5÷25-28/

መ/ር አብራራው ጫኔ /ከፍቼ/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

## ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም

መርሻ አለኸኝ /ከአ.አ.ዩኒቨርሲቲ/

በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት የምትገኘዋን የደሴን ከተማ ለቀን ወደሰሜን ጉዞ በጀመርን በ30ኛው ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሐይቅ ከተማን እናገኛለን:: ከተማዋ ስያሜዋን ያገኘችው 3ኪ.ሜ. ወጣ ብሎ ከሚገኘው አንድ ሐይቅ ነው:: ወደዚሁ ሐይቅ ለመሄድ በስተሰሜን የሚገኘውን ተራራ አቋርጠን ቁልቁለቱን ጥቂት ከተጓዝን በኋላ በርቀት የሚታየው ሐይቅና በእሱም ያለው ነገር ሳበንና ቆመን ማጤን ጀመርን:: በሐይቁ ሰሜን ምዕራብ ክፍል ባለው ደሴት የበለጠ ትኩረታችን በመሳቡ ስለእሱ ከጓደኛዬ ጋር መነጋገር ጀመርን:: ደሴቱ በርቀት ሲታይ መልህቋን ጥላ ዕቃ የምትጭን መርከብን ይመስላል:: የሐይቁ የውኃ መጠን በመቀነሱ ደሴቱ ከዋናው መሬት ጋር ተገናኝቷል:: በዚህ ደሴት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ገዳማት በጥንታዊነቱና በታሪካዊነቱ ታዋቂ የሆነው የሐይቅ እስጢፍኖስ ገዳም ይገኛል:: ምንም እንኳን ይህ ቦታ በ13 ኛው መ.ክ.ዘ በአባ ኢየሱስ ሞዓ ሲገደም 44 አድባራት ያዋስኑት እንደ ነበር ታሪክ ቢያትትም ዛሬ በምሥራቅ የእግዚአብሔር አብ፣ በምዕራብ የሊባኖስ አቦ፣ በሰሜን የቅድስት ማርያም ፣ በደቡብ ምሥራቅ የቅዱስ ሚካኤል ፣ በሰሜን ምዕራብ የምጽ ገበታው ቅዱስ ጊዮርጊስ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ቀርተውታል::

የሐይቅ እስጢፋኖስን ገዳም የከበበው ሐይቅ ጥንት በዚህ መልክ እንዳልነበረ ገድለ አባ ኢየሱስ ሞዓ በስፋው ያትታል:: አሁን ገዳሙ ካለበት ቦታ ላይ ጥንት አንዲት ባለጸጋ ሴት ትኖር ነበር:: ይህች ሴት ለቀጠረቻት ገረድ ትፈጭላት ዘንድ ብዙ እህል ትሰጣታለች:: ገረዷም ምንም እንኳ ከእመቤቷ እህሉን ብትቀበልም የዋለባትሥራ በጣም አድክሟት ኖሮ «ወላዲተ አምላክ እኔ ደክሞኛል አንቺ ፍጭልኝ » ብላ ተኛች:: ሏት ከመኝ ታዋ ተነሥታ እመቤቷ የሰጠቻትን እህል አስቀመጠችበት ቦታ ብታየው ዱቄት ሆኖ አገኘችው:: በነገሩ የተደሰተች ይቺ ገረድም የጭንቅ አማላጂቱን አመስግና እህሉን አስረከበች:: እመቤቲቱም ይህን ታሪክ በሰማች ጊዜ ገረዷን አስጠርታ «ይህን እህል አንቺ አልፈጨሽውም፣ እኔም ሆን ሌላ ያየሽ ሰው የለም:: በመሆ ኑም ደሞዝሽን አልከፍልሽም» ትላታች:: ገረዷም «እህል እንድፈጭልሽ ቀጥረሽኛል፣ ስለዚህ እህሉ ተፈጭቶ ዱቄት ሆኖ ከተገኘ ደመወዜንክፈል ይገባሻል »ብላ ወደ ሽማግሌ ይዛት ወጣች:: ይሁን እንጂ ሽማግሌዎቹ «ስትፈጪ ካልታየሽ ሊከፈልሽ አይገባም» ብለው በገረዷ ፈረዱባት:: ይህንን ኢርቱዕ ፍርድ የሰማችው ገረድም «እረኞች ይፍረዱኝ» በማለት ወደ እረኞች ይዛት ሄደች:: እረኞችም «የትም ፍጭው ዱቄ ቱን አምጭው» እንደተባለው የስጠሻት እህል ተፈጭቶ ዱቄት ሆኖከተገኘ ደመወዟን ትከፍያለሽ በማለት በእመቤቷ ፈረዱባት:: ማታውን ያልታሰበ ዝናብ መጥቶ የመጀመሪያዎቹ ሽማግሌዎች የፈረዱባትን ቦታና አካባቢ አሰጠመው:: ከመሬትም ወደ ላይ ውኃ መነጨ:: ከመካከል እረኞቹ የፈረዱበት ስፍራ ሳይሰጥም ሲቀር የቀረው ቀዬ በሙሉ በውኃ ተሸፈነ:: ያ ቦታ ነው ዛሬ የሐይቅ ደሴት የሆነው::

የእልፍ ቅዱሳን አባቶች መገኛ የሆነው ይህ ደሴት የክርስትና ሃይማኖት የተሰበከበት በ9ነኛው መ.ክ.ዘ በአፄ ድልነአድ ዘመን በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ ዘአዜብ 2ኛ ነው:: በ866 ዓ.ም የግብፁ ጳጳስ አቡነ ሰላማ 2ኛ ወደ አክሱም ሲሄዱ በሐይቁ በስተምሥራቅ ድማሞ በሚባል ተራራ እንዳረፉ ስለደሴቱ ታሪክ ይሰማሉ:: እኒህ አባት ሕዝቡን ካስተማሩ በኋላ ወደ አክሱም ሄደው በዘመኑ ለነበረው አፄ ድልነአድ ለአንተ ለመንበረ መንግሥትህ ፣ ለእኔም ለመንበረ ክህነቴ ትሆነን ዘንድ የምትገባን ቦታ አለችና እንሂድ ብለው ይዘውት ይመጣሉ:: ከአክሱም ይዘውት የመጡትን የእግዚ አብሔር አብ ጽላት አርፈውበት በነበረው በድማሞ ተራራ አስቀምጠው በ927 ዓ.ም ወደ ደሴቱ ገቡ:: ምንም እንኳ በደሴቱ የነበረ ጽላት ባለማግኘ ታቸው ቢቸገሩም መስከረም 15 ቀን ሌሊት አንዲት ቶራ የተባለች አውሬ «ምጽ ገበታ» እየተባለ በሚጠራው የደሴቱ ሰሜን ምዕራብ ጫፍ ላይ ስት ጮህ ይሰማሉ:: አቡነ ሰላማ 2ኛ የአውሬ ዋንጥሪ በመንፈስ ተረድተው ከተከታዮቻ ቸው ጋር ሲሄዱ አውሬዋ ጽላት ተጭና ያገኟታል:: ጽላቱንም ከአውሬዋ ወገብ ሲፈቱ አውሬዋ ከሕዝቡ ተሰወረች:: ጽላቱም «ዝውእቱ ታቦተ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት ወለታቦትኒ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘአውፅዕዎ ኅቡዓን እምኢየሩሳሌም » የሚል ጽሑፍና 2 ጽላት ተገኘ:: ይህ ቀን በየዓመቱ በታላቅ ድምቀት ይከበራል:: በነገሩ እጅግ የተደሰቱት አባት ጽላተ ጊዮርጊስን በሐይቁ በስተሰሜን ሲተክሉ ጽላተ እስጢፋኖስን ግን ዛሬ ካለበት ከደሴቱ ላይ ተከሉት:: ገዳሙም በሰማ ዕቱ እስጢፋኖስ መሰየሙም ለዚህ ነው::

ያ በርቀት ስንመለከተው የነበረን ግርምት እንዳለ በሐይቁ ሰሜን ምዕራብ ጠርዝ ያለውን ቁጤማ እያቆራረጥን ደረስን:: በተለይ በሐይቁ ጠርዝ የበቀለውን ረጃጅም ቄጤማ ስናቆራርጥ የተደሰተው ጓደኛዬ «እርጥብ በእርጥብ ነው መንገዱ ወደ እስጢፋኖስ ሲሄዱ» ብሎ በመግጠም አስፈገገኝ:: ገዳሙን በስተሰሜን ምዕራብ የሚያዋስነውን የምጽ ገበታ ጊዮርጊስን ከተሳለምን በኋላ ፊታች ንን ወደ እስጢፋኖስ ገዳም አዞርን:: ቦታው ለእግዚአብሔርን እየሠሩ የእግዚአብሔር በረከት የሚገኝበት ቦታ ነው:: ገና በገዳሙ በር የሚገኘውንና ጥንት አባ ፊልጶስ የተባሉ የገዳሙ አበምኔት በወቅቱ

ተነሥቶባቸው የነበረውን የሰይጣን ፈተና ለመቋቋም ቆመው በመጸለይ በሐይቁ ውስጥ ያለን ርኩስ መንፈስ እንዲቃጠል ካደረጉበት ቦታ ላይ ስንደርስ በምናኔ ከዓለም የተለዩት የገ ዳሙ መነኮሳት በኅብረት የውኃ መውረጃ ቱቦ እየተሸከሙ ሲገቡ አገኘና ቸው:: ሁሉም የማይገባንን አክብሮት የተሞላበት አቀባበል ካደረጉልን በኋላ በረከቱ ይደርሰን ዘንድ አንድ ቱቦ ለሁለት በመሸከም አብረናቸው ገባን:: ቦታው የቀደሙ አባቶች እግዚአብሔርን በማገልገል በረከት ያገኙበት ቅዱስ ሥፍራ እንደሆነ አፀዱ ይናገራል:: አንዱ አንዱን እያበረታታ ቱቦውን ከምናስቀምጥበት ቦታ ስንደርስ አንድ ሻል ያለ ቤት ተሠርቶ በማየታችን የምን ቤት እንደሆነ የገዳሙን መጋቢ አባ ፊሊጶስን ጠየቅናቸው:: አባታችን በተለየ ትኅትና «ልጆቼ ይህ ቦታ እንኳንስ የቤተክርስቲያን አባቶች ድሮም እነ አፄ ድልነዓድ መጥተው የተቀመጡበት ነው፤ እና ይኽ ቤት የሀገረ ስብከታችን ሊቀ ጳጳስ አቡነ አትና ቴዎስ ቀሪ ሕይወታቸውን እዚህ ሊያሳልፉ በራሳቸው ወጭ ያሠሩት ነው::» አሉን::

አባታችን አባ ፊልጶስ ከቀሩት መነኮሳት ፈቃድ ካገኙ በኋላ ሊያስጐበኙን ተያይዘን ሄድን:: ከአባ ጋር ወደ ዕቃ ቤቱ ስንሄድ ሳላስበው ከአጠገቤ የደረሰው እባብ አስደንግጦኝ ወደ አባ ሮጬ ስጠጋ አባ በዚህ ገዳምና በከበበው ሐይቅ የሚገኙ አውሬዎች ሁሉ ሰውን እንዳይጐዱ በአባ ኢየሱስ ሞዓ እንደተገዘቱና እነሱም ብዙ ጊዜ ተነድፈው እንዳልታመሙ ራሳቸውን አብነት አድርገው ነገሩን:: እግረ መንገዳችንን የአሁኑ መነኮሳት ከቀደሙት አባቶቻችን ተረክበው በተራ ምግብ የሚያበስሉበትን ቤት ካየን በኋላ ከዕቃ ቤቱ ደረስን:: በዚህ ቤት ውስጥ የአባቶቻችን ፅናት ምን ያህል እንደነበር የሚመሰክሩ የተለያዩ ንዋየ ቅድሳትና ቅርሶች ይገኛሉ ::


በሸዋ ክፍለ ሃገር የሚገኘውን የደብረ ሊባኖስን ገዳም የገደሙት አቡነ ተ/ሃይማኖት ለመመንኮስ በገዳሙ በቆዩበት ወቅት ለመነኮሳቱ ምግብ በቀን እስከ ዘጠኝ ቅርጫት እህል ይፈጩበት የነበረው





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ወፍጮና ሲፈጩም የሚሸከሙት ወደ 10ኪ.ግ የሚመዝን ከዕብነ በረድ የተሠራ መስቀል ሲታይ ግሩም የአንተ ሥራ ያሰኛል:: ከዚሁም ጐን ከ835 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸውና እኒሁ አባት ለወጥ ማጠራቀሚያነት ይገለግሉበት የነበረ ጋንና ማማሰያዎች ይገኛሉ:: አቡነ ተ/ሃይማኖት ለአገርና ለወገን ሲጸልዩ አንገታቸውን የሚያስደግፉበት ባላም እንደተተከለ ይገኛል:: አባ ፊልጶስ በማይቀየረውና ትኅትና በተመላው አንደበታቸው ሌሎችን በቤቱ የሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶች ካስጐበኙን በኋላ ባየነው ነገር እነደተመሰጥን እግረ መንገዳችንን በመነኮሳቱ በመልማት ላይ ያሉትን የተለያዩ አትክልቶች ካየን በኋላ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ወደ ሆነው መንፈሳዊ ቤተ መጻሕፍት ሄድን:: ያሉት ጥንታውያን ውድ መጻሕፍት የቤተመጻሕ ፍቱን ጥንታዊነት ቢመሰክሩም ከቤቱ ማርጀት በተጨማሪ መጻሕፍቱ በያሉበት እየጠፉ መሆናቸው ያሳዝናል::አባ «ምን እናድርግ ልጆቼ ቢጨንቀን እንዲህ እናደ ርጋለን» ብለው ጣታቸውን ወደታች ቀሰሩልን::



አዎ የጨነቀው.... እንዲሉ የተጨነቁት አባቶች ሰሌን ንጥፈው ዋና ዋና የሚባሉትን መጻሕፍት መሬት ላይ ደርድራዋቸዋል:: በርግጥም መጽሐፈ ምሥጢርና ሌሎች ውድና የጥንት መጻሕፍት በአይጥና በብል እየጠፉ ይገኛሉ:: በመጻሕፍት ቤቱ የቆዩና ታሪካዊ ዋጋ ያላቸው ብዙ የብራና መጻሕፍት አሉ:: መጽሐፈ ምሥጢርን የመሰለ ባለ 210 ገፅ ውድ የብራና መጽሐፍ በአይጥ ሲጠፉ ለሚያይ ምእመን እውነት እኔ የአባቶች ታሪክ ተረካቢ ነኝ? ያሰኛል ::

ከጠዋት ጀምሮ የዋለባቸው ሥራ ያላደከማቸው አባት ከቤተ መጻሕፍቱ ይዘውን ሲወጡ አይዟችሁ በማለት የማበረታቻ ቃል ከሰጡን በኋላ «ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም የመጣ ደከመኝ ሰለቸኝ ሣይል ማየት አለበት:: በዚህ ገዳም የምታዩት ሁሉ ታሪካዊ ነው» አሉንና ፈገግ አሉ:: አባ እውነታቸውን ነው:: የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በቦታው ያየውን ሁሉ በዚች ጠባብ ዓምድ ለመዘገብ ባለመቻሉ ቢያዝንም ምእመናን ይህንን ቅዱስ ቦታ ሄደው በማየት የራሳቸውን ማስታወሻ እንዲቀርፁ ይጋብዛል:: « እስጢፋኖስ ገዳም» ከሚለው ስም ጐን «የበርካታ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ትውፊቶች ደሴት» በመባል ቢሰየም የሚበዛበት አይሆንም:: ከቤተ መጻሕፍቱ እንደወጣን ያመራነው የጉብኝታችን ማገባደጃ ወደሆነው ወደ ደብሩ ነበር:: በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በመንግሥት ድጋፍ ወለሉ ሊሾ ከመሆኑ ውጭ ምንም ዓይነት ጥገና ሳይደረግለት ለ800 ዓመታት የቆየው ይህ ቤተክርስቲያን ከሁሉም በላይ የተደላደለ አቀማመጡ ግርማ ሞገስ እንዲላበስ አድርጐታል:: አባ ቤተክርስቲያኑ አስቸኳይ ዕድሳት እንደ ሚያስፈልገው በኀዘኔታ ገልፀውልን ፈታች ንን ወደ ምዕራብ ስናዞር የበለጠ ትኩረ ታችንን የሳቡ ሁለት ነገሮች አየን:: ከሁለት እንጨቶች መካከል የተንጠለጠለ ድንጋይ፣መነኮሳቱን ለጸሎት መጥሪያ የሚያገለግል ደወል ነው:: በዚያ ቦታ ድንጋዩም እየጮኸ እግዚአብሔርን ያገለግ ላል:: ሌላው ያስገረመን ነገር ከሐይቁ ውስጥ የወጣ የሼል እንስራ ሲሆን ይህ ሸክላ ከ400 ዓመታት በላይ በሐይቁ ውስጥ ከመኖሩ የተነሣ በባሕር እንስሳት ቅርፊት/ሼል/ ተሸፍኖ የተገኘ ነው:: ይህ እንስራ ሁለት ሰዎች ተባብርው ሊያነሡት አይችሉም::

በቦታው የደቂቃዎች እንኳ ቆይታ ያደረግን ሳይመስለን ሁለት ሰዓት የፈጀ ውን ጉብኝታችንን አጠቃለልን::

አባ ፊልጶስ የእሳቸው ድካም ሳይታያቸው እኛን እያበረታቱ ወደመነኮሳቱ በአት ወሰዱን:: መነኮሳቱም የእኛን መምጣት በጉጉት ይጠባበቁ ኖሮ በጽሑፍ ሊገለጽ በማይችል አባታዊ ትኅትና ተቀበለው ጋበዙን:: ዘጋቢው ምግብ ቀርቦለት እንዲበላ ሰዎች እንዲያ ተባብረው ሲጨነቁለት ሲያይ ያ ቀን የመጀመ ሪያው ነው:: አባቶች የበላን ሳይመስላቸው እኛ ግን በደንብ በልተን ስብሐት ተብሎ ታርጐ ማዕዱ ከፍ አለ:: ወደ ቦታው ሴቶች መግባት እንደ ማይችሉ በዚሁ ጊዜ ተረድተናል:: መለየት አይቀርም:: ሁሉም አባቶች ውዳሴ ማርያም ከደገሙልን በኋላ ጉዟችንን ወደ ሐይቅ ከተማ አደረግን::

በአባቶች ብርታትና ተጋድሎ የቆየንን ይህን ጥንታዊ ገዳም ቢቻል በቅ ርብ እንዳሉ የገዳሙ መነኮሳት ባይቻል ግን በርቀት ልንረዳው ያስፈልጋል:: ሌላው ቤተ ክርስቲያን ልታስብበት የሚገባው ጉዳይ በቀድሞው መንግሥት በሐይቁ በስተደቡብ የተጀመረው የመዝናኛ ቦታ ነው:: ይህ የመዝናኛ ቦታ ፍጻሜ አግኝቶ ሥራ ላይ ከዋለ የዚህን ቦታ ቅዱስነት ይፈታተናልና ቢቻል ቤተክርስቲ ያን የዚህ የመዝናኛ ቦታ ባለይዞታ የምትሆንበት ዘዴ ተፈልጐ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ቢውል መልካም ይሆናል::

እግዚአብሔር አምላክ ለአባታችን ለአባ ኢየሱስ ሞዓ የገባው ቃል ኪዳን ገዳሙን አገልግለን በእኛ ላይ ተፈጻሚ ይሆን ዘንድ ያነሣሣን:: አሜን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን በአባቶቻችን አንደበት

* «ሰውን ብትታገልና ብትዋጋ ታሸንፈዋልህ ወይም ያሸንፈሃል፣ ቤተክርስቲያን ግን ለማሸነፍ አይቻልም፣ ቤተክርስ ቲያን ሁለጊዜ ትዋጋለች ተሸንፋ ግን አታውቅም፤ ዲያብሎስ ዝና ሩን አራገፈ ቀስቱን ጨረሰ:: ቤተክርስቲያንን ግን አልጐዳ ትም :: »

*/የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ አፈወርቅ /የቤ/ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ 48/*

* «ነፋስ ነፈሰ ዝናብም ዘነበ ጐርፍም ጐረፈ ይህም ቤተክርስቲያንን ሊያናውጠው ቃጣ:: ቤተክርስቲያን ግን በጽኑ መሠረት በተዋሕዶ ሃይማኖት በመንፈሳዊ ምግባር ትሩፋት በጾም በጸሎት የተመሠረተ ስለ ሆነ ሊያናው ጸው አልቻለም:: »

*/መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ ኲኲሐ ሃይማኖት/*

* «ቤተክርስቲያንን ከክርስ ቶስ የሚለይ የለም ክርስቶስ ከቤተክርስቲያን እንደ ማይለይ ቃል ገብቷልና:: ስለዚህ ማንኛ ውም የጉዞ አቀበትና ቁልቁለት ቢያጋጥማትም ከክርስቶስ ጋር ያለች ቤተክርስቲያን አትደነግ ጥም:: በካታኮምብ ብትቀድስ በወርቅ በተለበጠ በሐር በተንቈጠቈጠ ቤተመቅደስ ብትቀድስ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ናት::»

*/ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ የቤተክርስ ቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ ገጽ 9/*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ጻድቁ አቡነ ሀብተ ማርያም

መምህር አብራራው ጫኔ /ከፍቼ/ እና አይቼው ዐብዩ /ከዓለም ከተማ/

ታላቁ ጻድቅ አባት አቡነ ሀብተ ማርያም የተወለዱት በመንዝ አውራጃ ልዩ ስሙ የራዊ የተባለ ቦታ ነው:: አባታቸው ፍሬ ብሩክና ዮስቴና በሕግ ጋብቻ ጸንተው የሚኖሩ የተከበሩ ባለጸጐች ነበሩ:: እግዚአብሔርን በመፍራት የተራበ እያበሉ፣ ለተጠማ እያጠጡ፣ለታረዘ እያለበሱ፣ያዘነ እያፅናኑ እንግዳ እየተቀበሉ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው በንጽሕና በቅድስና ይኑሩ እንጂ ልጅ አልነበራቸውም::

በዚህ ሁኔታ እያሉ ቅድስት ዮስቴና የምንና ሐሳብ መጣባቸው:: የሐሳባቸው ጥንስስ ወደ ተግባራዊነት ተሸጋግሮ ከዚህ በደስታ እየኖርኩ እግዚአብሔርንም ሳላስደስት ከምኖር መንኜ ለነፍሴ የሚበጅ ሥራ ልሥራ ብለው በአካባቢያቸው የሚገኝ ጫካ ውስጥ ዋሻ ፈልገው ገቡ:: የአዕዋፍና የአራዊት ድምፅ ብቻ በሚሰማበት በዚያ ዋሻ ውስጥ አንድ መነኩሴ አገኙ:: በብሕትውና የሚኖሩት አባትም ሰይጣን በምታት የመጣባቸው መስሏቸው በትእምርተ መስቀል አማተቡባቸው:: እርሳቸው ግን ሰው ናቸውና አልሸሹም:: መነኩሴውም ሴቲቱ እንዳልሸሹ ባዩ ጊዜ « የማይረባ ሥራ የምትሠሪ አንቺ ሴት ልታሳስችኝ መጣሽን ? ስለምን ሰይጣን በልቡናሽ ገባ ? » አሏቸው:: ቅድስት ዮስቴናም «እኔ ለዚህ ርኩስ ሥራ የመጣሁ አይደለሁም:: የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነኝ:: እሱን ለማገልገልና ለማስደሰት ሀብት ንብረቴን ትቼ የመጣሁት ለምንና ነው:: እዚህ ቦታ ሰው እንዳለ አላወቅሁም:: » አሏቸው:: ለባሕታዊውም እግዚአብሔር ድብቁን ሁሉ ገለጠላቸውና « አንቺ መናኝ አይደለሽም ወደ ቤትሽ ተመለሽ» አሏቸው:: ቅድስት ዮስቴና ግን ከአጠገባቸው እንዲርቁላቸው ብቻ የተናገሩአቸው ስለመሰላቸው የመነ ኩሴውን ሐሳብ መቀበል አልፈለጉም:: ይልቁንም ወደ ሌላ ገዳም ለመሄድ አሰቡ:: እኒያ የበቁ አባት «ምንኩስና ለአንቺ አልተፈቀደም ወደቤትሽ ግቢ ጸሎቱ ለዓለም ሁሉ የሚጠቅም ፣ ሰው ሁሉ የሚማጸነው፣ ስሙ ገድሉ ፣ ትሩፋቱ በዓለም ሁሉ የሚነገርለት፣ በአፀደ ሥጋ በአፀደ ነፍስ የሚያማልድ ፣ በምድር ሆኖ መንበረ ጸባዖትን የሚያይ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽና» አሏቸው:: የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ የሰሙ ቅድስት ዮስቴናም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደቤታቸው ተመለሱ:: ቃሉ የታመነ አምላክ በወዳጁ አንደበት ያናገረውን የሚፈጽም ነውና በነሐሴ 26 ቀን ቅድስት ዮስቴና ፀነሱ ::

ግንቦት 26 ቀንም ደምግባታቸው ያማረ፣ እንደ ንጋት ኮከብ የሚያበሩ ሀብተማርያም ተወለዱ:: ታላቅ ደስታም ተደረገ :: በ40 ቀናቸውም ክርስትና ተነሥተው ስመ ጥምቀታቸው ሀብተ ማርያም ተባለ::

ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ ቅዱሳንን ከየዘመኑ የሚመርጥ እግዚአብሔር አቡነ ሀብተማርያምንም ለቅድስና መረጣቸው:: በእናታቸው ጀርባ ታዝለው እንኳን ካህኑ በቤተክርስቲያን « እግዚኦ መሐርነ ክርስቶስ » ሲል እሳቸውም በሕፃን አንደበታቸው «እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ »ይሉ ነበር:: ይህንን ጸሎት ደጋግመው ይጸልዩ፣ በሌሊትም እናትና አባታቸው ሲተኙ ተነሥተው ወገባቸውን ታጥቀው አምላካቸውን ይለምኑ ፣ ላባቸው እስኪንጠፈጠፍ ይሰግዱ ነበር::

ወደ እረኝነት ከገቡ በኋላ እረኞች እየሰረቁ የሚያመጡትን እሸት ተካፍለው የማይበሉ እንደነበሩ ታሪካቸው ያስረዳል::



ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር አምላክ የሚገልጥላቸው ብዙ ምሥጢርም ነበራቸው:: አንድ ቀንም አባታቸው ጐን ከተኙበት እግዚአብሔር በድምጽ ጠራቸው:: ነቢዩ ሳሙኤልን በልጅነቱ ስሙን ደጋግሞ በመጥራት ሰማያዊውን ምሥጢር ያመለከተው ጌታ አሁንም ሀብተ ማርያምን « አንተን የተመረጠ ዕቃ አድርጌሃለሁና ቃሌን ለተመረጡ ሰዎች ተናገር» አላቸው::

እድሜአቸው እየጨመረ ሲመጣ አባታቸው እረኝነትን አስትተው ወደ ትምህርት ቤት አስገቧቸው:: ትምህርቱንም ከጥሩ ሥነምግባርና ሕግን ከመጠበቅ ጋር ጠንቅቀው ተማሩ:: ለአቅመ አዳምም ሲደርሱ ሚስት ታጨላ ቸው:: ነገር ግን እንጦንስንና መቃርስን በድንግልና እዲያገለግሉት የመረጠ ፣ ገብርክርስቶስን ከጫጉላ ቤት የጠራ አምላክ ሀብተማርያምንም ልቦናቸውን ለዚህ ስላነሣሣ ከአባታቸው ቤት ወጥተው ኮበለሉ:: በመንገዳቸውም « የምሄድበትን ጐዳና ምራኝ:: ቅን ልቦናንም ስጠኝ፣ ስለስምህም ብለህ በቸርነት ከዚህ ዓለም ጣጣ አድነኝ ፣ ሰውነቴን መከራ ከሚያጸኑባት ከፍትወታት እኩያት አድ ነኝ:: እኔ ባሪያህ ነኝና::» እያሉ ይጸልዩ ነበር::

በገዳምም አባ ሳሙኤል ለተባሉ አባት ረድነት ገቡ:: በዚያም ብዙ ገቢረ ተአምራት ተደርጐላችዋል:: ለምሳሌ አንድ ቀን በእንሥራ ውኃ ቀድተው ሲመለሱ አደናቅፎአቸው እንሥራው አመለጣቸው:: ነገር ግን እግራቸው ሥር መሬት ደርሳ ከመሰባበር ይልቅ እንደሸረሪት እየተፎአጨረች ራሳቸው ላይ ቁጭ አለች:: በሌላ ቀንም ለአባ ሳሙኤል ጧፍ ሲያበሩላቸው ከእጃቸው ወድቆ ጠፋ:: ደንግጠው ቢያነሡት ሳይለኮስ በራ:: አባ ሳሙኤልም እየተደነቁ « የዚህ ልጅ መጨረሻ ምን ይሆን? » ይሉ ጀመር ::

ከአቡነ መልከጸዴቅ ገዳም ተነሥተው ሲሄዱ መንገድ ላይ ከአንድ ዋሻ ውስጥ ለሦስት ወራት በጸሎት ቆይተዋል:: እግዚአብሔር « መታሰቢያህን በዚህ ዋሻ አደርገዋለሁ» ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል:: ይህ ዋሻ ዪስበይ አባ ሀብተማርያም ገዳም በመባል የሚታወቀው ነው::

የዕረፍት ቀናቸው በደረሰ ጊዜ ጌታ ተገልጦ ሰባት አክሊላትን እንደሚቀበሉ ነገራቸው:: እነዚህም ስለ ፍጹም ድንግልናቸው፣ ስለፍጹም ምናኔያቸው፣ ስለ ንጹሕ ምንኩስናቸው ፣ አራቱን ወንጌላት አዘውትረው ስለማንበባቸው፣ፈጽመው ስለመራባቸው እና ስለመጠማታቸው ፣ ስለ ልቦናቸው ንጽሕናና ስለንጹሕ ክህነታቸው የተዘጋጁላቸው ናቸው:: ከዚህ በኋላ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች:: ይህችም ቀን በአገረ ናግራን ያሉ ምእመናን ሰማዕትነት በተቀበሉበት መታሰቢያ ቀን ኅዳር 26 ቀን ሲሆን ዘመኑም በ1490 ዓ.ም ነው:: ካህናትና ቅዱሳን በሚያምር ልብስ ገንዘው በቅዱሳን መቃብር በአቡነ ተክለሃይማኖት ቦታ ቀበሯቸው:: አሁንም በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ደብረሊባኖስ አካባቢ በሚገኘው በሰበይ አቡነ ሀብተማርያም ገዳም ነሐሴ 26 ቀን ፅንሰታቸው፣ ግንቦት 26 ልደታቸው፣ ኅዳር 26 ቀን ደግሞ ዕረፍታቸው በድምቀት ይከበራል::

የአባታችን የአቡነ ሀብተ ማርያም ጸሎትና አማላጅነት በሁላችን ላይ አድሮ ይኑር:: አሜን::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ዓምደ ወራዙት

## የጽዋውንና የወጭቱን ውስጥ ማጥራት

ከዘሩባቤል

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግብዝነት ያይልባቸው የነበሩትን ጻፎችና ፈሪሳውያን ሲወቅሳቸው «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን በውስጡ ቅሚያና ስስት መልቶ ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለም ታጠሩ ወዮላችሁ:: አንተ ዕውር ፈሪሳዊ ውጭው ደግሞ ጥሩ እንዲሆን አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጡን አጥራ ማቴ.23÷25:: » ብሏቸው ነበር::

ጻፎች በነገሥታት ዘመን በቤተ መንግሥት አገልጋዮችና አማካሪዎች ነበሩ:: 1ኛዜና 27÷32:: ጥሩ ልብስ ለብ ሰው የቀለም ቀንድ በወገባቸው ይታጠቁ ነበር:: ከምርኮ በኋላ ግን እንደ ዕዝራ የሕግ ምሁራን ሆኑ:: ዕዝ 7÷6:: በመጀ መሪያ ካህናት ነበሩ:: በኋላም ለብቻቸው ልዩ ቡድን ሆኑ:: በደንባቸው መሠረት ለዕለት ኑሮአቸው አስፈላጊውን ነገር በእጅ ሥራ እያገኙ በነጻ ሕግን ያስተ ምሩ ሕግን ይተረጉሙ፣ እንዲሁም ይዳኙ ነበር:: ማር 7÷1፣ሉቃ 2÷46፣ 22÷66: ሕጉም እንደይጣስ የሽማግሌዎች ወግ የተባ ለውን ልማድ ያወጡት እነዚህ ክፍሎች ናቸው:: ከጻፎች ብዙዎቹ የፈሪሳውያን ሐሳብ ደጋፊዎች ነበሩ:: የሐዋ. 23÷9 ::

ፈሪሳውያን ደግሞ ከአይሁድ የሃይማኖት ወገኖች አንዱ ክፍል ሲሆኑ እነርሱም የሙሴን ሕግ በጥንቃቄ የተረጐሙ ናቸው:: ተርታውም ሕዝብ ሕጉን እንዳይተላለፍ ሲሉ ብዙ ትእዛዝና ሥርዓት በመጨመራቸው ለሕዝቡ ከባድ ሸክም ሆኖበት ነበረ:: ማቴ15÷1፣23÷1:: ከዚህም ሌላ ሀብታሞች እና በምኩራቦችም መሪዎች ነበሩ:: ይሁን እንጂ እንደነ ኒቆዲሞስና እንደነ ጳውሎስ ያሉ ቅን ሰዎች የተገኙት ከፈሪሳውያን መካከል ነው::

እነዚህ ክፍሎች ጻፎች እና ፈሪሳውያን መንፈሳዊ ዕውቀት እንጂ መንፈሳዊነት አልነበራቸውም:: አለባበሳቸውና አነጋገራቸው መንፈሳዊ ቢሆንም ተግባራቸው ግን ከሥጋውያን የባሰ ነበር:: ማዘዝን እንጂ መታዘዝን፣ የማይወዱ የተናገሩትን የማይፈጽሙ፣ ሥራቸውን በሰው ፊት ለታይታ ብለው የሚሠሩ ነበሩ:: ቢጾሙ፣ ቢጸልዩ፣ ቢመጸውቱ፣ ቢሰግዱ ሁሉንም የሚያደርጉት ለታይታ እና ለውዳሴ ከንቱ ነበር:: ማቴ. 6÷1-18:: ዘወትር የከበረ ልብስ የሚለብሱ፣ በምሳ የከበሬታ ስፍራ፣ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር የሚፈልጉ፣በገበያም ሰላምታና መምህር ሆይ፣መምህር ሆይ ተብለው መጠራትን የሚወዱ ከመሆናቸውም በላይ የሚያስከብር ሥራ ሳይኖራቸው አክብሩን፣ የሚያስወድድ ባሕርይ ሳይኖራቸው ውደዱን የሚሉ፣በመንፈሳዊነት ስም የሚነግዱ፣ ሥጋውያን ሆነው በመገኘታቸው «እናንተ ግብዞች... መንግሥተ ሰማያት በሰው ፊት የምትዘጉ ....ደንቆሮዎች እና ዕወሮች ...ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ::» ማቴ 23÷1-24 ተብለዋል::

ጻፎችና ፈሪሳውያን ውጫቸው ቅዱስ፣ ውስጣቸው ርኩስ በመሆኑ ልብ ያመላለሰውን ኩላሊት ያጤሰውን የሚያውቅ አምላክ ጥቃቅኑን ኃጢአት አጥርታችሁ የምትናገሩ ታላላቁን ግን ሰውራችሁ የምታስቀሩ፤ወጭት ጽዋ ሰውነታችሁን በውጭ ንጹሕ የምታደርጉ በውስጥ ግን ኃጢአትን የተመላችሁ እናንተ ዕውራን ፈሪሳውያን የውጭው ንጹሕ እንዲሆን ከፈለጋችሁ አስቀድማችሁ ሰውነታችሁን በውስጥ ንጹሕ አድርጉት ብሏቸዋል::

ውጭ የተባለው ሥጋ ሲሆን ውስጥ የተባለችው ደግሞ ነፍስ ናት:: ሰው ሥጋውን ቢያነጻ የሥጋ ንጽሕ ለነፍስ አይሆንም:: ነፍስ የነጻች እንደሆነ ግን ለሥጋም ይተርፈዋል:: ቅዱሳን የነፍሳቸው ንጽሕና ለሥጋቸው የሥጋቸው ደግሞ ለልብሳቸው ተርፎት በልብሳቸው በመቋሚያቸው እና በጭራቸው ከመፈወስ ደርሰዋል:: ነቢዩ ኤልያስ በጥምጥሙ፣ ነቢዩ ኤልሳዕ በበትሩ፣ ቅዱስ ጳውሎስ በልብሱ ተአምራት ያደርጉ ነበር:: 2ኛ ነገ 2÷8፣ 4÷29፣የሐዋ 19÷12::

ከዚህ ከጌታችን የተግሣጽ ትምህርት የምንማረው በቅድሚያ መለ ወጫ መጽዳት እና መጥራት ያለበት ውስጣችን መሆኑን ነው:: «በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ» ሮሜ12÷2፣ «በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ ::» ኤፌ 4÷23 እናንተ ኃጢአተኞች እጃችሁን አንጹ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ ልባችሁን አጥሩ:: » ያዕ4÷8 እንደተባለ የመለወጥ መጀመሪያ ከውስጥ ሰውነት ነው::

አብዛኛውን ጊዜ በቤተክርስቲያን የምንታይ ሰዎች መለወጥ የምንጀምረው ከላይ ነው:: የምንጠነቀቀውም ለዚህ ብቻ ነው:: ከአለባበሳችን ጀምሮ ለአነጋገራ ችን፣ ለአካሄዳችን እና ለአመጋገባችን ጭምር እንጠነቀቃለን:: የምንጠነቀቀውም በሰው ፊት ነው:: ምክንያቱም እኛ የምንፈልገው መንፈሳዊነትን ሳይሆን «እገሌ እኮ መንፈሳዊ ነው» መባልን ነውና:: ነጠላ የምንለብሰው ፣ የምንዘምረው ፣ የምንሰብከው፣ የምንመጸውተው ወዘተ... ለታይታ ነው:: ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰው በሌለበት መቀደስ ፣መዘመር ፣ መስበክና፣ መመጽወት የማንፈልግ ሰዎች ጥቂቶች አይደለንም::

በለሰለሰ አንደበት መናገር አንገት መድፋትና መቅለስለስም የመለወጥ ምልክት ወይም መንፈሳዊነት የሚመስለን ሰዎች እጅግ ብዙዎች ነን:: ይህም በውጭ ያለውን ብቻ ስለምንመለከት ነው:: እግዚአብሔር ግን የሚያየው የውስጡንም ነው:: ነቢዩ ሳሙኤል የኤልያብን መልከ ቀናነት አይቶ «በእውነት እግዚአብሔር በፊቱ የሚቀባው ይኸንን ነው::»ባለ ጊዜ እግዚአብሔር ሳሙኤልን «ፊቱን የቁመቱን ዘለግታ አትይ፤ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል»1ኛ ሳሙ. 16÷6-7 ያለው ለዚህ ነበር:: ምክንያቱም«እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለምና::»

እኛም በዘመርንበት አንደበታችን የምንዘፍነው፣ ባሸበሸብንበት እግራችን የምንደንሰው፣ ከቅዳሴ እና ከጉባኤ መልስ ወደ ኃጢአት የምንገሰግሰው፣ የምንሰርቀው የምንዋሸው ፣ የምናመነዝረው ወጭትና ጽዋ ሰውነታችን ውስጡ ባለመጽዳቱ ነው:: «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኩስትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ:: እንዲሁ እናንተ ደግሞ በውጭ ለሰው እንደ ጻድቃን ትታያላችሁ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ዓመፀኝነት ሞልቶባችኋል::» የተባለውን መርሳት አያስፈልግም:: ማቴ. 23÷27-28

መማር ብቻውን ዋጋ የለውም:: ምክንያቱም በተማርነው መንፈሳዊ ትምህርት ውስጣችንን እስካላጸዳንበት ጊዜ ድረስ ዕውቀት ብቻ ሆኖ ምናልባት መንፈሳዊ ዕውቀት ስላለን መንፈሳዊን ነገር እንናገር ይሆናል፤ ወይም ዕውቀቱ ስላለን ብቻ በመንፈሳዊ ቦታ እንሠራ ይሆናል:: ሰዎችም የምንውልበትን ቦታ እና የምንለብሰውን መንፈሳዊ ልብስ አይተው የምንናገረውን አድምጠው እንደ መንፈሳውያን ይቆጥሩን ይሆናል:: ነገር ግን እኛ መንፈሳዉያን ሆነን እስካል ተገኘንና ውስጣችንም እስካልጸዳ ድረስ ዕውቀት ብቻውን ዋጋ የለውም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚፈልገው ልባችንን ነውና:: «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ፣ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ::» ምሳ 23÷26::እንዲል::

ፈቃደ ሥጋችንን ለፈቃደ ነፍሳችን አስገዝተን፣ ውስጣችን ጠርቶ ሕይወታችን ካልተለወጠ በስተቀር የአንደበት ለውጥ ብቻውን ፍሬ የለውም :: በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግር ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ እንደሚያታልሉ ሐሳውያን መሆን ነው:: ሮሜ 16÷18:: መንፈሳዊነት አነጋገርን በማሳመር ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር አፈ ኰልታፋውን ሙሴን ለአገልግሎት አይ መርጠውም ነበር:: ዘጸ.





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

4÷10:: በመቅለስለስም ቢሆን ይሁዳ
እየተቅለሰለሰ ቀርቦ ጌታን ስሞ ታል፤
ይሁን እንጂ የውስጡን ከፍቅረ ንዋይ
አለመጽዳት የሚያውቅ አምላክ «ይሁዳ
ሆይ በመሳም የሰውን ልጅ አሳ ልፈህ
ትሰጣለህን? » ብሎታል:: ሉቃ 22÷48::

ጌታችን በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም
ሳለ ያደረገውን ምልክት አይተው ብዙ
ሰዎች በውጭ ተለውጠው በስሙ አምነው
ነበር፤ «ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ
ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር
አያስፈልገውም ነበር፤ አይተማመናቸው
ነበር፤ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና:: »
ይላል:: ዮሐ.2÷23-25 ምክንያቱም ውስጣ
ቸው ፈጽሞ አልጸ ዳምና ከጥብርያዶስ
መጥተው በጀልባ ተሳፍረው ኢየሱስ ክርስ
ቶስን ፍለጋ ወደ ቅፍርናሆም የገሰገሱትን
ሰዎች ከላይ ለተመለከታቸው ፍጹም . መን
ፈሳውያን ቢመስሉም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን
«እውነት እውነት እላችኋለሁ የምትፈል
ጉኝ እንጀራን ስለበላችሁ እና ስለጠገባችሁ
ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደ
ለም:: ለሚጠፋ መብል አትሥሩ ነገርግን
ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው
ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤» ብሏቸዋል::
ዮሐ. 6÷22-27:: እነዚህ ሰዎች በልባ ቸው
የነበረው የእንጀራ ፍቅር እንጂ የክርስቶስ
ፍቅር አልነበረም::

በመንፈሳዊ ሕይወት የቆምንበት
የቅድስና ሥፍራና እኛ ወይም የምንናገረ
ውና የምንሠራው ከተለያየ ይህ ነገር
የሚያስገነዝበን የውስጣችንን አለመ ጽዳት
ነው:: ትርፉም እገሌ እኮ መንፈሳዊ ሰው
ነበር፣ አሁን ግን መናፍቅ ሆነ፣ አመንዝራ
ሆነ፣ ሌባ ሆነ ወዘተ... ተብሎ መቅረት
ይሆ ናል:: አንድ ሰው በሁኔታው
መንፈሳዊ ሊመስል፣ለጊዜው መንፈሳዊ
ሥራ ሊሠራ ወይም መንፈሳዊ ትምህርት
ተምሮ ሊቅ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን
ውስጡ እስካል ጸዳ ድረስ ነገ ሊክድና
ሊለወጥ ፣ ሌላ ሊሆን፣ ክፉ ሥራም ሊሠራ
እንደሚችል መገመት አለብን::
እንዲህም ከሆነ ማንም በማንም ምክንያት
ተሰነካክሎ አይወድ ቅም:: ይህ ንን
በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ
ይላል:: «አንተግን አይሁዳዊ ብትባል
በሕግም ብትደገፍ በእግዚአብሔ ርም
ብትመካ ፈቃዱንም ብታውቅ ከሕግም
ተምረህ የሚሻለውን ፈትነህ ብት ወድ ፣
በሕግም የዕውቀትና የእውነት መልክ
ስላለህ ፣ የዕውሮች መሪ፣ በጨለ ማም
ላሉ ብርሃን፣ የሰነፎችንም አስተማሪ ፣
የሕጻናትም መምህር እንደሆንህ በራስህ
ብትታመን፣እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታ
ስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ
ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን ? አታመን
ዝር የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን
የምት ጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን ?
በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአ
ብሔርን ታሳፍራለህን? በእናንተ ሰበብ
የእግዚአብሔርን ስም በአሕዛብ መካከል
ይሰደባልና ተብሎ እንደተጻፈ::» ሮሜ 2÷
17-24::

በሁላችንም ላይ እንደሚታየው
በመንፈስ ጀምረን በሥጋ የምንጨርሰው
በቅድሚያ ውስጣችን ባለመጽዳቱ ነው ::
ስማችን መንፈሳዊ ቢመስልም በውስጣችን
ያለው ግን ዝሙት፣ መዳራት፣ ጣዖትን
ማምለክ፣ሟርት ፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣
ቁጣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት
፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ስካር ዘፋኝነት
ነው:: ስለዚህ ከሁሉ አስቀድመን
ልንታገላቸው የሚገቡ እነዚህን በውስጣችን
የሠለጠኑትን ፍትወታት እኩያትን ነው::
«እንግዲህ ክፋ ትን ሁሉ፣ተንኰልንም
ሁሉ፣ ግብዝነት
ንም፣ቅንዓትንም፣ሐሜትንም ሁሉ አስወግ
ዳችሁ፣ ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ
እንደሆነ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ
ተንኰል የሌለበትን የቃሉን ወተት
ተመኙ::» 1ኛጴጥ.2÷1-3:: እንዲህ ካልሆነ
ግን እንደ ገላትያ ሰዎች መሆናችን የማይ
ቀር ነው:: «የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች
ሆይ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ
እንደተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ለእውነት
እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን
ነው? .. እንዲህን የማ ታስተውሉ ናችሁ?
በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ
ትፈጽማላችሁን?» ገላ.3÷1-3::

ከዝሙት መንደር ውልቅብላ
የወጣችው መግደላዊት ማርያም የዝሙት
ነገር ትዝ ሳይላት በጽናት እስከ
መጨረሻው የተጓዘችው ወጭትና ጽዋ
ሰውነቷ በቅድሚያ ውስጡ በመጽዳቱ
ነበር:: በመሆኑም ኃጢአተኞች እንደመ
ሆናችን መጠን እርሷን አብነት ልናደርግ
ያስፈልገናል:: ደግሞም ወጭትና ጽዋ ሸክላ
በመሆኑ ተሰባሪ ዕቃ ነው:: ከዚህም
የምንገነዘበው ነገር ቢኖር ዛሬ የምንሳሳ
ለትና የምንጨነቅለት ሰውነታችን ነገ
ተነገ ወዲያ ተሰባሪ ወይም ሟች መሆኑን
ነው:: ምንም ቢሆን ወደ አፈርነታ ችን
መመለሳ ችን የማይቀር ነውና:: ስለዚህም
ውስጣችንን ለማጽዳት እንድን ችል
የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም
አማላጅነት አይለየን አሜን::

# ንስሐ - ለምንና እንዴት ?

ከተሾመ አይቼው

ባለፉት ሁለት እትሞቻችን የባሕር
ዳሩ ተሾመ አይቼው በንስሐ ዙሪያ ሰፋ
ያለ ጽሑፍ ማስነበባቸው ይታወሳል:: ለዚህ
እትምም ንስሐን ለማንና እንዴት መናዘዝ
እንደሚገባ ፣ ከንስሐ በኋላ ያለ ሕይወት
ምን መሆን እንዳለበት በመጨረሻም የን
ስሐ ፍሬን ምንነት ያቀረቡልናል::

## ንስሐችንን ለማንና እንዴት እንናዘዝ?

እግዚአብሔር አምላክ አገልጋዮቹ ይሆኑ
ዘንድ የመረጣቸው፣ «በምድር ያሠራችሁት
በሰማይ የታሠረ ይሆናል፣ በምድር
የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል»
ብሎ በማይታበለው ቃሉ የሾማቸው
አዕይንተ እግዚአብሔር /የእግዚአብሔር
ዓይኖች /የተባሉ ካህናት ኃጢአታችንን
የምንናዘዝላቸው ከታሠርንበትም የኃጢአት
ማሠሪያ የሚፈቱን የእግዚአብሔር መልእ
ክተኞች ናቸው:: ማቴ18÷18

ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች የሠሩትን
በደል እንዳይታወቅባቸው ለንስሐ አባታ
ቸው ኃጢአታቸውን ከመንገር ይልቅ በየገ
ዳማቱ በየአድባራቱ በመሄድ መናዘዝን፣
ግፉም ሲል አንድ ጊዜ የሠሩትን ኃጢአት
ሌላም ጊዜ ስለሚደግሙት ካህናትን
መቀያየርን ይመርጣሉ:: ሕይወታችንን
ለሚ ያውቅ የንስሐ አባት ራሳችንን
መግለጥ እንጂ ዛሬ አንዱ ጋር ነገ ሌላ
ቦታ መሄዱ አይደገፍም:: የሮማ ካቶሊክ
ካህኑና ተነሳሒው እንዳይተያዩ በመጋረጃ
እንዲለ ያዩ ሥርዓት አወጣች:: ከእነርሱ
የወጡት ፕሮቴስታንቶችም አያስፈልግም
ብለው ኃጢአታችሁን «ለጌታ ብቻ»
ንገሩት ካህን አያስፈልግም አሉ:: በ20ኛው
መቶ ክ/ዘመን የተነሡ ደቀ
መዛሙርቶቻቸው ደግሞ «ንስሐን ተቀብሎ
ቀኖና የሚሰጥ» ኮምፒውተር ሠርተው
በገበያ ላይ አዋሉ:: ሰዎችን ለዚህ ሁሉ
ያበቃቸው ንስሐቸውን ለማንና እንዴት
መናዘዝ እንዳለባቸው ባለማወቃቸው
ይመስላል:: ከዚህም በተጨማሪ አንድ
ሰው ለንስሐ አባቱ ኃጢአቱን ሳያፍርና
ሳይፈራ መናገር የሚችለው ራሱን
በትኅትና ዝቅ ያደረገና አምላኩን
መበደሉን ከልቡ ያመነበት እንደሆነ ነው::
ስለዚህ መፀፀታችን ለፍሬ እንዲበቃ
ከቤተሰብ ያልተለየን የቤተሰባችንን የንስሐ
አባት የንስሐ አባታችን በማድረግ፣
ራሳችንን ችለን በግላችን የምንኖርም
በአጥቢያችን የሚገኙትን አባት በማነጋገር
የንስሐ አባት መያዝ ይገባል::

በሌላ በኩል ግን ንሰሐ የሚገቡ
በት ወቅት ግማሹን ተናግረን ሌላውን
የሚተውም አሉ:: ይህ ግን «ግማሽ ጐፈሬ
ግማሽ መላጣ» ዓይነት የተዘበራረቀ በመ
ሆኑ ለመንፈሳውያን የሚበጅ አይደለም::
ስለዚህ ኃጠአቶቻችንን ያለመዘንጋትና
አንድም ሳያስቀሩ መናገር ያስፈልጋል::
ለዚህ ነው አንድ አባት «እኛ ኃጢአታች
ንን የምናስታውስ /የምንናዘዝ/ እንደሆነ
እግዚአብሔር ይረሳልናል:: እኛ ግን ኃጢአ
ታችንን የማናስታውስ /የማንናዘዝ/ ከሆነ
እግዚአብሔር ያስታውሰዋል::»ያሉት::

## ከንስሐ በኋላ ያለ ሕይወት ምን መምሰል አለበት?

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ
በመልእክቱ« የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋች
ሁበት በመዳራት፣ በሥጋ ምኞትም፣
በስካርም፣ በዘፈንም፣ ያለልክም በመጠ
ጣት፣ ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ
የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃል»
1ጴጥ. 4÷3 በማለት አስቀድሞ በጨለማ
ስለነበረውና ኋላም በወንጌል ብርሃን
ስለተለወጠው ስለ አዲሱ ሕይወት ተናግ
ሯል::

አንድሰው ከንስሐ በኋላ ያለ
ሕይወቱ በወንጌል ላይ የተመሠረተ አዲስ
በመሆኑ፣ በፊት ከነበረው ኃጢአት የነፃ
ነው:: ይህ ማለት አንድ ጊዜ ንስሐ የገባ
ሰው ደግሞ ኃጢአት አይሠራም ማለት
አይደለም:: መጽሐፍ «ጻድቅ ሰባት ጊዜ
ይወድቃል፤ ይነሣማል::» ያለው ይህንኑ
ለማሳየት ነው:: ስለዚህ ንስሐ በገባን
ማግሥት ራሳችንን እንደ ንጹሐንና
ቅዱሳን በመቁጠር መመጻደቅ ሳይሆን
ለበለጠ መንፈሳዊ ተጋድሎ መዘ ጋጀት
ይገባል:: ምክንያቱም ሰይጣን ከእጁ
ያመለጣቸውን ነፍስ ወደ ግዛቱና ግዞቱ



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ለመመለስ ተስፋ እንደማይቆርጥ ይታወቃልና::

ከንስሐ በኋላ ያለ ሕይወት ዘሩን በለሰለሰ ማሣው ላይ በበተነ ገበሬ ሊመሰል ይቻላል:: ገበሬው ሰብሉ አሽቶ ፣ጐምርቶ፣ ታጭዶም ከገለባ ተለይቶ ጐተራ አስኪገባ እንቅልፍ እንደሌለው? መንፈሳዊ ሰውም በ40ና በ80 ቀን በመጠመቅ የጀመረው በጾም፣በጸሎት ፣በስግደት አጠንክሮ ወደ አምላኩ እስኪጠራ ድረስ ተዘናግቶ አይቀመ ጥም:: ስለዚህ ንስሐችንን ለማጽናት እንደ ውሻ ወደ ትፋታችን /ኃጢአታችን/ እንዳንመለስ ከፈለግን ጥንት ወደ ኃጢአት ይገፋፉን ከነበሩ ጓደኞችና ቦታዎች መለየት ይገ ባል:: ከጠጪዎች መካከል ተቀምጦ አልጠጣም፣ከዳንሰኞቹ ተራ ገብቶ ዘፈን አልወድም፣ አለያም ከአመንዝራዎች መካከል ተገኝቶ የዝሙትን ወሬ አታንሡብኝ ማለት እሳት ላይ ተቀምጦ አታቃጥለኝ፣ እጅን አንበሳ አፍ ከቶ አትብላኝ እንደማለት ይቆጠራል:: አንዳንድ ሰዎች ሰይጣን አሳስቶኝ ወደቅሁ ለማለት ከላይ የዘረዘርናቸውን ነገሮች በሙሉ ይፈጽማሉ::

በአጠቃላይ መልካም እርሻ የሆነውን ከንስሐ በኋላ ያለሕይወታች ንን በመንፈሳዊ ተጋድሎ በጾም፣ በጸ ሎት፣ በስግደት፣መጠበቅ ይገባል ::

### የንስሐ ፍሬ

ሐዋርያው እንደተናገረው የንስ ሐና የመንፈሳዊነት ፍሬው ፍቅር፣ደስታ፣ሰላም፣ትዕግሥት፣ቸርነት፣በጐነት፣ እምነት የዋሕነት ራስን መግዛት:: ገላ. 5÷22 በመጨረሻም ገነት መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ነው:: አንድ ሰው ንስሐ የሚገባው «እገሌ ጻድቅ ነው » ለመባል ሳይሆን እነዚህን መንፈሳዊ ሀብቶች ገንዘቡ ለማድረግ ነው:: ሰለዚህ ሰይጣንና የሥጋ ፍላጐት አሸንፈን የእግዚአ ብሔር የአምላካችን መንግሥት ወራሾች እንሆን ዘንድ ንስሐ እንግባ::

ለዚህም የበቃን እንድንሆን እግዚአብሔር ይርዳን:: አሜን::

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

## ጥያቄዎቻችሁ

ጥያቄ1- አንድ ሰው ሚስት ቢያገባና ዝሙት ፈጽማ ብትገኝ መጽሐፍ «ፍታት» ይላል:: በመሆኑም በትክክል ሴትዮዋ ዘሙታ ከተገኘችና ካልተቀበላት እንዲፈታት ተፈቅዶለታል:: ታዲያ ይህ ሰው ሌላ ሴት መልሶ በቅዱስ ቁርባን ማግባት ይችላል?

ተስፋዬ ወልደ ሚካኤል /ቦረና- ያቤሎ/

መልስ- በሥርዓተ ቤተክርስቲያን መሠረት አንድ ክርስቲያን ሥልጣነ ክህነት ከሌለውና በበቂ ምክንያት /በዝሙት፣ በሞት፣ ወዘተ.. / ከመጀመሪያ ሚስቱ ቢለያይ እስከ ሁለት ጊዜ ድረስ ማግባት ይችላል:: አሁንም ችግር ከተፈጠረበት ግን እንዲሁ እግዚአብሔርን እያገለገለ ይኑር:: በመሆኑም በእነዚህ ሁለት ጊዜያት ሁሉ የካህን ጸሎት ተደርጎለት በቅዱስ ቁርባን ያገባል:: ፍት.ነገሥ. አንቀጽ 24÷896፣ አንቀጽ 24÷906:: ከዚህ ውጭ ያለ ቅዱስ ቁርባን ከሆነ ግን የአመጸኝነት ምልክት ነውና በቤተክርስቲያን እንደ ጋብቻ አይቆጠም :: እንዲያውም ለክርስቲያን ከቅዱስ ቁርባን መለየት ሞት እንደሆነ ሊታወቅ ያስፈልጋል:: ዮሐ.6÷54:: ጥያቄውም ሆነ መልሱ ሁለቱንም ጾታዎች እንደሚመለከት ልናስታውስ እንወዳለን::

ጥያቄ.2- ለሰው ልጆች ከተሰጡት ጥበባት መካከል ድርሰት አንዱ ነው:: ደራሲ መሆን ባልችልም ጥሩ ጸሐፊ ለመሆን ፍላጎቱ አለኝ:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ ድርሰቶችን ማንበብ እንደሚያስፈልግ አያጠያይቅም:: ታዲያ መንፈሳዊ ሰው ከንባብ መታገድ አለበት?

ወልደ ትንሣኤ ኃ/ማርያም
/ጎንደር/

መልስ - አንድ ክርስቲያን እንደማንኛውም ሰው ተሰጥኦው ካለው ደራሲ መሆን ይችላል:: እንደተባለው የድርሰት ችሎታን ለማዳበርና የበሰለ ጽሑፍ ለመጻፍ ንባብ አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም ደራሲ ለመሆን ፍላጎት ያለው ሰው ተሰጥኦውን እንዲያዳብር ብዙ ማንበብ ይጠበቅበታል:: ነገር ግን መንፈሳዊ ሰው አንድን ነገር ለመሥራት ሲፈልግ መንፈሳዊ ሕይወቱን የማይጎዳ መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ይኖርበታል:: የሚጠቅመውንና የሚጎዳውንም የሚመለከተው ከቃለ እግዚአብሔር እና ከሕገ ቤተክርስቲያን አንጻር ነው:: ስለዚህ ከዕድሜውና ከመንፈሳዊ ብስለቱ አንጻር የሚያነባቸው ነገሮች ሁሉ የተመረጡ ሊሆኑ ያስፈልጋል:: የእሳትነት ባሕርይ የሚያደላበት የዕድሜ ደረጃ ያለ ወጣት ልቅ የሆነ ወሲብን የሚያስፋፉ መጻሕፍትን /Pornographic Books/ ቢያነብ በዝሙት ሊፈተን ብሎም ሊወድቅ ይችላል:: ነገር ግን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ላይ ብዙም ፈተና የማያመጡበትንና የዕውቀት አድ ማሱን ሊያሰፉ የሚችሉ መጻሕፍትን ቢያነብ ይጠቀማል እንጂ አይጎዳም:: ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው እየመረጠ ያነባል እንጂ ከንባብ አይታገድም:: 2ቆሮ.7÷1:: 1ቆሮ 10÷23-24::

ጥያቄ 3- ዕድሜዬ 18 እና ድንግል ነኝ:: አንዳንድ ጊዜ ግን በሐሳቤ ወደፊት ስለሚኖረኝ የወሲብ ሕይወት አስባለሁ:: ይህ ሐሳቤ ዝሙት ይባላል? ደግሞም ከዕድሜዬ አንጻር በአሁኑ ሰዓት ብዙ የጓደኝነት ጥያቄዎች ቢቀርቡልኝም አልተቀበልኳቸውም:: ለመሆኑ የከንፈር ወዳጅ /Boy friend/መያዝ ኃጢአት ነው? ብቻ በእነዚህ ምክንያቶች እየተጨነቅሁ ብጾም፣ ባስቀድስና ጉባኤያትን ብካፈልም እስከዛሬ ድረስ ሥጋወደሙን ከመቀበል ታቅቤአለሁ እና መላ በሉኝ:: በዚያ ላይ የንስሐ አባቴ ትንሽ ልጅ አድርገው ስለሚመለከቱን /ከጓደኞቼ ጋር / ንስሐችንን አይቀበሉንም:: ዝም ብለው ሰግዳችሁ ቁረቡ ይሉናልና ምን ማድረግ ይሻለኛል?

ማ.ማ ከ አ.አ.ዩ

መልስ - በቅድሚያ ሙሉ አድራሻሽን ባለመግለጽሽ ለአንድ ዓመት ያህል ሊዘገይብሽ ችሏል::

«ወደፊት ስለሚኖረኝ የወሲብ ሕይወት አስባለሁ » ስትይ ብዙም ግልጽ ባይሆንም እንደተረዳነው ግን ወደፊት ስለሚኖርሽ የጋብቻ ሕይወት ይመስለናል:: እንዲህ ከሆነ ዝሙት አይባልም:: ቢሆንም ገና ከጋብቻ በኋላ ለሚሆነው ነገር ከአሁኑ ጀምሮ ከሚገባው በላይ መጨነቅ አያስፈልግም:: አንድን ነገር ያለጊዜው ማሰብ ለማይገባ ምኞትና ውድቀት ይዳርጋልና:: እንዲሁም በአእምሮሽ የሥጋ ፍትወት እርካታን የምታስቢ ከሆነ የሀልዮ ዝሙት ሊባል ይችላልና በጸሎትና የበለጠ ወደ እግዚአብሔር በመቅርብ ልታጠፊው ይገባል:: ማቴ 5÷ 28፣ያዕ 4÷7፣ ቆላ 3÷5-7::

በዘመናችን ብዙ ወጣቶች ሲፈጽሙት የምንመለከተው እና ያለዘላቂ ዓላማ እንዲያው ለጊዜአዊ ደስታ ብቻ የሚይዙት ዓይነት የከንፈር ወዳጅ /Boy friend/ አይፈቀድም:: የክርስቲያኖች ትልቁ ችሎታም ጊዜአዊ የሥጋ ፍትወትን በኃይለ እግዚአብሔር አሸንፎ ለክብር መብቃት በመሆኑ የጊዜውን ሳይሆን የዘላለሙን ማሰብ ይገባናል:: ከዚህ አንጻር ሐሳብሽ ወዲያና ወዲህ እያለ የሚያስቸግርሽ ከሆነ እንድትረጋጊ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይሆነኛል የምትይውን እስከ ጋብቻ የሚጠብቅሽ እጮኛ መያዝ ትችያ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ለሽ። ነገር ግን በየጊዜው እንደ የአስፈላጊቱ የሚቀያየረውን በስም እንጂ ብዙም ከትዳር ጓደኛ የማይለየው ዓይነት /በግብር የሚተዋወቁበት/ የከንፈር ወዳጅ /Boy friend/ መያዝ ኃጢአት ነው። እንደተገነዘብ ነው ይህ ዓይነቱ ሐሳብ የሚመጣው ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ጓደኞች ጋር ከመዋል ፣ወደ ዝሙት የሚገፋፉ መጻሕፍትን ፣ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን እንዲሁም ፊልሞችን ከማዘውተር የተነሣ ይሆናል። ስለዚህ አቅምን ዐውቆ መቆጠቡ ይመረጣል።

ንስሐ አባትሽን ለብቻሽ ሄደሽ ኃጢአትሽን መናዘዝ እንደምትፈልጊ ንገሪአቸውና የሚያዙሽን ፈጽመሽ ዛሬ ነገ ሳትይ ቁረቢ። ቅዱስ ቁርባን ያጸናል፣ ከኃጢአትም ይጠብቃልና። ንስሐ አባትሽ በጣም ብዙ የንስሐ ልጆች ኖሯቸው አንቺን ተረጋግተው ማዳመጥ የማይችሉ ከሆኑ ግን አሳውቀሻቸው ሌላ አባት መያዝ ትችያለሽ። በተረፈ አድራሻሽን ካሳወቅሽን የተቀሩትን ጥያቄዎች በግል ልንመልስልሽ ዝግጁ ነን።

ጥያቄ 4 - የ19 ዓመት ወጣት ነኝ። ከአንዲት ልጅ ፍቅር ይዞኛል። ማለትም ልብ ለልብ ሁለታችንም እንደምንፈላለግ ዐውቃለሁ። ማነጋገር ደግሞ በጣም እፈራለሁ። እርሷን ለመርሳት ብሞክርም በፍጹም አልቻልኩም። እንዳላያትና እርሷ በምትሄድበት ሁሉ እንዳልሄድ ወስኜ ሳላያት ለተወሰነ ጊዜ ብቆይ እንኳን በጸሎት ሰዓት ሳይቀር ከፊቴ ድቅን እያለች ታስቸግረኛለች። ቢጨንቀኝ እርሷ መጥታ እንድታነጋግረኝ ወይም እኔኑ ድፍረት እንዲሰጠኝ መጸለይ ጀመርኩ። በሌላ በኩል ደግሞ እርሷን ማጣት አልፈልግም። በጣም ተጨንቄያ ለሁና እባካችሁ ከዚህ ጭንቀቴ እንድትገ ላግሉኝ በእግዚአብሔር ስም እለምናች ኋለሁ።

ግርማ
/ከአ.አ/

መልስ - ወንድማችን አንተን የገጠመህና የደረሰብህ ሁሉ በአንተ የዕድሜ ክልል ባሉ በብዙ ወጣቶች የሚደርስ ነውና ልትጨነቅ አይገባም። እንዲያውም አንተ በጣም አስተዋይ ነህ፣ መፍትሔው ለሌሎች ማወያየትና ጸሎት መሆኑን ዐውቀሃልና። ይህ ያለህበት ዕድሜ የእሳትነት ባሕርይ የሚያይልበትና ብዙ ነገር ሲሠራ ረጋ ብሎ በማመዛዘን የሚበጀውን ከማድረግ በስሜት ብቻ በመመራት እርምጃ የሚወሰድበት ወቅት ስለሆነ እንዳትሳሳት ልጅቷን የወደድካት ከምን አንጻር እንደሆነ ረጋ ብለህ አስብ። ለተቀደሰ ዓላማ /ጋብቻ/ አስበሐት ነው ወይስ ውጪያዊ አቋሟን ብቻ ተመልክተህ በጊዜያዊ ፍላጎትህ ተሸንፈህ ? ፍቅርህ ወረተኝነት የሌለበትና ዘላቂውን የጋብቻ ሕይወት በማሰብ ከሆነ ለዚሁ ዓላማ እንደምትፈልጋት በድፍረት ግለጽላት። ያውም እንደገለ ጽክልን ከሆነ በእርሷም በኩል ፍላጎት አለ። ስለዚህ ሥራህ ኃጢአት እስካልሆነ ድረስ መፍራት የለብህም። ለንስሐ አባት ህም በምክርና በጸሎት እንዲሁም በሚያስፈልገው ሁሉ እንዲረዱህ ግልጽ አድርገህ ንገራቸው። ባሕላችን ስለሚይዛት እርሷ እንድታነጋግርህ ግን አትጠብቅ። የራስህ ሥራ መሆኑን አስበህ ደፍረህ በትኅትና አነጋግራት። ነገርግን እንደማትፈልግህ ጫን ብላ ከነገረችህ አንዳንድ ሥርዓት አልባ ወጣቶች እንደሚያደርጉት ችክ በማለት አላስወጣ አላስገባ ማለት የለብህም። መንፈሳዊ እንደመሆንህ ብትወዳትም እንኳን ጠንክረህ የተባልከውን በጸጋ ተቀብለህ እግዚአብሔር ለአንተ ያላትን እስኪሰጥህ መጠበቅ ይኖርብሃል። ፊል.4÷13 ።

በዚሁ አጋጣሚ አንዳንድ በዕድሜ የደረሳችሁ እኅቶቻችንም ወንድሞቻችሁ ለጋብቻ እንደሚፈልጓችሁ ሲያነጋግሯችሁ «የትአባክ» ዓይነት መልስ እየመለሳችሁላቸው ባታስበረግጓቸው መልካም ነው። የማትፈልጓቸው እንኳ ቢሆን በትኅትና አስርዷቸው እንጂ ቁጣና ስድብ ከእናንተ አንደበት ሊወጣ አይገባም። ኤፌ. 4÷29-32፣ ቆላ.3÷8 ።

በዚሁ አጋጣሚ ተመሳሳይ ጥያቄ የምታቀርቡልን ምእመናን ዕድሜያችሁን ፣የኑሮ ሁኔታ፣ የትዳር ሁኔታ እና የቤተክርስቲያን ተሳትፎአችሁን ብትጠቅሱ ለመልሳችን መሟላት አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

# ውርጃ /Abortion/

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር
በዶ/ር አይድዐ ግርማ

እግዚአብሔር አምላክ ለሴቶች ከሰጣቸው ጸጋ አንዱ እና ትልቁ ከፍጥረት ሁሉ አልቆ በአርአያውና በምሳሌው የፈጠረውን የሰው ልጅ በትንኟ ማኅፀን ፀንሰው ለመውለድ መቻላቸው ነው። ይህ የእናት እና ልጅ ግንኙነትም በምሳሌነት የሚጠቀሰው «ፍቅር» የሰጠውን አምላካዊ ሥጦታ በመቀናቀን የሚሠሩ አንዳንድ ድርጊቶች ገጽታቸው በግለሰብ ብቻ የማይ ወሰኑ በመሆናቸው ትኩረት እንዲሰጣቸው ለማሳየት ግድ ሆነ ከእነዚህም ኢአርቶዶ ክሳዊ ድርጊቶች መካከል አንደኛው ውርጃ /abortion /ነው። አንድ ሕያዊት ነፍስ ያለችውንና በእግዚአብሔር የከበረውን ፍጥረት /ፅንስ/ እንደ አልባሌ ዕቃ አውጥ ተው መጣል በሀገራችን ሕግ የተከለከለ ቢሆንም ድርጊቱ ግን ከዕለት ዕለት በመ ጨመር ብዙ ሰዎችን በሥጋም በነፍስም በመጉዳት ላይ ይገኛል።

በባለሙያዎች አገላለጽ ውርጃ ሁለት ዓይነት መልክ አለው። የመጀመሪያው ከእናቲቱ ቁጥጥር ውጪ የሆነው ግብታዊ ውርጃ /spontaneons abortion/ ይባላል። ለዚህም ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ ያህል ከመጀመሪያው የእርግዝና መታወክ የተነሣ በሚፈጠረው እንቁላሉ በሥርዓት ማደግ አለመቻል ወይም የሰውነት ቅርጽ መበላሸት ምክንያት ወይም በአሥራ አንደኛውና በአሥራ ዘጠነኛው የእርግዝና ሳምንታት መካከል በሚፈጠሩ እናታዊ ምክንያቶች ውርጃ ሊከሰት ይችላል። ይህም በጎጂ ሕዋሳት ምክንያት በሚፈጠር የፅንስ መበላሸት ወይም እናቲቱ ላይ በሚደርሱ የሥነ ልቡና ተጽዕኖች ምክንያት የሚመጣ ይሆናል።

ግብታዊ ውርጃ ከቁጥጥር ውጪ የሚመጣና በእግዚአብሔር የማያስጠይቅ ቢሆንም ወላጆች ጽንሱን በጥንቃቄ የመያዝ ግዴታ አለባቸው። በግዴለሽነት ፅንሱ አደጋ ቢደርስበት ተጠያቂዎች ይሆናሉና።

ሁለተኛው ለዚህ ጽሑፍ መዘጋጀት መነሻ የሆነው ሆን ተብሎ የሚፈጸመው ውርጃ ነው። /Induced abortion /ይባላል ይህም ሰዎች ፅንሱን ባለመፈለጋቸው የሚፈጽሙት ገድሎ የማስወጣት ድርጊት ነው። የሚፈጸመውም ከሚከተሉት ሁለት መንገዶች በአንዱ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ጽንሱን ባለመፈለጋቸው በየጉራንጉሩ እጀሰብ መድኃኒቶችን በመጠቀም ሲፈጽሙት ሌሎች ደግሞ በግል ጥቅም በታወሩና ነፍሰ ገዳይነትን የገቢ ምንጭ ባደረጉ ባለሙያዎች በመታገዝ ነው። « አትግደል » የሚለውን ትእዛዝ እግዚአብሔር በመጣስ የሚፈጸመው ይህ ድርጊት ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። ለዚህ ተጠያቂዎች ደግሞ በፈቃደ ሥጋ ተነድተው ድርጊቱን የፈጽሙት ወንድና ሴቷ ብቻ ሳይሆኑ ውርጃን መፍትሔ አድርገው ያቀረቡ ክፉ መካሪዎች ፣ መድኃኒት በጥብጠው ያቀረቡ የመንደር አስወራጆችና በድብቅ ውርጃን የሚፈጽሙ የሕክምና ባለሙያዎች ጭምር ናቸው። የሴቷን ነፍስ ከሞት ለማዳን በየጤና ማዕከላቱ የሕክምና እርዳታ የሚያደርጉ የሕክምና ባለሙያዎች በመልካም ሥራቸው ይመሰገናሉ እንጂ ከወቀሳው የነጹ ናቸው።

መልካም እና ክርስቲያናዊ አስተዳደግ በማጣት እና በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን በሚተላለፈው ፍትወተ ሥጋ ቀስቃሽ መልእክት ምክንያት የሚፈጠረው ይህ ችግር ለብዙ ወጣቶች ሕይወት መበላሸት ምክንያት ሆኗል። በሐረር ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው ዕድሜያቸው ከ 13-16 የደረሱት 20% የሚሆኑ ሴቶችና 65% የሚሆኑ ወንዶች ቢያንስ አንድጊዜ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽመዋል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከእነዚህም ውስጥ 20% የሚሆኑት ሴቶች ያረገዙ ሲሆኑ ካረገዙትም መካከል ኃጢአታቸውን በሌላ ኃጢአት ለመሸፈን 56% ውርጃን መርጠዋል:: በዚህ ዕድሜ ላይ ለሚፈጸመው ውርጃ ምሳሌ ይሆን ዘንድ ይህ ጥናት ተጠቀሰ እንጂ በሌሎችም አካባቢዎች ውርጃ እየሠለጠነ መምጣቱን እንባብያን ማስተዋል ያስፈልጋቸዋል::

በአጠቃላይ ከጋብቻ በፊት የሚያረግዙት ሴቶች ሰባ አምስት በመቶዎቹ ውርጃን ይፈጽማሉ:: ነገሩን እንዲባባስ ካደረጉት ምክንያቶች :-

• ወላጆች ልጆችን በመልካም ሥነ ምግባር፣ በክርስቲያናዊ ሕይወት አለማሳደጋቸው፣መንፈሳዊነትንና እምነታቸውን ለልጆቻቸው አለማውረሳቸው::

• በቅድስት ቤተክርስቲያን ወጣቶች የምክር አገልግሎት እንዲያገኙና በየሰንበት ት/ቤቶችም የጾታ ትምህርት ለመስጠት የሚችል የሰው ኃይል አለመኖሩ እና

• አንዳንድ መገናኛ ብዙኃን ምንም ኃላፊነት ሳይሰማቸው ዝሙትን የሚያስፋፋ መልእክቶችን ማስተላለፋቸው የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል::ኮንዶም መጠቀምን ለሕዝብ ማስተዋወቅ ለአብነት ከሚጠቀሱት አንዱ ነው::

ከሀገራችንም ውጪ ወርጃ ለብዙ ወጣቶች ሕይወት እንቅፋት መሆኑን አንዳንድ ጥናቶች ይጠቁማሉ:: ለም ሳሌ በአሜሪካ በአንድ ዓመት ብቻ ከ1 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች ያረግዛሉ:: ውርጃን ሕጋዊ ማድረግ መፍትሔ የመሰላቸው ነገር ግን የውጤቱ ክፋት ሊቆጣጠሩት ከሚችሉት በላይ የሆነባቸው እንደ እንግ ሊዝ ያሉ አገሮችም አሉ:: ለዚህ መፍት ሔው የሰዎች በትእዛዘ እግዚአብሔር መመራት መቻል ብቻ ነው::

• ውርጃ ነፍስ ማጥፋት በመሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ከማስጠየቁ በተጨማሪ የሚከተሉትን ችግሮች ያመጣል::

•ደም በብዛት በመፍሰሱ ለሞት ያደርሣል፣

የማኅፀን በኅጅ ሕዋሳት መወረር ፣ በቱቦዎች ላይ የሚፈጠር በሽታ ከዚያም በኋላ ለመውለድ አለመቻል፣

• የወር አበባ መምጫ ጊዜ መዛባት፣ከመጣም የሚያሰቃይ ሕመም መስማት፣አንዳንድ ጊዜም መጥፎ ሽታ ያሉው ፈሳሽ መከሰት::

በማኅበራዊ ሕይወትም ሆነ በሥነ ልቦና በኩል የሚገጥሙ ችግሮች አሉ::

ኅብረተሰቡ ውርጃን ለሚፈጽሙ ሰዎች ባለው ዝቅተኛ አመለካከት ምክንያት ትዳር የማግኘት ችግር ሊመጣ ይችላል:: በሁለተኛ ደረጃም የነፍስ ገዳይነት ስሜት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ስለማይለያቸው የሥነ ልቦና ችግር ይገጥማቸዋል:: ከዚህ ሁሉ ለመዳን ብቸኛው መንገድ እራስን በንጽሕና ለተቀደሰ ጋብቻ ማዘጋጀት ፣ የፈጸሙ ሰዎችም እራሳቸውን ጥቅም እንደሌለው ሰው ከመቁጠር ይልቅ ንስሐ ገብቶ ከአምላክ መታረቅ ነው::

በ1985 ዓ.ም በአዲስ አበባ በ1,000 ሴቶች ላይ በተደረገ ጥናት በወሊድ ምክንያት ከሞቱት 5.6% ሴቶች ግማሾቹ /50%/ ሕይወታቸውን ያጡት በውርጃ ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል:: ኅብርተሰባችንን ከሥጋም ሆነ ከነፍስ ቅጣት ለማዳን ውርጃ የሚቆም በት ብቸኛው መፍትሔ ቃለ እግዚአብ ሔርን መጠበቅ መሆኑን እንገንዘብ::

እግዚአብሔር አምላክ በወንድ አብራክ እና በሴት ማኅፀን ካለው ዘር እንሥቶ ዕድሜ እስከተጫነው አረጋዊ ድረስ ላለው የሰው ልጅ ያስባልና ፅንስን ገድሎ ከማውጣት እንክልክል:: ለዚህ ነው የይስሐቅን ሚስት ርብቃን «ሁለት ወገኖች በማኅፀንሽ ናቸው ::» /ዘፍ.25÷23 በማለት በማኅፀን ያሉትም ወገኖች መሆናቸውን ያስተማረን::

ስለዚህ ከጥፋት ተከልክለን የአምላካችን መንግሥት ወራሾች እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን::

## ወደ እውነት ለመድረስ በሐሰት ጐዳና ?

### ከዓባይነህ ካሴ

እውነት ማለት ትክክለኛና ስሕተት የሌለበት ቃል ነው:: ቃሉ እውነት የሆነ እግዚአብሔር እውነትን ለሰው ገልጧል:: «በእግዚአብሔር ለተመረጡት እምነት እንዲሆንላቸው በዘላለም ሕይወት ተስፋ እንደ እምልኮት ያለውን እውነት እንዲያውቁ ተላከ፤ ስለዚህም ሕይወት የማይዋሽ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ::» ቲቶ1÷2:: « በእውነትህ ቀድሳቸው ፤ ቃልህ እውነት ነው:: » ዮሐ 17÷17፣ ሮሜ 1÷19እንዲል:: በሕገ ወንጌልጸንቶ በመኖር የእርሱ ደቀመዛሙርት በመሆን የምትታወቅ እውነት ነጻ የምታወጣ ናት:: ዮሐ 8÷31-32 ::

ሐሰት ደግሞ ከእውነት የራቀ ቃል ነው:: የሐሰትም አባት ጥንተጠላታችን ዲያብሎስ በመሆኑ ሐሰትን የሚናገሩ ሁሉ የሚመሩት በእርሱ መንፈስ ነው:: 2ኛ ዜና 18÷ 22፣ ኤር.14÷14:: «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ ፤ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ:: እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም:: ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፣ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና:: » ዮሐ8÷44፣ ዘፍ3÷4 ፣4÷9:: እውነትን የማያምኑ በሐሰትም የሚኖሩ ይፈርድባቸዋል:: 2 ተሰ. 2÷9-12::

በዓለማችን የሰው ልጅ የኑሮን ውጣ ውረድ ለማለፍ የማይወጣው ዳገት፣ የማይወርደው ቁልቁለት፣ የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም:: ሥልጣን ይዞ በትረ መንግሥት ለመጨበጥ፣ነግዶ የብዙ ብዙ ለማትረፍ፣ ሥራ ለመቀጠርና ለመቅጠርም ሆነ ፍርድ ለመፍረድና ለማስፈረድ የሚጓዝበት መንገድ ከእውነት ይልቅ ሐሰትን የተከተለ ነው:: ከእግዚአብሔር የሆነች እውነት እንደ ድሪቶ የትም ተጥላ ከዲያብሎስ የሆነች ሐሰት ግን በሰዎች ጭንቅላት ላይ መንበሯን ዘርግታ ተደላድላ ትታያለች::

የሐሰት መንገድ እንደ ዘመኑ ቴክኖሎጂ እየረቀቀና እየተወሳሰበ እንደ እውነት ለመቆጠር የሰውን ኀሊና ግራ በማጋባት ላይ ይገኛል:: ሐሰቱን እውነት ነው ብሎ ለማሳመን ዓይኑን በጨው ታጥቦ የሚቀርበው ብዙ ነው:: የዕድሜ ደረጃን ለማስቀነስ አልፎ አልፎም ለማስጨመር የሚደረገው ጥረት የአደባባይ ምሥጢር ከሆነ ሰንበትበት ብሏል:: ሽቅብ ማደጉ ፣ የዕድሜ ባለጸጋ መሆኑ ተጠልቶ እንደ ካሮት ቁልቁል መውረድ የተመረጠበት አስጸያፊ ሥራ:: ሆስፒታሎችን፣ ማዘጋጃ ቤቶችና የቀበሌ ጽ/ቤቶችን ፋታ ከነሷቸው ጥያቄዎች አንዱ የዕድሜ ጉዳይ ነው:: ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት ሥልጣን ያላቸው አካላትም የባለጉዳዮቻቸውን አመጣጥ ስለሚያውቁ በቀጠሮ ያመላልሷቸዋል:: እንዲህ የሚያደርጉትም «በእግርህ ብቻ አትምጣ በእጅህም ና::» ለማለት ነው::

በየመሥሪያ ቤቱ የሥራ ማስታወቂያ በወጣ ቁጥር መስፈርቱን አሟልቻለሁ ለማለት ከተመረቁ ዓመት ሳይሞላቸው የአምስትና የአሥር ዓመት የሥራ ልምድ አስጽፈው ደረታቸውን ነፍተው የሚቀርቡ ጥቂቶች አይደሉም:: ከየት መጣ? የሚያጠያይቀውም ይኸው ነው:: በጉቦ በመማለጃና በዝምድና የሚሠራው ሥራ ብዙ ነውና:: በዚህ ዓይነት ብዙዎችን የሚያስለቅስ የሚያሳዝንና የሚያበሳጭሥራ ስለሚሠራ የፍትሕ ያለህ እያለ የሚጮኸውና የሚቆዝመው ሕዝብ ጥቂት አይደለም:: ዓለማችን ክፉ ካላደረጉ በማይተኙ፣ ካላሰናከሉም በማያንቀላፉ ሰዎች በመሞላቷ ችግሩ እየተባባሰ እንጂ እየቀለለ አይደለም:: ምሳ 4÷17::

በዓለማችን ፍርድ ቤቶችንም ሆነ ከቀበሌ ጀምሮ ያሉትን የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን ታማኝነት እንዲያጡ ካደረጋቸው ነገሮች አንዱና ዋነኛው የጉቦ ቅሌት ነው:: ገንዘብ የሌለው /ጉቦ የማይሰጥ/ የእውነት ያለህ እያለ እየጮኸ በመጣበት መንገድ እያለቀሰ ይመለሳል እንጂ አይፈረድለትም:: ወይም በቀጠሮ ተጉላልቶ ሰልችቶ እንዲተው ተፅዕኖ ይደረግበታል:: ሴቶች ከሆኑ ደግሞ ምናልባት የገንዘቡ ነገር ባይሳካላቸው ራሳቸውን እንደ ገጸ በረከት እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ:: አለበለዚያም በዘመድ በአዝማድ፣ በአምቻ በጋብቻ ለማስፈጸም መሯሯጡ መንከራተቱ የማይቀር ጉዳይ ነው::

አጥር ለማሳጠር፣ ቤት ለማሳደስ ወይም አዲስ ቤት ለመሥራት የግድ ከከተማ ልማትና ከማዘጋጃ ቤት ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል:: ይሁን እንጂ ዲዛይኑን ለማስጸደቅ ባለጉዳዮች ብዙ ውጣ ውረድ ያጋጥማቸዋል:: መፍትሔው ግን አንድ ነው:: ይኸውም በጉቦ መገላገል:: ይኸም ብቻ አይደለም:: ተቋራጩ ከዲዛይን ውጪ ለሚሠራውም ሥራ መሐንዲሱ ተባባሪ የሚሆነው በጉቦ ብቻ ነው:: ነገሩ ሁሉ «እከከኝ ልከክህ::» ሆኗል:: ሰው ምን ይለኛል? እግዚአብሔርስ ? የሚለው ነገር ከጠፋ አያሌ ዘመናት ተቆጥረዋል::

ነጋዴው ከጉምሩክ ለሚያወጣው ዕቃ ሊከፍል የሚገባው ቀረጥ የሚቀንስለት « ከትርፉ እንካፈላለን::» በሚል ፈሊጥ ነው:: «ከቀረጡ ይኽንን ያህል ካስቀነስክልኝ እኔ ደግሞ ይኽን ያህል እሰጣለሁ »



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በሚለው ከተስማሙ በኋላ ሁሉ ነገር በምሥጢር ይፈጸማል:: በእውነት የሚሠ ራም የሚያሠራም በመጥፋቱ ሁሉም እንደ አማራጭ አድርጐ የተቀበለው እና ያጸደ ቀው መንገድ ይኸው ሆነ::

ያልታመመውን ጤነኛውን ሰው ሻል ያለ ከተማ እንዲመደብ እገሌ እንዲህ ዓይነት በሽታ አለበትና አሁን ያለበት አካባቢ አይስማማውም በማለት በሐሰት ብዕር የሚከትበው የጤና ባለሙያም ያለ ጉቦ የሚንቀሳቀስ ዓይነት አይደለም:: ሲመ ረቅ እጁን አንሥቶ የገባውንቃል ወደ ጐን በመተው ብቻ ሳይሆን ፈጽሞ ረስቶ በየ ጤና ተቋሚቱ የሚሠራው ሥራ ትዕግሥት ለሌለው የሚያበሳጭ ትዕግሥት ላለው ደግሞ የሚያሳዝን ነው:: እጅግም የበዛ ባይሆን አልፎ አልፎ በጐን ጉቦ ተቀብለው የመበቀያ መሣሪያ የሚሆኑ፣ መዳን የሚችለውን በሽተኛ ያልሆነ መርፌ ወግተው ከዚህ ዓለም የሚያሰናብቱ ባለሙያዎች አሉ::

በየመሥሪያ ቤቱ የወጣውን እና የገባውን ገንዘብ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲያጣራ የሚላክ ኦዲተር ታጥቦ ታጥኖ በፍቅር የሚቀበለው እንደተለ መደው ያው ጉቦ ነው:: ከዚህ በኋላ የሚ ቀርቡትን የሐሰትመረጃዎች ሁሉ ተቀብሎ ባለዕዳውንነፃ ያደርገዋል:: ጉቦ ካልበላ ግን ትክክለኛውን መረጃ እንኳን አልቀበልም እያለ ያስቸግራል::

ለአብነት ያህል እነዚህን ዘረዘ ርናቸው እንጂ በሐሰት የሚሠሩት ሥራ ዎች እንዲህ በቀላሉ ተዘርዝረው የሚያበቁ ዓይነት አይደሉም:: በየሥራ መስኩ የግፍን እንጀራ የናቁ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ቢኖሩም የሐሰት እንጀራ እየበሉ የሚያገሱ ሰዎች ግን ቁጥራቸው እጅግ እየበዛ ነው:: የሐሰት አባት የዚህ ዓለም ገዥ ዲያብሎስ በጐ ኅሊናን ደምስሶ የሰው ልጅ በሐሰት ጐዳና እንዲጓዝ እያደረገው ነው:: « የሐሰት እንጀራ ለሰው የጣፈጠ ነው:: » ምሳ. 20÷17 እንዲል:: አስቃይተው ካልገዙ ፣ቀምተው ካልበሉ፣ ፍርድ ካላጓደሉ፣ ድኻውን ካልበደሉ እና ጉቦ ካልተቀበሉ ኑሮ የኀዘን ጥላሸት የቀባቻቸው የሚመስላ ቸው በዝተዋል:: ከችግር አትላቀቅ ተብሎ በሕግ የተፈረደበት ይመስል ድኻው ማኅበረሰብም እንደዚህ ባለው በሐሰት የተመሰቃቀለ ዓለም መኖር አቅቶት በማልቀስ ላይ ይገኛል:: እኛስ ከየትኛው ወገን እንሆን?

በእኩል ደሞዝ ከተቀጠሩት መካ ከል አንደኛው ከየት አመጣው ሳይባል በአጭር ጊዜ ውስጥ መኪና ገዝቶ፣ ቤት ሠርቶ፣ደግመህ ከለበስከው ትሞታለህ የተባለ ይመስል ዛሬ የለበሰውን ነገ አሸቀ ንጥሮ ሲጥለው ማየት ለአንዳንዶች መልስ ያጣ ጥያቄ ሆኗል:: ይባስ ብሎም ያው ሰው የትናንት ጓደኛውን « ምነው ወን ድም አትሻሻልም እንዴ?» ብሎ ሞራሉን ይነካዋል:: መሻሻል በጉቦ! ይህ እንዲህ ቢሆንም በአንድ በኩል ደግሞ እንኳን ከሌሎች ሊቀበሉ ቀርቶ ካለቻቸው ከፍ ለው የሚመጸውቱ፣ቀደው የሚያለብሱ፣ ቆርሰው የሚያጐርሱ የጽድቅ አርበኞች አሉ ::

ሰው በሐሰት መንገድ እንዲጓዝ የሚያደርገው የፈቃደ ሥጋው ማየል ነው:: በብልቶቹ ውስጥ ከሚዋጉት ምኞቶች የተነሣ ይፈተናል:: ያዕ 4÷1:: በሥጋ ምኞትም እየተሳበና እየተታለለ የመቀበ ሪያውን ጉድጓድ ይምሳል:: « ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል፤ ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች:: ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች » ያዕ 1÷14:: የሰው ልጅ ሆዱን ስለሚያመልክና በምድር ያለውን ኃላፊውንና ጠፊውን ብቻ ስለሚመለከትም ይወድቃል :: « አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ መጨረሻቸው ጥፋት ነው፣ ሆዳቸው አምላካቸው ነው ፣ ክብራቸው በነውራቸው ነው፣ ሐሳባቸው ምድራዊ ነው:: » ፊል.3÷18 ::

ክርስቲያኖች ግን አገራቸው በሰማይ ፣ መሆኗን ሲለሚያውቁ በዓለም ነገር ተጠላልፈው አይወድቁም :: ፊል 3÷19 ምክንያቱም እውነተኞች ክርስቲ ያኖች ከዓለም ተመረጡ እንጂ ከዓለም አይደሉምና :: ዮሐ 15÷19 መማለጃንና ጉቦን ስለሚጠሉም በሕይወት ይኖራሉ:: ምሳ 15÷27 መማለጃ ዓይነልቡናን እንደ ሚያሳውር፣ የማስተዋል ዓይኖችንም እንደ ሚጋርድ ስለሚያውቁ እንደ እግዚአብሔር ቃል ጸንተው ይኖራሉ:: «መማለጃን አትቀ በል፣ መማለጃ የዓይናማዎቹን ሰዎች ዓይን ያሳውራልና :: » ዘጸ 23÷8 ::

በዚህች ዓለም በመረቧ ሳይተበ ተቡ በወጥመዷም ሳይያዙ የሚኖሩ ÷ፈተና ዋንም የሚያልፉ ሰዎች ባለማለፍ ጸንታ የምትኖረው የእግዚአብሔር መንግሥት የእነርሱ ናት « አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል ? በተቀደሰው ተራራህ ማን ይቆማል? ...ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፣ ...በንጹሑ ላይ መማለጃን የማይቀበል :: » ይላል:: መዝ.14÷1-5 ክርስቲያኖች ከዓለም ትብትብ ራሳቸውን አግልለው እውነትን በመሻታቸው የማጭበርበር በሽታ በተጠናወ ታቸው ሰዎች ዘንድ « ወይ አይበላ ወይ አያስበላ » ተብለው ይተቻሉ:: ይሳደባሉ:: «ግርዶሽ ፣ አጉል ሐቀኛ ወዘተ.. »የሚል ቅጽልም ይቀጸልላቸዋል::

በአጠቃላይ ጉቦ ፍርድ እንዲጣ መም ቀጠሮም እንዲራዘም ያደርጋል:: እውነትን ይሸፍናል፤ ሰዎችን ያበላሻል ፤ ትክክለኛነትን ያስቀራል ፤ ዳኞችንና የተለያዩ ባለሥልጣኖችንም ያስነውራል:: ዘጸ 16÷19 ፣1ኛሳሙ 8÷3፣ 12÷3፣ መዝ 25÷10፣ ኢሳ 33÷15፣ አሞ 5÷12::

ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን የጣላ ቸው የማይገባቸውን ክብር ጉቦ አድርጐ በመስጠት ነው:: ዘፍ3÷1-8 አቤሜሌክ ሰባ የሚሆኑትን የአባቱን የጌዴዎንን ልጆች ባንድ ድንጋይ ላይ ያሳረዳቸው ለምናምንቴ ዎችና ለወሮበሎች ጉቦ ሰጥቶ ነው:: መሳ. 9÷4:: በኤልዛቤል ትእዛዝ ናቡቴን ያስገደሉ ከበርቴዎችና ሽማግሌዎች «ናቡቴ ንጉሡንና እግዚአብሔርን ሰድቧል» ብለው በሐሰት የሚመሰክሩ ምናምንቴዎችን የገዟቸው በገንዘብ ነው:: 1ኛ ነገ.20÷8-16 ሐማ መርዶክዮስን እንደዚያ አምርሮ የጠላው አይሁድንም ለመበቀል ንጉሡን እስከማስፈቀድ የደረሰው የማይገባ የክብር ጉቦ ስለቀረበት ነው:: አስቴ.3÷5:: ይሁዳ ጌታን አሳልፎ የሰጠው ሠላሳ ብር ጉቦ ተቀብሎ ነው:: ማቴ 26÷16:: የጌታን መቃብር ሲጠብቁ የነበሩት ጭፍሮች ትንሣኤውን እንደይሰብኩ አንደበታቸው የታሰረው፣ አፋቸውም የተዘጋው ጉቦ በመብላታቸው ነው:: ማቴ 28÷11-15 ድሜጥሮስ የተባለው አንጥረኛ ቅዱስ ጳውሎስን የተቃወመው ጣዖት እየሠራ በኃጢአት የሚያገኘው ትርፍ እንደሚቀ ርበት ስላወቀ ነው:: የሐዋ 19÷24 ጉቦም በኃጢአት የሚገኝ ትርፍ ነው:: «ትርፍ ለማግኘት የሚሳሳ ሰው የራሱን ቤት ያውካል፤መማለጃን የሚጠላ ግን በሕይወት ይኖራል::» ምሳ 15÷27::

ጉቦ የክፉዎችና የሐሰተኞች ጐዳና በመሆኑ ምንም ይሁን ምን አንጓዝበ ትም ::« በኃጥአን መንገድ አትግባ÷ በክፉ ሰዎችም ጐዳና አትሂድ :: ከእርሷ ራቅ አትሂድባትም ፤ ፈቀቅ በል ተዋትም:: ክፉ ካላደረጉ አይተኙምና ፤ካላሰናከሉም እንቅ ልፋቸው ይወገዳልና :: የኃጢአትን እንጀራ ይበላሉና ፣ የግፍን ወይንጠጅ ይጠጣሉና ::» ምሳ.4÷14-17 እንደተባለ :: ብልፅግ ናቸውንም አይተን ልንቀና አይገባም :: « በክፉዎች ላይ አትቅና ፣ዓመፃንም በሚያደ ርጉ ላይ አትቅና ፤እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና ፣ እንደ ለመለመ ቅጠልም ይረግፋሉና:: በእግዚአብሔር ታመን፣ መልካምን አድርግ፣ በምድርም ተቀመጥ ፣ታምነህም ተሰማራ :: በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፣ የልብህን መሻት ያደርግልሃል:: .... እንዳትበድል አትቅና:: መዝ 36÷1-4፣ 8:: ተብሏልና የተደላደለ በሚመስል ኑሮአቸውም አንሰናከል:: « እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር ያለ ጥቂት ነገር ሁከት ካለበት ከብዙ መዝገብ ይሻላል:: የጐመን ወጥ በፍቅር መብላት የሰባ ፍሪዳን ጥል ባለበት ዘንድ ከመብላት ይሻላል::» ምሳ 15÷16 በመሆኑም ይህንን ሁሉ አውቀን በእውነት ጐዳና እንድንጓዝ ፣የእውነትንም እንጀራ እንድንበላ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን፣ አሜን::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ

## የንዋየ ቅድሳት ዝርፊያ ከትናንት እስከ ዛሬ

ክፍል 3 ከኤፍሬም እሸቴ

ባለፉት ሁለት እትሞች ቤተክርስቲያናችን በተለይ ንዋየ ቅድሳትን በተመለከተ የደረሰባትን ችግር ማስነበባችን ይታወሳል:: ከ1933 ዓ.ም በኋላም ቢሆን ቤተክርስቲያን የንዋየ ቅድሳት ጥበቃን በተመለከተ ብዙ መሻሻል ያደረገች አትመስልም:: ለዚህም አብነት የሚሆነን የንዋየ ቅድሳቱ ዝርፊያ እስከአሁን ድረስ አለ መቆሙ፣ ይልቁንም ከዓመት ዓመት እየበረታ መሄዱ ነው:: ምክንያቶች ይሆኖሉ ተብለው ከሚታሰቡት መካ ከል የሚከተሉትን እንጥቀስ:-

1ኛ- የትምህርት ማነስ:-

ቤተክርስቲያን ቃለ ወንጌልን ለልጆቿ በማስተማሯ፣ ምእመናንም መብትና ግዴታቸውን ለይተው በማ ወቃቸው በገንዘባቸው፣ በዕውቀታቸ ውና በጉልበታቸው ለማገልገል ይቅርና አንገታቸውን ለሰይፍ፣ አጥንታቸውን ለመንኮራኩር ለመስጠት ወደኋላ አይሉም:: ነገር ግን የሚያስተምራቸ ውና የሚመክራቸው ሲያጡ ከመንፈሳዊነት ጐዳና ወደ ዓለማዊነት በመሄድ ለቤተክርስቲያናቸው በተለይም ንዋየ ቅድሳትን ለመጠበቅ ሳይበቁ ይችላሉ::

2ኛ-በሌላም በኩል የዘመናዊው ትም ህርት በተጠናከረ መልኩ ወደ ሃገራ ችን መግባትን ተከትሎ የገባው የፀረ ሃይማኖት እግዚአብሔር የለሽ አስተሳሰብ /የኮሙኒዝም ትምህርት/ ምእመናን ለመንፈሳዊ ነገር የነበራቸውን አመለካከት በመቀነሱ ለንዋየ ቅድሳት ይደረግ የነበረውን ጥንቃቄ አስቀረው::

3ኛ- ከ1966 ዓ.ም በኋላ በመጣው የመሬት ሥሪት ምክንያት ቤተክርስቲያን እና አገልጋዮቿ ከነበራቸው ይዞታ በመፈናቀላቸው፣ በዚህም ምክንያት ቅርሶች አደጋ ላይ ወድቀዋል::

4ኛ- ንዋየ ቅድሳት እንዲጠበቁ የተጠናከረ አያያዝ አለመኖሩ ሌላው ትልቅ ጉድለት ነው:: እጅግ ውድ የሆኑ ቅርሶች ያሉባቸው ብዙ ገዳማትና አድባራት የሚደረግላቸው ጥበቃ በጣም አናሳ ነው:: ስለዚህ በእግዚአብሔር ቸርነት ከአደጋ ከመትረፋቸው በስተቀር በሰው ሰውኛ ዓይን ለዝርፊያ የተጋለጡ ሆነዋል::

5ኛ- በገጠሩ አካባቢ የነበረው የሕዝብ አሰፋፈር በ1977 ዓ.ም ወደ መንደር ሰፋሪነት ሲቀየር ምእመኑ ቤተክርስቲያንን ከብቦ ከመስፈር ወደ ሌላ ቦታ መሄዱ አብያተክርስቲያናቱን ያለጠባቂ አቆያቸው:: ይህም ለዘራፊዎች መንገድ ከፈተ::

6ኛ- ከዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ በመንፈሳዊነት ጐራ የሌሉ፣ ለሥጋዊ ጥቅማቸው ብቻ ቤተክርስተያንን የተጠጉ አንዳንድ ሰዎች አባቶቻችን መከራውን ሁሉ ታግሠው ያቆዩትን ንብረት ከሌቦች ጋር በመተባበር አስዘ ረፉቸው:: የዚህም ምክንያቱ የመን ፈሳዊነት መጉደል ነው::

ምክንያቶቹ እነዚህ ብቻ ባይሆኑም ግን ዋናዋናዎቹ ናቸው ብለን እናምናለን:: ይህንን ከዓመት ዓመት እየጨመረ የመጣውን ዝርፊያ ለመቋቋም በመወሰድ ላይ ያለውን እርምጃ በተመለከተ በማስታወቂያና ባሕል ሚኒስቴር የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት የሰጠንን መረጃ ከዚህ ቀጥሎ እናቀርባለን:: በዚህ አጋጣሚም መረጃውን በመስጠት የተባበረንን ድርጅትና የድርጅቱ ሠራተኛ የሆኑትን አቶ በቀለ አበባውን በመጽሔታ ችን ዝግጅት ክፍል ስም እናመሰግና ለን::

### የንዋየ ቅድሳት ዝርፊያን ለመከላከል የተደረገ ጥረት፣ የተወሰዱ እርምጃዎችና የወደፊት እቅድ

ቅርስ፣ ሕዝቦች በረዥም የታሪክ ዘመናቸው የሚያፈሩዋቸው የማንነታቸው መለያና የታሪክና የባሕል አሻራዎች ናቸው:: ኢትዮጵያም በዓለም ውስጥ የረዥም ዘመን አኩሪ ታሪክ ካላቸው ሀገሮች አንዷ በመሆኗ መተኪያ የማይገኝላቸው ብርቅና ድንቅ የሆኑ ታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶች አሏት:: ከእነዚህ ቅርሶቿ መካከል በየአድባራቱና ገዳማቱ የሚገኙ በርካታ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍትና ንዋየ ቅድሳት ይገኙበ ታል::

በእነዚህ ንዋየ ቅድሳት ላይ በጦርነትና ለግል ጥቅም በቆሙ ግለሰቦች አማካይነት በተለያዩ ጊዜያት ስርቆት፣ዝርፊያና ውድመት ተካሂዶባቸዋል:: በተለይም የኢትዮጵያ ታሪካ ዊ እና ባሕላዊ ቅርሶች በውጭ ሀገር እጅግ ተፈላጊ ስለሆኑ አንዳንድ የውጭ ቱሪስቶች ከአንዳንድ ስግብግብ ግለሰቦች ጋር በመመሳጠር በርካታ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍትን እና ንዋየ ቅድሳትን ከሀገር አስወጥተዋል::ለማስወጣት ሲሞክሩም በቁጥጥርና በፍተሻ ተይዘዋል::

ለምሳሌ ያህልም በ1984 ዓ.ም 22 የብራና መጻሕፍት በአንድ የውጭ አገር ዜጋ አማካይነት ከሀገር ሊወጡ ሲሉ በባሕር ዳር የሲቪል አቪየሽን ሠራተኞች ብርቱ ቁጥጥር ተይዘው ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ ተደርጓል:: እንደዚሁም በ1987 ዓ.ም አንድ የስዊዘርላንድ ዜጋ አንድ ጥንታዊ የብራና መጽሐፍ ከሀገር ሊያወጣ ሲሞክር በባሕርዳር ኤርፖርት ፈታሾች ተይዞበታል::

ቀደም ሲል የታሪካዊ ቅርሶች አስተዳደር፣ በኋላም በባሕል ሚኒስቴር የቅርስ ጥናትና ጥበቃ መምሪያ፣ በአሁኑ ጊዜም በማስታወቃያና ባሕል ሚኒስቴር የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት የሀገሪቱን ታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶች ለማጥናት ለመመዝገብ፣ለመጠበቅ፣ለመንከባከብና ለመጠገን ከተሰጠው ኃላፊነት አኳያ የንዋየ ቅድሳትን ምዝገባ፣ ቁጥጥርና፣ጥበቃ በተመለከተ መሥሪያ ቤቱ ከአከናወናቸው ተግባራት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በቅድሚያ ቅርሶችን በዘመናዊ የአሠራር ስልት መመዝገብና ለመዘክርነት በሚያመች መልኩ መያዝ ይኖርባቸዋል:: ቅርሶችን በዚህ ዓይነት መልኩ የመመዝገብ ሁኔታ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት:: በሀገሪቱ ያሉትን የቅርሶች ብዛት ዓይነትና ሥርጭት ለይቶ ለማወቅ ይቻላል:: ይህ ከሆነ በተናጠልም ሆነ በክምችት መልክ የሚገኙበት ቦታ በምን ዓይነት ጥበቃ ወይም አያያዝ ላይ እንደሚገኙ መከታተል፣ እንዳይሸጠ - ፣ እንዳይሰ ረቁና በሕገወጥ መንገድ ከአገር እንደ ይወጡ ለመከላከል ይረዳል:: በተጨ ማሪም ለጥናት ወይም ለኤግዚቢሽን ከሀገር የሚወጡ ቅርሶችን በወቅቱ መመለስና አለመመለሳቸውን መቆጣጠር ይቻላል::

ስለሆነም በመሥሪያ ቤቱ በኩል ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው የታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶችን ምዝገባ የማካሄዱ ተግባር ስለሆነ ንዋየ ቅድሳትን በተመለከተ በ322 ገዳማትና አድባራት በመዘዋወር ከ14 ሺህ ንዋየ ቅድሳት በላይ ተመዝግበው ኮድ ተሰጧቸው በፎቶግራፍ ተቀርፀውና መግለጫ ተሰጥቶባቸው ይገኛሉ:: መመዝገቡ ብቻውን በቂ ባለመሆኑ ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ እንዲ ድረግላቸው ቅስቀሳና ትምህርት ተካሂ ዷል:: ትምህርቱና ቅስቀሳው ከተደረገላቸው መካከል የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ይገኙበታል::

በተለያዩ ጊዜያት በንዋየ ቅድሳት ላይ ስርቆትና ዝርፊያዎች ሲፈጸሙ ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት የትብብር ጥያቄዎች ይቀርባሉ:: ለምሳሌ ያህልም አንዳንዶቹን መጥቀስ ይቻላል:: በግንቦት ወር 1984 ዓ.ም በጎጃም አዝዋ ማሪያም 16 ንዋየ ቅድሳት ጠፍተዋል:: እነዚህ ቅርሶች ቀደም ሲል በቅርስ ጥናትና ጥበቃ በኩል ተመዝግበው ስለነበር ለኢንተርፖል ፎቶግራፋቸውና መግለጫቸው ተልኳል::

በ1986 በደቡብ ወሎ ከላላ ወረዳ ከጋስጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም ባለ ሁለት ቅፅ ስንክሳር በመሰረቁ ሪፖርቱ ለቅርስ ጥናትና በቃ ስለቀረበና ይህም ቅርስ በድርጅቱ በኩል የተመዘገበ፣ በፎቶግራፍ የተቀ ረፀና ኮድ የተሰጠው ስለነበር ከሀገር ውስጥ እንዳይወጣና ተገቢው ፍለጋና ክትትል እንዲካሄድ የቅርሱ ሙሉ መግለጫ ዝርዝር ለጠቅላይ ቤተክ ህነት ጽ/ቤት እንዲሁም በወቅቱ ለነበረው የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስ ቴርና ለፖሊስ ሠራዊት ማዕከላዊ ቢሮ ተልኳል::

በ1987 ዓ.ም በእንደርታ ወረዳ የጨለቆት ደብረ ምሕረት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆኑ 11 ንዋየ ቅድሳት በመሰረቃቸው ከክልሉና ከመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ በተገለጠው መሠረት ድርጅቱ የበኩሉን ክትትል እያደረገ ነው::

እንደዚሁም በ1987 ዓ.ም ጎንደር ዳባት ወረዳ ከደቋ ኪዳነ ምሕ ረት 20 ንዋየ ቅድሳት በመሰረቃቸው በዚህ የስርቆት ተግባር ተጠርጥረው የተያዙት ግለሰቦች ጉዳይ በአስቸኳይ ተጣርቶ የተወሰደው ሕጋዊ እርምጃ ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት እንዲገለጽ ለክልል 14 ፖሊስ ኮሚሽን በወቅቱ ማሳሰቢያ ተጽፏል:: ድርጅቱ የዚህን ውጤት እየተጠባበቀ ነው::

በስጦታ መልክ ከሀገር የሚ ወጠ - ማንኛውም የባሕል ዕቃዎች ፈቃድ የሚሰጠው የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅት ስለሆነ አንዳንድ ታሪ ካዊና ባሕላዊ የሆኑ ቅርሶችን በተለ ይም ንዋየ ቅድሳትን በስጦታ የባሕል ዕቃዎች ስም ከሀገር ውስጥ ለማስወጣት የሚደረገውን ሙከራ ድርጅቱ እየተከላከለ ነው:: በተለይም የብራና መጻሕፍት፣ ጥንታዊ መስቀሎችና ሌሎችም ንዋየ ቅድሳት ከሀገር እንዳ ይወጡና ወደ ፈቃድ ጠያቂዎቹም እጅ እንዳይመለሱ በመከላከል የተደረገው ጥረት የሚያበረታታና ወደፊትም በተጠናከረ መልኩ የሚቀጠል ይሆናል::

በተለያዩ ጊዜያት በጦርነት እና በሌሎችም ምክንያቶች ከሀገራ ችን የወጡ ቅርሶች እንዲመለሱ በዮኔስኮ በኩል ለሚደረገው ጥረት ሀገራችን ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የቅርስና የሙዚየም ድርጅቶች አባል በመሆ ንና ስምምነቶችን በመፈራረም እንቅስቃሴዎች ተካሄደዋል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ በውጭ ሀገር የሚገኙ የብራና መጻሕፍትን ዝርዝርና ብዛት ለማወቅ ከተለያዩ ተቋማትና ኤምባሲዎች መረጃ ማግኘት የሚቻልበት ጥናት ተጀምሯል::

የንዋየ ቅድሳትን በአጠቃላይም የታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶ ችን ስርቆትና ዝርፊያ ለመከላከል ዋነኛው መፍትሔ አሁንም ምዝገባ ቁጥጥርና ትምህርታዊ ቅስቀሳውን ይበልጥ ማጠናከር ነው:: ይህም የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅቱ በሠለጠነ የሰው ኃይልና በጀት አቅም አኳያ ተግባራዊ የሚሆን ነው:: ድርጅቱ በሠለጠነ የሰው ኃይልና በጀት እየተጠናከረ ሲሄድ የቅርሶች ምዝገባ ትምህርታዊ ቅስቀሳና፣ ቁጥጥር ባልተካሄደባቸው አካባቢዎች እንቅስቃሴው ይቀጥላል:: አብዛኛው ቅርሶቻችን የሚገኙት በሃይማኖት ተቋማት በመሆኑ እነዚህን ብርቅና ድንቅ ቅርሶቻችንን ተንከባክበው እዚህ ያደረሱት የሃይማኖት አባቶችና አገልጋዮች ናቸው:: ይሁን እንጂ በሳይንሳዊ የቅርሶች እንክብካቤና ጥበቃ ላይ የተመሠረተ የሙያ ግንዛቤና አሠራር ስለሌላቸው ትምህርቱና ቅስቀሳው ይበልጥ የሚጠናከርበት ሁኔታ በድርጅቱ በኩል ይቀየሳል::

ታሪካዊ እና ባሕላዊ ቅርሶቻችንን ከዝርፊያ ከስርቆትና ከሌሎችም ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች መከላከልና መንከባከብ የሚቻለው ከቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ጋር ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦችና ተቋማት ሁሉ የተጠናከረ ግንኙነት ሲፈጥሩና በተለይም ኅብረተሰቡ ስለ ቅርሶች የሚኖረው ግንዛቤ እንዲዳብር ሲደረግ ነው::

በአጠቃላይ የታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶቻቸው ባለቤት የሆኑት የኢትዮጵያ ብሔርብሔረሰቦች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚገኙ የፖሊስ ኮሚሽኖች፣ የጉምሩክና ሌሎችም የመገናኛ መሥመር የፍተሻ ጣቢያዎች ከቅርስ ጥናትና ጥበቃ እንዲሁም በየክልሉ ከሚገኙ የባሕልና ማስታወቂያ ቢሮዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊፈጥሩ ይገባል:: በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ድርጅትና በክልል የባሕልና ማስታወቅያ ቢሮዎች በኩል ለሚካሄዱ የታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶች ምዝገባና ቁጥጥር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ግንባር ቀደም ሆና የማስተባበር ኃላፊነት ይጠበቅባታል::

## ክርስቲያናዊ /ምሳሌያዊ/ አባባሎች

..... ትልቅ ብልሃት - ለትምህርት መትጋት

..... ሃይማኖት ያለፍቅር - ጸሎት ያለግብር አይሠምርም

..... ማየት ከመልአክ - መቀበል ከአምላክ

..... ምድር በዛፍ - ሕግ በመጽሐፍ

..... ስለ ትእግሥቱ ይደሙ - ስለ ሥርዓቱ ይቆሙ

..... አለመባ - ቤተክርስቲያን አትግባ

..... ነቢያት በቀየሱ - ሐዋርያት ገሠገሡ

..... አንድ ሎሌ - ለሁለት ጌታ አይገዛም

..... አንተ አስበሃል - ሥላሴ ያውቁልሃል::

መ/ር ሉሉ ኃይሌ
/ሐረር/



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# የቤተክርስቲያን ታሪክ

ካለፈው የቀጠለ /በብርሃኑ ጎበና/

## የሮማ ቄሳሮችና ክርስቲያናት

ክብር የማይጠግቡት ኩንስ ንሶቹ የሮም ቄሳሮች እንደ አምላክ ራሳቸውን በሚቆጥሩባት፣ በሕዝቡም ዘንድ እንደ አማልክት በሚታዩባትና በሚመለኩባት ሮማ የወንጌል መስበክ የማይታሰብ መስሎ ቢገመትም ነፍሳቸውን የወደዱ፣ ዓለምን የጠሉ ክርስቲያኖች የሰላም ችቧቸውን እያንቦገቦጉ የክሕደት ጽልመት ለጋረደው ሕዝብ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን አበሩለት:: ያለ ፍርሃት ክርስቶስን ሰበኩ::

የሮም ቄሳሮች ክርስቲያኖ ችን እጅግ ይጸየፏቸውና ይጠሉአቸው ነበር:: የጥላቻቸው መንሥ ኤም ቄሳሮቹ በሕይወት እያሉ ምስላቸውን አስቀርፀው ሕዝቡ እን ደ አምላክ እያያቸው ለምስላ ቸው እንዲሰግድ ያደርጉ ነበር:: ዳሩ ግን ክርስቲያኖች ሊሰገድለትና ሊመለክ የሚገባው አምላክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ለቄሳሮቹ ምስል መስገ ድም ሆነ እነርሱን አማልክት አድርጎ ማመን ክሕደ ትና ከጌታም ጋር የሚያጣላ መሆ ኑን ሲያስተምሩ ብዙዎች ትምህር ታቸውን ተቀብለው ተግባራዊ በማ ድረጋቸው ቄሳሮቹ ክርስቲያኖችን አምረው ጠሉ ::

እንደ ኔሮን ቄሳር ያሉት የሮማን ከተማ በእጅ አዙር በባለ ሚሎቻቸው እንድትቃጠል እያደ ረጉ አማልክቶቻችን በክርስ ቲያኖች ምክንያት አዝነውና ተቆ ጥተው እሳት ከሰማይ አዘንመው ከተማይቱን አቃጠሉ:: እያሉ ዓይን ያወጣ የበሬ ወለደ ዓይነት ተረት እየተረቱ ሕዝቡን በክርስቲያኑ ላይ እንዲነሣሣ አድርገው ብዙ ክርስቲያኖችን በኢሰብአዊ ድርጊት ፈጅተዋል::

ብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጴጥ ሮስና ቅዱስ ጳውሎስም ሰማዕትነ ትን የተቀበሉት በዚሁ በኔሮን ቄሳር ዘመነ መንግሥት ነው:: ከኔሮን ቄሳር በኋላ የተነሡት እነ ትራጃንም በጭካኔያቸው የበለጡ ሆኑ እንጂ ያነሡ አልነበሩም:: በክርስቲያኖች ላይ የመከራ ዱላቸውን አሳርፈዋል:: ክርስቲያኖችን ለተራብ አንበሳ አስወርውረዋል:: ለምሳሌ የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ተማሪ የነበረው አግናጥዮስ /ምጥው ለአንበሳ/ ለአንበሳ የተሰጠው በዚሁ በትራጃን ዘመነ መንግሥት ነው:: ይህ አግናጥዮስ በቤተክርስ ቲያን ትውፊት በማቴ18.ቁ2 ላይ የተጠቀሰው ሕፃን እንደሆነ ይታመ ናል:: በአንጾኪያም ሁለተኛ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሏል[11]:: ከሮም ቄሳሮች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ ጠንከር ያለ የመከራ ዱላ ያሳረፈውና በእኩይነቱም አውራ ተዋናይ የነበ ረው ዲዮቅልጥያኖስ የተባለው ቄሳር ነው:: ዲዮቅልጥያኖስ ተራ ወታደር ሳለ ሀገሩ ከፋርስ መንግ ሥት ጋር በተዋጋች ጊዜ ያሳየው ጀብዱና የጀግንነት ሙያው በመላ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ውስጥ ለመታወቅ አብቅቶታል:: መልካም ዝናንም አትርፎለታል:: እንደአጋጣ ሚም ሆኖ በዘመኑ የሮም መንግሥት አስተዳደር ከስፋቱ የተነሣ ተዘበራርቆ ወደ መውደ ቁም አዘንብሎ ስለነበር ዲዮቅልጥ ያኖስ በትረ መንግሥቱን ይዞ አውግስጦስ የሮም ንጉሠ ነገሥት ተባለ::

በ296 ዓ.ም የፋርስ መንግሥት የሮምን የግዛት ድን በር በመጣሱ ጋሌሪዮስ የሮም የጦር ሠራዊት አበጋዝ ሆኖ ወደ ፋርስ ዘመተ:: ነገር ግን በውጊያው ላይ የፋርስ ጦር ኃይሉ የሮምን ኃይል ድል አደረገው:: ጋላሪዮስም ተማርኮ ወደ ፋርስ ከተወሰደ በኋላ አምልጦ አንጾኪያ ገባ:: በዚህ ጊዜ ዲዮቅልጥኖስም ወደ ፋርስ ዘምቶ ስለነበረው ሠራዊቱና ስለ አማቹ ስለጋሌሪዮስም በደኅና መመለስ ካህናተ ጣዖቱን ለማስጠንቆል ወደ ቤተ ጣዖቱ ሄደ:: ከዚያም ለጣዖቱ ለአጵሎስ የተለመደውን ገፈራ ካቀ ረቡ በኋላ ከካህናቱ መልስ አገኛ ለሁ ብሎ ቢጠባበቅ ሳይነግሩት ቀሩ:: ምክንያቱን ቢጠይቅ ከተከታ ዮችህ መካከል በትእምርተ መስቀል የሚያማትቡ /ክርስቲያ ኖች/ ስላሉ ነው አሉት:: በዚህ ተናዶ በክርስቲያኖች ሁሉ ላይ የሞት ቅጣት እንዲፈጸምባ ቸው አዘዘ ::

ጋሌሪዮስም ወደ ግዛቱ በተ መለሰ ጊዜ ካህናተ ጣዖቱ ተሰብ ስበው ድል የሆነው በክርስቲያኖች መኖር መሆኑን አሳመኑት:: እርሱም የዲዮቅልጥያኖስ አጫፋሪ ሆኖ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በጦር ሠራዊት ውስጥ እንዳይገኝ አዘዘ:: በሱ የሚመራ፣ ክርስቲያኖችን እያ ደነ የሚያጠፋ የፀረ ክርስቲያን ድርጅት አቋቋመ:: ብዙ ክርስቲያኖችንና የክርስቲያን ቅርሶቻቸ ውም እንዳልነበሩ ሆኑ ::

ክርስቲያኖች ሥቃይ ሲጸናባ ቸው ወደ ቤተ ጣዖት እንዲመ ለሱ በማለት ሳይገደሉ ሕዋሶቻ ቸውን እየቀነጣጠሱ ያሰቃዩ ዋቸው ነበር:: የሚቆራርጡትን አካላቸውንም እየወሰዱ ለጣዖቶ ቻቸው ያጤሱት ነበር:: ክርስቲያ ኖች ግን ይህ ሁሉ ግፍ ሲፈጸምባ ቸው መከራውን ተሰቅቀው ከእም ነታቸው ወደ ኋላ አላሉም:: እንዲ ያውም ሲቆርጡት ከሥሩ እንደሚ ያቆጠቁጥ ዛፍ ቁጥራቸው እየጨ መረ ሔደ[13]::

«ክርስቲያንና ሚስማር አንድ ናቸው ሁለቱም ሲመቱዋቸው እየ ጠበቁ ይሄዳሉ » እንደተባለው በሚደርስባቸው መከራ ሁሉ አልተ በገሩም እንዲያውም መከራው አጸ ናቸው:: ዲዮቅልጥያኖስ ግን በኒቆሚዲያ ከተማ በሚገኘው ቤተ መንግሥቱ ሰገነት ላይ ሆኖ የከተማይቱ ክርስቲያኖች ሲታረ ዱና አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠ ሉ ይመለከት ነበር::

የዲዮቅልጥያኖስ የበረታ ዱላ ቤተክርስቲያንን ከጉዞዋ አልገታ ትም የሲኦል ደጆች አይችሏትም ተብሎላታልና:: ታሪኳን በደሟ እያቀለመች በግበበምድር መጓዟዋን ቀጠለች::

## ግበበምድር

በገጸምድር እንዳይኖሩ ራሳቸ ውን አማልክት አድርገው በቀረቡ የሮም ነገሥታት የተፈረደ ባቸው ክርስቲያኖች ዋሻ ፈልፍ ለው ጉድጓድ ቆፍረው በዋሻ በፍርኩታ ውስጥ መኖርና ትምህር ታቸው ንም ማስፋፋት ቀጠሉ:: ቤተክር ስቲያን ካታኮምብ /ግበበም ድር/ ከገባች በኋላ ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል:: በዚህ ዋሻ ውስጥ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሰማዕታትን አፅም እየሰበሰቡ
ጸሎት ይጸልዩ ነበር።
በግበበምድር ቤተመጻሕፍት
ባለመኖሩ ወደ ውጭ ወጥቶ ለመፈ
ለግና ለማዘጀትም ነፃነት ስላልነበ
ራቸው ክርስቲያኖች ይማማሩ የነ
በሩት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አን
ዳንድ ምሳሌዎችን በሥዕል በማስ
ፈር ነበር። የመሣያ መሣሪያ በግበ
በምድሩ ስለማያገኙ ሥዕሎች የሚ
ሣሉት በዋሻው ዙሪያ በአመድና
በከሰል ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ያመኑበትን በእርሱም አምነው የሞ
ቱትን ሁሉ የሚያድናቸው ቸርና
ታማኝ ጠባቂ መሆኑን ለማስረዳት
እረኛው በጉን እንደ ተሸከመ አድ
ርገው ይስሉ፣ በብሉይ እና በሐዲስ
ኪዳን የሠፈሩትን ታሪኮችም በዋ
ሻው ዙሪያ በመሣል በሥዕላዊ ገለጻ
ልጆቻቸውንና አዲስ አማንያንን
ያስተምሩ ነበር።

በዚህ ዘመን ክርስቲያኖች
ዓሣን እርስ በርሣቸው የሚተዋ
ዋቁበት መለያቸው አድርገው ይጠ
ቀሙበት ነበር። በጥንት ግሪኮች
ዓሣ ሲሉ «ኢኽቲስ» ይላሉ የዚህ
ፊደል እያንዳንዱ ምሕፃር ቃልነት
አለው። ኢ-ኢየሱስ ።ኽ-ኽርስቶስ።
ቴ-ቴውአዮስ /የእግዚአብሔር ልጅ
/ ። ስ-ስቴር /መድኅን/ ለማለት
ሲሆን በተገናኝ ሲነበብ «ኢየሱስ
ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር
መድኅን» ማለት ነው።

ቤተክርስቲያን እስከ ታላቁ
ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት
ድረስ በካታኮምብ /ግበበምድር/
ተጉዛለች። በዚህም ጉዞዋ ብዙዎ
ችን ከሞት ወደ ሕይወት ስባ
ለች። ክርስቲያኖችም የማይበገሩና
ለዓለማቸው ጽኑአን እና እስከ ሞት
ድረስ የታመኑ መሆናቸውን አስመ
ስክረዋል።

## መፍቀሬ እግዚአብሔር ቆስጠንጢኖስ

ከሦስት መቶ የመከራና የስደት
ዘመናት በኋላ ቤተ ክርስቲያን
ጥቂት ዕረፍት ያገኘችው በታላቁ
ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት
ነው። በ258 ዓ.ም ዛሬ የዩጐዝ
ላቪያ ግዛት በሆነችው በናይሳን
የተወለደው ታላቁ ቆስጠንጢኖስ
አባቱ ኮስታንዲዮስ እናቱ ዕሌኒ
ይባላሉ። አባቱ አረማዊ እናቱ ክር
ስቲያን ነበረች። ከሕፃንነቱ ጀምሮ
የክርስትና ትምህርት ከእናቱ
ሲማር ያደገው ታላቁ ቆስጠ
ንጢኖስ በሮም ምዕራብ ክፍል
በገላትያ ሲነግሥ ገና የ18 ዓመት
ወጣት ነበር።

በ312 ዓ.ም ቆስጠንጢኖስ
በማክሴንዲዮስ ላይ በዘመተበት
ጊዜ ገና በጉዞ ላይ እንዳለ «በዚህ
ድል ታደርጋለህ» የሚል በመስ
ቀል ቅርጽ የተጻፈ ጽሑፍ በጠፈረ
ሰማይ አየ። በዚህ እየተመራ ሄዶ
ከማክሴንድዮስ ጋር ጦርነት ገጥ
ሞ። በጦርነቱም የቆስጠንጢኖስ
ሠራዊት ድል በማድረጉና ንጉሡ
ማክሴንድዮስም በመሞቱ ቆስጠን
ጢኖስ የማክሴንድዮስ ዕጻ
የነበረውን ጠቅሎ በመያዝ አውግስ
ጦስ ተባለ። ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ
ያየው መስቀላዊ ቅርጽ ያስገኘለ
ትም ተአምራዊ ድል ስለ ክርስ
ትና የበለጠ እንዲመረምርና
እንዲያውቅ፣ክርስቲያኖችንም እንዲ
ወድ ረድቶታል። ሠራዊቱም
በፈረሱ አንገት፣በጋሻው እምብርት
የመስቀል ቅርጽ እንዲያደርግ
አወጀ። ከዚያ ጊዜ በኋላ የቆስጠ
ንጢኖስ ጦር ሠራዊት የሚለየው
በመስቀሉ ሆነ።

ቆስጠንጢኖስ ለቤተክርስ
ቲያን ከዚህ በፊት ያልተሰጧትን
መብቶች ሰጥቷል። ቤተክርስቲያን
ከግብር ነጻ እንድትሆን። ከመንግ
ሥቱ ገቢ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያንም
የተወሰነ ድርሻ ንዲኖራት ምንም
እንኳን ጌታ ከሙታን ተለይቶ
የተነሣበት ቀን ዕለተ እሑድ በመ
ሆኗ በክርስቲኖች ዘንድ ከትንሣኤ
ዕለት አንሥቶ የተከበረች ብትሆ
ንም ከ321 ዓ.ም ጀምሮ በመን
ሥት ደረጃ የክርስቲያኖች የበዓል
ቀን እንድትሆንና በንጉሡ ነገሥ
ቱም ግዛት ውስጥ ሥራ እንዳይሠ
ራባት አወጀ።

እናቱ ቅድስት ዕሌኒም
በ327 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ
የጌታን መስቀል ከተቀበረበት
አውጥታለች። ታላቁ ቆስጠንጢኖስ
በ337 ዓ.ም ግንቦት 22 ቀን
በጰራቅሊጦስ ዕለት እሑድ በ54
ዓመቱ አረፈ። እናቱ ንግሥት
ዕሌኒም ያረፈችው በ328 ዓ.ም
ነው።/

.... ይቀጥላል...

# የምድረ ርስት ልጆች ነን

ከማርታ

ምድረ ርስት ለአብርሃምና
ለዘሩ የተሰጠች የተስፋይቱ ምድር
ከነዓን ናት። ዘፍ÷12-7 እሥራኤል
ዘሥጋ እንደ ተስፋ ቃሉ ምድረ
ርስትን ለመውረስ ለብዙ ዘመናት ደጅ
ጠንተዋል። በግብፅ የባርነት ቀንበር
ተይዘው ሳሉ እንኳን የአባቶቻቸው
አምላክ አንድ ቀን ያን ቀንበር ሰብሮ
ነፃ እንዲያወጣቸው የተስፋይቱንም
ምድር እንደሚያወርሳቸው ያውቁ
ነበር።

የአባቶችን ቃልኪዳን ለልጅ
ልጅ የሚጠብቅ አምላክ እግዚአብ
ሔርም እሥራኤልን ፈጽሞ አልረሳቸ
ውም ነበር። ምክንያቱም እርሱ ለአብ
ርሃም የማለውን መሐላውን ቅዱሱን
ኪዳን የሚያስብ አምላክ ነውና።
ሉቃ.1÷72። እግዚአብሔር ለአብር
ሃም እሥራኤል ወደ ግብፅ እንደሚሰ
ደዱ ከአራት መቶ ዓመታትም በኋላ
መልሶ እንደሚያድናቸው ምድረ
ርስትንም እንደሚያወርሳቸው ነግሮት
ነበርና። ዘፍ.15÷13

ጊዜው ሲደርስም እግዚአብሔር
ለሙሴ በደብረ ሲና ተገልጦ ፣ ሕዝቡን
ከግብፅ እንደሚያወጣቸውና ማርና
ወተት የምታፈስውን አገር እንደሚያወ
ርሳቸው ነገረው። ዘጸ.3÷6 ለዚህም
አገልግሎት ሙሴን መረጠው። ምክን
ያቱም ሙሴ ከግብፅ ብዙ ገንዘብ
ይልቅ ስለክርስቶስ መነቀፍን፣ በኃ
ጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ፣ ከእግ
ዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበ
ልን የመረጠ ጀግና ነውና። ዕብ.11
÷26።

እግዚአብሔር በሰጠው አማ ናዊ
ተስፋ መሠረት ግብፃውያንን በአሥር
መቅሰፍት ቀጥቶ በሙሴ መሪነት
ሕዝቡን በተአምራት አወጣቸው። በሰማ
ይም መጋቤ ብሉይ ቅዱስ ሚካኤል
መዓልቱን በደመና ዓምድ ፣ሌሊቱን
ደግሞ በብርሃን ዓምድ ይመራቸው
ነበር። ዘጸ.14÷15-31።

ሕዝቡ ግን ድምፁን እየሰሙ
፣ተአምራቱንም እያዩ በመጠራጠቸው
በበረሀው ማዕበል እየተመቱ በየጐዳናው
ይንጠባጠቡ ነበር። እግዚአብሔርም
«ተአምራቴንና ክብሬን ያዩ እነዚህ
ሰዎች ሁሉ አሥር ጊዜ ስለተፈታ
ተኑኝ ነገሬንም ስላልሰሙ በእውነት
ለአባቶቻቸው የማልሁላቸውን
ምድር አያዩም፣ ከእነርሱም የናቀኝ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሰው ሁሉ አያያትም።» ብሎ ለሙሴ ነገረው። ዘጸ.17÷7 ዘጸ 14÷22፣መዝ.77÷17፣ዕብ.3÷8፣4÷2።

በዚህ ዓይነት ጉዞ ሲወድቁና ሲነሡ ሲጣሉና ሲታረቁ ከቤርሳቤህ በስተደቡብ በሲና ውስጥ ወደሚገኝ ፋራን ምድረ በዳ ደረሱ። ሙሴም እግዚአብሔር ስላዘዘው ምድሪቱን እን ዲሰልሉ አሥራ ሁለት ሰላዮችን ላከ። እነርሱም እርባ ቀን ሰልለው የስን ዴዋን ዛላ የወይኗን ዘላላ ይዘው ተመለሱ ። አንዱ ዛላ ቢታሽ አንድ እፍኝ፣አንዱም ዘለላ ቢጨመቅ አንድ ጽዋ መላ። በዚህም ምድረ ርስት የበረከት ምድር መሆኗን ዐወቁ። « በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን ሕይወ ትንም እስከ ዘላለም አዝዞአልና» መዝ፡ 132÷ 3።

ይሁን እንጂ ከአሥራ ሁለቱ አሥሩ ወደ ማኅበሩ ክፉ ወሬ በማምጣታቸው፣በምድሪቱ ከሚኖሩ ባት ኃያላን የተነሣ የተሰፋዪቱን ምድር መውረስ እንደማይቻል በመ ናገራቸው ማኅበሩ ሁሉ ጮኹ ፣ ሌሊቱንም ሙሉ ሲያለቅሱ አደሩ። በሙሴና በአሮን ላይም አጉመረሙ ። በግብፅ ወይም በምድረ በዳ ምነው በሞትን ኖሮ አሉ። ወደ ግብፅ ባርነት ለመመለስም ወሰኑ። በዚህም ጊዜ ሙሴና አሮን በማኅበሩ ፊት በግም ባራቸው ወድቁ።

ሁለቱ ሰላዮች ካሌብና ኢያሱ ግን ልብሳቸውን ቀድደው «ዞረን የሰለልናት ምድር እጅግ መልካም ናት እግዚአብሔርስ ከወደደን ወተ ትና ማር ወደምታፈስሰው ወደዚች ምድር ያገባናል።..ነገርግን በእግዚአ ብሔር ላይ አታምፁ ፣እንደ እንጀራ ይሆኑልናል። የምድሪቱን ሰዎች አት ፍሩ ጥላቸው ከላያቸው ተገፍፎአል፣ እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር ነው።» ብለው በእምነት ተናገሩ። ዳሩ ግን የሚሰማቸው አላገኙም የእግዚእብ ሔር ክብር ተገልጦ ባያድናቸው ኖሮ በደንጊያ ሊወግሯቸው ነበር። ሕዝ ቡም የሙሴ አማላጅነት ባያተር ፋቸው ኖሮ በቸነፈር ሊጠፉ ነበር።

ሙሴ በመጨረሻ ፈስጋ በተባ ለው ተራራ ራስ ላይ ሆኖ ምድረ ርስትን አሻግሮ አይቶ በመሞቱ አገልጋዩ ኢያሱ በእግሩ ተተክቶ ሕዝቡን መርቶ ዮርዳኖስን በደረቅ ካሻገራቸው በኋላ የተስፋዪቱን ምድር አውርሷቸዋል። ሕዝቡ በቃዴስ በረሀ የኳተኑት ለአርባ ዓመታት ያህል ነበር። የረገፈው ረግፎ ልጆቻቸው ምድረ ርስትን በገመድ ተከፋፍለዋታል። ኢያ.18÷1።

## ማርና ወተት የምታፈስስ ምድር፡-

ምድረ ርስት ማርና ወተት የምታፈስስ አገር መባሏ ፣ ወንዙና ጅረቱ ማርና ወተት የሚያፈስ ሆኖ አይደለም። ማር የተባለ ሕገ ኦሪት ሲሆን ወተት ደግሞ ሕገ ወንጌል ናት። ምሳሌነቱም ማር የነካው ልብስ ለጊዜው ሲያዩት የሚለቅ አይመስ ልም። እንጂ በውኃ ባጠቡት ጊዜ ግን ሙልጭ ብሎ የሚለቅ ነው። በዚሁ ዓይነት ኦሪትም ቀድማ ስትመ ሠረት የምትለቅ ሕግ አትመስልም ነበርና ነው። ወተት /ቅቤ / የነካው ልብስ ደግሞ ለጊዜው ሲያዩት የሚለቅ ይመስላል እንጂ በውኃም በሳሙናም ቢሉት የሚለቅቅ አይደለም። ወንጌልም ቀድማ በመቶ ሃያው ቤተ ሰብ መካከል ስትመሠረት የምትጸና ሕግ አትመስልም ነበር። ይሁን እንጂ ውንጌል የምትሻር የምትለቅ አይደለችም። ምድረ ርስት በማር የተመሰለች ሕገ ኦሪት በወተትም የተመሰለች ሕገ ወንጌል የሚሠራባት የሚነገርባትና የሚፈጽምባት ምድር ስለሆነች ማርና ወተት የምታፈስስ ምድር ተብላለች ማለት ነው። አንድም ሐጋኄ ሕግጋት አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወለደው በዚያ ነውና። ማርና ወተት የምታፈስ ተብላለች፡-

ሀ• ማርና ወተት የምታፈስ ርስት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ። ምክንያቱም፡-

*1ኛ.* በማር የተመሰለ ሕገ ኦሪትንና በወተት የተመሰለች ሕገ ወንጌልን የሠራ አምላክ። እና

*2ኛ.* ለ5500 ዘመናት በኃጢአት መርሮ የነበረው የሰው ሕይወት የጣ ፈጠበት ማር እና የጠወለገውም ሕይወት የለመለመበት ወተት ኢየ ሱስ ክርስቶስ ከእርሷ ተወልዷ ልና።

*3ኛ.* የተስፋይቱ ምድር ፍሬ ስንዴና ወይን ነበረ። እምቤታችንም የማኅፀኗ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ስንዴ ሥጋ ውን መብል፣ ወይን ደሙን መጠ ጥ አድርጎ ሰጥቶናልና።

*4ኛ.* በምድረ ግብፅ የነበሩ እሥራኤል ዘሥጋ ምድረ ርስትን ተስፋ ያደርጉ እንደነበር፣ በሲኦል የነበሩም ነፍሳት ከአዳም ጀምሮ ተስፋቸው እመቤታችን ነበረችና። «አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት። አዳም ከገነት በተሰደደ ጊዜ ተስፋው አንቺ ነበረሽ። » እንዲል ቅዳሴ ማርያም።

*5ኛ.* ኢየሩሳሌም ማለት ሀገረ ሰላም ማለት ነው። እመቤታችንም ሰውና እግዚአብሔር፣ ሰውና መላእክ ትም የተገናኙባት የሰላም መገናኛ ድልድ ይና መሸጋገሪያ በመሆኗ፣ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘባት ሀገረ ሰላም ኢየሩሳሌም ናትና። ቅዱስ ኤፍሬም «ዛቲ ይእቲ ኢየሩሳ ሌም ሀገሮሙ ለነቢያት ወማኅደረ ፍስሓ ሆሙ ለኵሎሙ ቅዱሳን የቅ ዱሳን ሁሉ የደስታ ማደሪያ የነቢያት ሀገረ ትንቢታቸው ኢየሩሳ ሌም ይህች ናት።»ያለው እመቤታ ችንን ነውና።

*6ኛ.* እሥራኤል ምድረ ርስትን በገመድ /በሐብል/ እንደተከፋፈሏት /አንዳገኟት/ እመቤታችንንም ነቢ ያት በሐብለ ትንቢት ፣ሐዋርያት በሐብለ ስብከት ፣ሊቃውንት በሐብለ ድርሰት አግኝተዋታልና። ካህናት ደግሞ በሐብለ ማኅሌት በሐብለ ሰዓ ታትና በሐብለ ቅዳሴ ሲያገኟት ምእ መናንም ጐልጐታን፣ ውዳሴ ማር ያምን፣ አርጋኖን ወዘተ... » በመድ ገም በሐብለ ጸሎት ያገኟታልና።

ለ• ርስታችን ለዘላለሙ ባለማለፍ ጸንታ የምትኖር መንግሥተ ሰማያት ናት ማቴ5÷3፣ 1ጴጥ.3÷13 ፣ራእ 21÷1። የዋሖች ይወርሷታል። ማቴ 5÷3። እኛም ሃይማኖትን ይዘን ምግባርን ሠርተን ከተገኘን እንወርሳ ታለን። ሮሜ 8÷17፣ ገላ 3÷29። እሥራኤል ምድረ ርስትን በብዙ መከራና ደጅ ጥናት እንደወረሷት ሰማያዊት ርስት መንግሥተ ሰማያ ትም የምትወረሰው በብዙ መከራ ነው። የሐዋ.14÷22። ምክንያቱም መንገዷ ቀጭን ጠባብም ነውና። ማቴ.7÷14። በመሆኗም ወደ እርሷ ለመግባት የግድ መስቀሉን መሸከም ያስፈልጋል። ማቴ 16 ÷24። እሥራ ኤል የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ምድረ ርስትን እንደወረሷት መንግሥተ ሰማያትም የምት ወረሰው በጥምቀት በሚገኝ ልጅነት ነው። ዮሐ፡ 3÷5። ምክንያቱም እሥራኤል ቀይ ባሕርን መሻገራቸው የጥምቀት ምሳሌ ነው። ቆሮ.10÷1። ቅዱስ ጳውሎስ ሰማያዊት ኢየሩሳ ሌም ያለው መንግሥተ ሰማያትን ነው ዕብ.12÷22

ሐ• ርስታችን ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ቤተክርስቲያን ናት። ኤፌ.5÷26፣የሐዋ.20÷28 ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት። በወርቅ በዐፈር በከተማ በገጠር ብትሠራ ክብሯ አንድ ነው። ምእመናን እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ኹነው ሃይማኖታቸውን ይመሰክሩባ ታልና፣ የአንድ የክርስቶስ አካልናትና 1ቆሮ.14፣ ኤፌ4፣5 ፣ቆላ1÷18።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ከምድረ ርስት ስንዴ እና ወይን እንደተገኘ በቤተክርስቲያንም ስንዴ ሥጋውና ወይን ደሙ ይገኝባታል:: ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኰት ደሙ ተለውጦ ደመ መለኰት የሚሆነው በእርሷ ነውና:: በኢየሩሳሌም ሥጋው እንደተቆረሰ ደሙም እንደፈሰሰ ሥጋውና ደሙ ዕለት ዕለት የሚፈተትባት ናትና:: ኢየሩሳሌም ሀገረ ሰላም እንደሆነች ሁሉ የሰላም መንገድ ወንጌል የሚሰበክባት የሰላም ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝባት ናትና::

በኃጢአት የመረረውና የጠወለገው የሰው ሕይወት የሚጣፍጥባት ማር እና የሚለመልምባት ወተት ቃሉ የሚነገርባት የእግዚአሔር ቃሉ ማርም ወተትም ነውና:: መዝ.118÷103፣ ሕዝ .2÷3፣ 1ጴጥ2÷3:: በአጠቃላይ በምድር ያለች የእግዚአብሔር ርስታችን ናት::

## እሥራኤልና ምድረ ርስት፡-

እሥራኤል ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደተቀበሉት በማመን ርስታቸውን አይሸጡም አይለውጡም ነበር:: ምክንያቱም «ምድርም ለእኔ ናትና÷ እናንተም እንግዶችና መጻተኞች ናችሁና ምድርን ለዘላለም አትሸጡ:: በርስታችሁም ምድር ሁሉ መቤዠ ትን ለምድሪቱ አድርጉ » የሚል ቃል በመኖሩ ነው:: ዘሌ. 25÷23::

ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካም ልጆቻቸውም ሆኑ የልጅ ልጆቻቸውን ይህንን ጠብቀው ኖረዋል :: ለምሳሌ ናቡቴን ንግሥቲቱ ኤልዛቤል በድንጋይ አስወግራ በግፍ ያስገደለችው ለንጉሡ ለአክዓብ ሳይፈራና ሳያፍር «የአባቶቼን ርስት አልሸጥም:: አልለውጥም::» በማለቱ ነው:: ናቡቴ ጀግና በመሆኑ የአባቱን ርስት እንደያዘ የሞትን ጽዋ ለመጨለጥ በቅቷል:: 1ነገ.20÷1 -29::

## እኛስ ከዚህ የምንማረው ምንድነው?

እንግዲህ አኛ ከታሪኩ የምንማረው ነገር ቢኖር 1ኛ ርስት እመቤታችንን 2ኛ በደሙ የተመሠረተች ርስት ቤተክርስቲያናች ንን 3ኛ እንደ ተስፋ ቃሉ የምንወርሳትን ሰማያዊ ርስት መንግሥተ ሰማያትን መሸጥና መለወጥ እንደማይገባን ነው::

ናቡቴ የአባቶቼን ርስት እንዳልሸጥ እግዚአብሔር ይጠብቀኝ ብሎ በቃሉ እስከ ሞት ድረስ እንደጸና በአባቶቻችን ርስት በእመቤታችን ፍቅርና አማላጅነት ለመጽናት፣ የአባቶ ቻችንን ሃይማኖት ትውፊት በመያዝ በአባቶቻችን ቤተክርስቲያን ለመገኘት፣ የአባቶቻችን ርስት የመንግሥተ ሰማያት ዜጐች ለመሆን እኛም እስከ ሞት ድረስ መታመን ይጠበቅብናል:: ምክንያቱም የሕይወት አክሊል የሚገኘው እስከ ሞት ድረስ በመታመን ነውና:: ራእ.2÷10:: በገ ድል በትሩፋት ሃይማኖትን በመጠበቅ 2ጢሞ.4÷7::

አሥሩ ሰዎች ወደ ማኅበሩ ክፉ ወሬ በማምጣት እሥራኤል ምድረ ርስትን እንዳይወርሱ እንቅፋት አንደሆኑባቸው በዘመናችንም ወደ ማኅበሩ /ወደ ቤተክስቲያን/ክፉ ወሬ የሚያመጡ መናፍቃን የበዙበት ስለሆነ ልንጠነቀቅ ይገባናል:: አሥሩ ራሳቸው እንዳልገቡ ለሚገቡትም እንቅፋት ሆነው እንደ ተገኙ ፣ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት የሚዘጉ፣ እነርሱ የማይገቡ የሚገ ቡትንም የሚከለክሉ ሰዎች ጥቂቶች አይደሉም:: ማቴ 23÷13::

አባቶቻችን በመጋዝ የተተረተ ሩት ፣ በሰይፍ የተመተሩት ፣ በእሳት የተቃጠሉት ፣ ለአናብስት የተጣሉት ፣ ወደ ጥልቅ ባሕርም የተ ወረወሩት ለምድራዊ ዝና እና ክብር ብለው ሳይሆን ርስታቸውን ላለማ ጣት ብለው ነበር:: በመሆኑም የኑሮ አቸውን ፍሬ ማለትም ገድላቸውን ትሩፋታቸውን እየተመለከትን በእምነታቸው ልንመስላቸው ይገባል:: ዕብ 13÷7::

እሥራኤል ዘሥጋ በጉዳና እየተንጠባጠቡ የቀሩት እና በክፉ ወሬም ተሰነካክለው በቃዴስ ምድረ በዳ የረገፉት እንደ አባቶቻቸው እንደ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ መሆን እነርሱንም መምሰል ስላቃታቸው ነው:: ዛሬም እውነተኛዋን መንገድ ይዘው መጓዝ ከጀመሩ በኋላ በየጉዳናው በፈቃደ ሥጋ ተይዘው የሚቀሩ፣ በክፉ ወሬም ተሰነካክለው የሚወድቁ፤ ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት ለመመለስ የሚወስኑ፣ በአባቶች ላይ የሚያጉረመርሙ፣ እንደ ኢያሱ እና ካሌብ እውነቱን የሚናገሩ ከተገኙ ደግሞ በድንጋይ ወግረው ለማጥፋት የሚሞክሩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን አሉ:: እነኚህም የኑሮ አቸውን ፍሬ ተመልክተው አባቶቻ ቸውን መምሰልና መሆን ያቃታቸው ናቸው:: ምክንያቱም ዓይነ ልቡናቸውን አሳውረው የወንጌል ትርጓሜ /የወንጌል ኑሮ/ የሆነውን የአባቶቻችውን ገድልና ትሩፋት ሲነቅፉ ይሰማሉ::

ርስታቸውን ይዘው እንደ ናቡቴ የሞቱ አባቶቻችን ወንጌልን አንብበው ተርጉመው ያለፉ ብቻ ሳይሆኑ በሕገ ወንጌል ጸንተው በመኖር ወንጌልን በሕይወታቸው የተ ረጐሙ ናቸው:: ይህም በየገድ ሎቻ ቸው ተጽፎ ይገኛል:: ይሁን እንጂ ቃሉን ቆሞ መለፍለፍና የቤተክ ርስቲያን ልብስ ለብሶ መታየት ብቻ መንፈሳዊነት የሚመስላቸው ሥጋው ያን መንፈሳዊውን ነገር በዓይነ ሥጋ በመመልከትና በዓለም ጥበብ በመመራመር ሲዘባበቱ ይሰማሉ:: ሲያዩአቸው ሃይማኖተኞችና መንፈሳውያን የሚመስሉ ቢመረምሯቸው ግን መናፍቃንና ሥጋውያን በሆኑት ዘንድ በቤተክርስቲያን ያለው መንፈ ሳዊው ነገር ሁሉ ትምህርተ ሃይማኖቱ ፣ ሥርዓተ ቤተክርስ ቲያኑ፣ ማኅሌቱ ፣ ሰዓታቱ፤ ቅዳ ሴው፣ ጾሙ፣ ጸሎቱ፣ ዝክሩ፣ ሰንበቴው ፣ጸበሉ ፣መስቀሉ ፣ ቅኔው ትርጓሜው ወዘተ ሞኝነት ነውና:: 1ቆሮ 2÷14፣ 1ቆሮ 1÷18:: አለማስተዋል ነው እንጂ በቤተክ ርስቲያን ያለው ሁሉ ወንጌል ነው::

እኛ ግን ይህንን ሁሉ በማስተዋል በፈቃደ ሥጋ ሳንናወጥ በክፉ ወሬ ሳንሸበር በነበረው ጸንተን እንድንኖር የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን::

> **ማስታወቂያ**
>
> *በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው ቁ 3 የማኅበረ ቅዱሳን መዝሙር በገበያ ላይ ውሏል::*
>
> *መዝሙሩን በማኅበረ ቅዱሳን የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያ ያገኛሉ::*
>
> *አድራሻ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ሆኖ በሸዋ ዳቦ ቤት ወደ ዐፄ ናዖድ ትምህርት ቤት በኩል::*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ይድረስ ለከርታታው

በአካልና በስም አላውቅህም:: ነገር ግን ያለህበትን ቦታና ሁኔታ አውቃለሁ እኔም እንደአንተው ነበርኩና ጭንቀትህም ይገባኛል:: ብዙ ጊዜ በዓላማህ መጽናት አቅቶህ፣አንዱን ይዘህ ሳትጨርሰው ወደ ሌላው ስትራመድ ፣የቱን ይዘህ የትኛውን ደግሞ መተው እንደሚገባህ መወሰን አቅቶህ ብቻ ንፋስ ወዲያና ወዲህ እንደሚያወዛውዘው ዛፍ ትንከራተታለህ:: ይህን ስሜትህን ተረድቻለሁ::

ለመሆኑ እንደዚህ መሆንህን አውቀኸው ይሆን? እኔ እንጃ አይመስለኝም:: አሁን እንኳን «ከርታታው» ብዬ ስጠራህ ማንን ሊል ፈልጎ ነው? ብለህ ሌላ የምታውቀው ከርታታ እንዳለ ለማስታወስ እየጣርክ አይደል ? መልእክቴ ግን ለአንተው ነውና አስተውለው ታስታውሳለህ ? ገና ቤተክርስቲያን መምጣት እንደጀመርክ ትንሽ ፈተና ገጥሞህ መታገስ አቅቶህ «ኦርቶዶክስ መሆን አልችልም እንዲያውም ኦርቶዶክስ ትክክል አልደለም » ብለህ ወዲያው ፊትህን ወደሌላ እንዳዞርክ? እሺ ይህንን ካስታወስክ ከዚያ የሄድክበት ደግሞ ብዙው ነገር አልጥም ብሎህ ወደ ሌላ እንደተሸጋገርክና የሚስማማህን ፍለጋ እንደተንከራተትክስ ? እዚያም ከውጭ እንደሰማኸው ሳይሆንልህ ቀርቶ ሌላጋ መሄድህንስ አስታወስክ? ለዚህ እኮ ነው «ከርታታው» ብዬ የጠራሁህ:: እዚያና እዚህ ስትል ከአንዱ ወደ ሌላው ስትሻገር አንዱንም ሳትይዝ እንደተንከራተትክ አድራሻህ ጠፍቶ የማይሆን ቦታ ትወድቃለህና እባክህ ከርታታው ወንድሜ ወደ መጀመሪያው ቤትህ ተመለስ ኤፌ.4÷4

ያንተው ወንድማገኝ አበራ
/ሐረር/

## ሥርዓት ይጠበቅ

በቅዳሴ ጊዜ ወንዶችና ሴቶች ምእመናን ለየብቻ ሆነው በመካከላቸው ክፍተት ኖሮ ማስቀደስ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የነበረ ሥርዓት ነው:: እንዲያውም ሴቶች በስተቀኝ ወንዶች በስተግራ ይሆናሉ:: እኔ ባለሁበት አካባቢ ግን ወንዶችና ሴቶች ተቀላቅለው ነው የሚያስቀድሱት :: በአንድ አግዳሚ ወንበር ላይም ይቀመጣሉና ሥርዓት የተፋለሰ ይመስለኛል:: ስለዚህ ካህናትና ዲያቆናት ለማስተካከል ጥረት ቢያደርጉና ምእመናንም አው ቀውት ቢፈጽሙት ማልካም ነው:: ጌታመሣይ ተክሉ

/ቦንጋ ቅ.ሚካኤል ቤ/ክ/

## ቀው ጸልይ ከልብህ

2ጢሞ 3÷1-5

ደሀና ኑሮ ሊኖር ሁልጊዜ እንደሻተ
አንድ ቀን ሳይደላው ወንድሙ እየሞተ
ስጉት ስስታም አለ እጁን ያልዘረጋ
በራስ ወዳድነት ልቡ የተዘጋ
ለስፍስፍነት፡ የለውም ዳርቻ
እሱ የሚያስበው ስለገንዘብ ብቻ
አንተ ግን ወንድሜ ተው ጸልይ ከልብህ
በስስት መስኮት ገንዘብ የሚያስወድ
ሰይጣን ሳይገባብህ::

ከመንበሩ በላ
አለታ ወንዶ

## ምን እንበለው ?

አትስረቅ እያለኝ እርሱ ከሰረቀ
አትግደል እያለ እርሱ አንገት ካነቀ
ኀብረትን አውጆ እርሱ ከለያየ
ትኅትናን ሰብኮ እርሱው ከታበየ
ጠባቡን አስፍቶ በሰፊው ከሄደ
ዝሙትን አውግዞ በፍትወት ካበደ
ሕይወቱ እንደቃሉ ሆኖ ካልታመነ
የ «እጅ ሥራ ፎቶ » አስመሳይ ከሆነ
ጥቂት ሰው አድኖ ሰብከተ ነገሩ
ብዙውን ካጠፋ ሕይወቱ ምግባሩ
ራሱን ሳያንጽ ለሆነው ለፋፊ
ሰባኪ እንበለው ወይንስ ቀባፊ?

ደረጀ ኃ/ወልድ
/አዲሳኢታ/

## በጸሎታችሁ አስቡን፣ አጽናኑንም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የመስቀለ ብርሃን ሰበካ ጉባኤ በየመን ሀገር ይገኛል:: ይህ የሰበካ ጉባኤ በርካታ ምእመናን ሲኖሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቀጥተኛ እምነት፣ ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ በቅዱስ ሲኖዶስ እውቅናን ያገኘ ሰበካ ጉባኤ ነው:: በየገዳማቱ፣ በየአድባራቱ፣ በየሰንበት ት/ቤቱና በየሰበካ ጉባኤው የተሰበሰባችሁ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ የተዋሕዶ ቤተሰቦች በሙሉ ሰላመ እግዚአብሔር ይብዛላችሁ እያልን በግልም ሆነ በኅብረት በጸሎታችሁ እንድታስቡን በትምህርታዊና ምክራዊ ጽሑፎቻችሁ እንድታጽናኑ ንና እንድታበረታቱን በሕያው እግዚአብሔር ስም እንጠይቃለን::

አድራሻችን:-
MESKELE BEREHAN PARISH COUNCIL
P.O.BOX. 19480 /22238
SANA'A
YEMEN

# ከማኅበሩ ፍሬዎች ተቋደሱ

## ስምዐ ጽድቅ

## ሐመር

| ለደንበኝነት | | |
|---|---|---|
| ጋዜጣ | የዓመት | የ6 ወር |
| ለክፍለ ሀገር | ብር 21.00 | ብር 10.50 |
| ለአዲስ አበባ | ብር 20.00 | ብር 10.00 |
| ከሀገር ውጪ | 12 ዶላር | 6 ዶላር |

አድራሻዎን የከፈሉበትን ማስረጃ ፖ.ሣ.ቁ 800078 ይላኩልን።
የመጽሔታችን ደንበኛ ቢሆኑ አንዲትም እትም አታልፎትም።

| መጽሔት | የዓመት | የ6 ወር |
|---|---|---|
| የክፍለ ሀገር | ብር 38.00 | ብር 19.20 |
| ለአዲስ አበባ | ብር 37.80 | ብር 18.70 |
| ከሀገር ውጪ | 24 ዶለር | 12 ዶላር |

አድራሻችን - ለወ/ሮ ዓይናለም ታዬ ደመቀ
4ኪሎ ባንክ ቅርንጫፍ
የሂሳብ ቁጥር -79808
ፖ.ሣ.ቁ- 80078
ስልክ-550099 Ext 46-አ.አ

(ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ) መጽሐፍና
ፖስት ካርዶች

መዝሙር ካሴት
ቁጥር 1፣2፣3 /አማርኛ/
ቁጥር 1 /ኦሮምኛ/

ዋጋው 3 ብር ብቻ

ቦሌ ማተሚያ ድርጅት

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡